# Ethio-SHEP

# ገበያ ተኮር አቀራረብ



# የአተገባበር መመሪያ

SHEP

ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE

በአነስተኛ ይዞታ ሆርቲከልቸር አምራች አርሶ አደሮችን ገበያ
ተኮር የግብርና ዘዴ በማስተዋወቅ የማብቃት ፕሮጀክት
(Ethio-SHEP)

JICA

# Ethio-SHEP
# Implementation Guideline

Guidelines for the Implementation Process of Smallholder Horticulture Empowerment and Promotion Approach

# የርዕስ ማውጫ ገጽ


መቅድም ከግብርና ሚኒስቴር ........ 1
መቅድም ከጃይካ ........ 2
ምስጋና ........ 3
አስተዋጽኦ ያበረከቱ አካላት ዝርዝር ........ 4
መቅድም ........ 5

ምዕራፍ 1: አጠቃላይ ዳራ እና ጽንሰ-ሀሳብ ........ 7
1. አጠቃላይ ጽንሰ-ሀሳብ እና ተጨባጭ ውጤት መረዳት ........ 8
1.1. የኢትዮ-ሼፕ ፕሮጀክት አካሄድ:- መግቢያ ........ 8
2. የሼፕ ዘዴ ጽንሰ ሃሳብ ........ 10
2.1. የሼፕ ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ ........ 10
2.2. የኢትዮ-ሼፕ ትግበራ አራት (4) ወሳኝ ደረጃዎች ........ 13

ምዕራፍ 2: የ“ኢትዮ-ሼፕ” ፕሮጀክት የትግበራ ሂደት መመሪያ ........ 15
2-1: የዝግጅት ሂደት ........ 16
1. ቅድመ-ዝግጅት 1. የግንዛቤ ማሳደግያ ማነቃቂያ ወርክሾፕ እና የመነሻ ዕቅድ ዝግጅት ........ 16
2. ቅድመ-ዝግጅት 2. በፕሮጀክቱ የሚታቀፉ ወረዳዎች መምረጥ ........ 20
3. ቅድመ-ዝግጅት 3: የሼፕ የአሰልጣኞች ስልጠና ኡደት ........ 23
4. ቅድመ-ዝግጅት 4: ተጠቃሚ አርሶ አደሮችና ማህበራትን መምረጥ ........ 27
2-2: የአርሶ አደሮች አቅም የማሳደግ ስልጠና ........ 30
1. ደረጃ 1: የአርሶ አደር ተወካዮች የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም ማዘጋጀት ........ 30
2. ደረጃ 2: አሳታፊ መነሻ ጥናት ........ 33
3. ደረጃ 3: የገበያ ጥናት ........ 38
4. ደረጃ 4: የሚመረተው ሰብል መረጣ ........ 42
5. ደረጃ 5: የገበያ ትስስር መድረክ ........ 46
6. ደረጃ 6: ኢትዮ-ሸፕ ቴክኒካዊ የአሰልጣኞች ስልጠና (ቴ.አ.ስ) ........ 51
7. ደረጃ 7: አሳታፊ የችግሮች ትንተና፣ የሰብል ጊዜ ሰሌዳ እና የበጀት ዝግጅት አስራር ........ 55
8. ደረጃ 8: የመስክ-ላይ ስልጠና ........ 62
9. ደረጃ 9: የሥርዐተ-ፆታ ግንዛቤ ለማሳደግ የተዘጋጀ የስልጠና ማንዋል ........ 67
10. ደረጃ 10: የልምድ ልውውጥ ጉብኝት በማዘጋጀት የአርሶ አደሮችን የመማር ፍላጎት ማነሳሳት ........ 73
11. ደረጃ 11: የመስክ ጉብኝት ቀን/ የገበሬ በዓል ማዘጋጀት ........ 79

ምዕራፍ 3: ድጋፋዊ ክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ ........ 83
1. መደበኛ ክትትል ........ 84
2. የመጨረሻ ዳሰሳ ጥናት ........ 87

ተያያዥ ሰነዶችና ቅጾች ዝርዝር ........ 90

# የዓዕጽሮተ-ቃላት ዝርዝር

| ምዕጻረ-ቃል | (ተጨማሪ ማብራሪያ (ተያያዥ መግለጫ)) |
|---|---|
| ሰ.አ ገ.ት.መ<br>CP&IAD | የሰብሎች አመራረትና ገቢ ትንተና መረጃ/ |
| DAs | የልማት ሰራተኞች/ |
| Ethio-SHEP<br>ኢትዮ-ሸፕ | የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች ገበያ ተኮር ሆርቲካልቸር ልማት አጋዥ ፕሮጀክት/ |
| FTC | የገበሬዎች ማሰልጠኛ ማዕከል |
| ሆሰአ እና ድምአቴ 24 | የሆርቲካልቸር ሰብሎች አመራረትና የድህረ ምርት አያያዝ ቴክኒክ ጠቅላላ እዉቀት - 24 |
| GoE | የኢትዮጵያ መንግስት/ |
| ጃይካ/ JICA | የጃፓን ዓለም ዓቀፍ የልማት ትብብር ኤጀንሲ/ |
| ገ.ት.ፎ/MLF | የገበያ ትስስር ፎረም/መድረክ |
| MoA<br>ግ.ሚ. | ግብርና ሚኒስቴር |
| ABoA/ OBoA | አማራ ክልል ግብርና ቢሮ / ኦሮሚያ ክልል ግብርናና የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ቢሮ |
| M&E | ክትትልና ግምገማ/ምዘና |
| SHEP<br>ሸፕ | የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች ገበያ ተኮር ሆርቲካልቸር ልማት አጋዥ ፕሮጀክት |
| የመ. ው.ተ ማ. | የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት |

# የሰንጠረዥ ማውጫ


ሰንጠረዥ 1. የፕሮጀክቱ መግለጫ ........ 9
ሰንጠረዥ 2. ተግባር የሼፕ ዘዴ የግንዛቤ መፍጠርያ ፕሮግራም እና የመነሻ ዕቅድ አቀራረብ ስርዓት መግቢያ ........ 17
ሰንጠረዥ 3. የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ወረዳዎች ለመምረጥ የኮሚቴ ስብሰባ ማዘጋጀት (ምሳሌ) ........ 20
ሰንጠረዥ 4. በመስክ ግምገማ በመስኖ ልማት ቦታዎች ውስጥ መሰረታዊ ጉዳዮችን መካተታቸውን የምናረጋግጠበት ነጥቦች (ናሙና) ........ 21
ሰንጠረዥ 5. በፕሮጀክቱ ስለሚታቀፉ የአርሶ አደር ቡድኖች መምረጫ መስፈርቶች ........ 27
ሰንጠረዥ 6. ለተጠቃሚ አርሶ አደሮች የግንዛቤ ማሳደጊያ ቅስቀሳ መርሃ-ግብር ........ 31
ሰንጠረዥ 7. አሳታፊ መሰረታዊ መረጃ / መነሻ ዳሰሳዊ ጥናት ተግባራዊ ልምምድ ለማካሄድ የሚያገለግል መርሀ-ግብር........ 34
ሰንጠረዥ 8. ናሙና የገበያ ዳሰሳ ጥናት ተግባራትና የጊዜ ሰሌዳ ........ 38
ሰንጠረዥ 9. የጥናት ቡድን ተግባርና ሃላፊነቶች........ 39
ሰንጠረዥ 10. የሰብል መምረጥ ልምምድ ናሙና እቅድ ........ 42
ሰንጠረዥ 11. የገበያ ትስስር መድረክ መርሀ-ግብር (ናሙና) ........ 47
ሰንጠረዥ 12. የአሰልጣኞች ስልጠናን ለማካሄድ ናሙና የጊዜ ሰሌዳ ........ 52
ሰንጠረዥ 13. ናሙና መርሃ-ግበት የሰብል የማምረቻ የጊዜ ሰሌዳ እና በጀት ማዘጋጃት........ 56
ሰንጠረዥ 14. የችግር ትንተና ናሙና ቅጽ........ 58
ሰንጠረዥ 15. ምሳሌ፣ የችግር ትንተና ........ 58
ሰንጠረዥ 16. ናሙና የመስክ ላይ ስልጠና ፕሮግራም ........ 63
ሰንጠረዥ 17. በአርሲ ዞን የተዘጋጀ የልምድ ልውውጥ ጉብኝት ናሙና የድርጊት መርሃ ግብር ........ 74
ሰንጠረዥ 18. የመስክ ጉብኝት ዕቅድ ምሳሌ ........ 80


# የስዕል ዝርዝር


ስዕል 1. ያልተመጣጠነ የገበያ መረጃ የመቅረፍ ጠቃሚነት ........11
ስዕል 2. ሁለት አይነት ተነሳሽነቶች አሉ፡- ውስጣዊ እና ውጫዊ ........12
ስዕል 3. ሰዎች ሰስቱን ስነ-ልቦናዊ ፍላጎቶች (ነጻነት፣ ብቁነት (ችሎታ/ ተወዳዳሪነት) እና ተዛማጅነት) በአንድነት ሲያሳኩ ውስጣዊ ተነሳሽነት ይሰማቸዋል። አንዱ ወይም ሁለቱ ብቻ ግን በቂ አይደለም።........13
ስዕል 4. የሼፕ ትግበራ አራት ደረጃዎች ........13
ስዕል 5. የመነሻ ዕቅድ ማቅረቢያ ናሙና ቅጽ ........19
ስዕል 6. የፕሮጀክት መጨረሻ ዳሰሳዊ ጥናት መረጃ መሰብሰብያ ቅጽ........36
ስዕል 7. የመሰረታዊ መረጃ / መነሻ ዳሰሳ ጥናት የተሞላ ቅጽ - ምሳሌ........36
ስዕል 8. የመሰረታዊ/ መነሻና መጨረሻ ዳሰሳ ጥናቶች ላይ የግብርና ዘዴ ክህሎቶች መረጃ መሰብሰብያ ቅጽ-ጂ-24 ........37
ስዕል 9. የገበያ ጥናት መጠይቅ ........41
ስዕል 10. የገበያ ጥናት የተሞላ መጠይቅ ማሳያ ምሳሌ........41
ስዕል 11. የሰብል መረጣ ቅጽ ........45
ስዕል 12. የሰብል መረጣ ቅጽ -ምሳሌ........45
ስዕል 13. እቶ ፍቃዱ በገበያ ትስስር ፎረም የገበያ ዕድል አግኝተዋል *(ከአርሶ አደሮች ድምፅ, 2013 ዓ.ም። የተወሰደ)* ........50
ስዕል 14. ናሙና ቅጽ፡- የምርት ጊዜ ሰሌዳ እና በጀት ፍላጎት........59
ስዕል 15. ምሳሌ የምርት ጊዜ ሰሌዳና በጀት ፍላጎት ስሌት ........59
ስዕል 16. የሰብል ማምረቻ ጊዜ ሰሌዳ እና በጀት ማዘጋጃ ፎርም ........60
ስዕል 17. ልኬትን በተግባር መለማመጃ ፎርምእ ........75

# መቅድም ከግብርና ሚኒስቴር

Ethiopia's economy is much dependent on agriculture, with about 85% of the population relying on agriculture for their livelihood. In account of this, the horticulture development department has a major role in increasing production and productivity of farmers through implementation of improved technologies and practices. Our department has implemented the National Horticulture Development and Marketing Strategy aiming at sustainably increasing the production and productivity of horticultural crops to improve the food and nutrition security and income-generation capacity of the producers. Recently, our ministry had reform and restructured directorates. Thus the previous Horticulture Development and Technology Transfer Directorate has been upgraded to Horticulture Development Department under State Minister of Agriculture and Horticulture Development Sector and it consists of desks of Vegetables & Herbs, Fruit, Roots & Enset, and Floriculture Development.

The Ethio-SHEP project has been one of the partners in supporting our ministry's horticulture development initiatives. The project has been jointly implemented by JICA and Ministry of Agriculture (MoA), Oromia Bureau of Agriculture (OBoA) and Amhara Bureau of Agriculture (ABoA) to realize the market-oriented agricultural extension services to smallholder farmers on the ground. Through its six-year intervention, the SHEP approach has been recognized by our ministry and target regions as one of the effective & practical market-oriented extension approach.

During the intervention period, the Ethio-SHEP project developed user-friendly extension materials and distributed them to project areas in hard and soft copies that are to be utilized by counterparts during their regular training programs. The Ethio-SHEP Implementation Guideline is one of the most important documents developed through two-round workshops in June 2021 & July 2022 by agricultural experts selected from MoA, regional and zonal agricultural experts and including other partners such as, SAA and IFAD as a result of the six-year Ethio-SHEP project intervention

Our department hereby endorses the Ethio-SHEP Implementation Guideline as a final version so as to utilize it in scaling up of the SHEP approach and update periodically in line with revision of the horticulture extension package. At this opportunity, our ministry has great recognition to the Ethio-SHEP project for promoting market-oriented agriculture with smallholder horticulture farmers nearly for six years to practice "Farming as a Business" in the two regions (Amhara and Oromia) since 2017.

Mr. Abdella Negash Seid
Chief Executive Officer
Horticulture Development Department
Ministry of Agriculture

# መቅድም ከጃይካ

**S**mallholder **H**orticulture **E**mpowerment & **P**romotion (SHEP) Approach was originally developed in Kenya through a technical cooperation project between JICA and the Ministry of Agriculture of Kenya in 2006. SHEP is an approach, which helps to realize" Market-Oriented Agriculture" by transforming farmers' mind from "grow and sell" to "grow to sell". In Kenya, with this approach, the project achieved doubling income of 2,500 smallholder farmers only within 2 years (2007-2009). Since then, SHEP approach has rapidly expanded to 30 countries in Africa and 50 countries worldwide as one of the key pillars of JICA's Agricultural Cooperation.

In Ethiopia, JICA and the Ethiopian Government started the implementation of "The Project for Smallholder Horticulture Farmer Empowerment Through Promotion of Market-Oriented Agriculture (Ethio-SHEP)" in Amhara & Oromia region in 2017. The project made remarkable achievement at farmer's level (both in terms of income and production techniques) as well as significantly contributed to the capacity development of experts in the target areas.  The provisional results of the Terminal Evaluation of the project conducted in August 2022 shows that the target farmers increased crop productivity (kg/ha) and the average price of their produce (ETB/kg) after the two-year interventions by the project, which resulted in growth of their net income by 125% on average.

Building on this success, this implementation guideline was developed in collaboration with counterparts (MoA, ABoA and OBoA) based on practical experiences from the implementation of the Ethio-SHEP project in Ethiopia . After series of discussion & consultation with senior experts from Federal, Region and Zone including development partners (Sasakawa and IFAD), the guideline was finalized and has been prepared in 3 languages (English, Amharic and Afaan Oromo) with detail steps on how to implement market-oriented agriculture extension service using the SHEP approach while fully taking into account the Ethiopian context such as policy, institution, markets, and local conditions of the farmers on the ground.

The achievements from the last 6 years of the project clearly showed that the SHEP approach could definitely contribute to strengthen & transform Ethiopian agriculture extension service by changing smallholder farmers' landscape & livelihood. I hope this implementation guideline will be an integral part of the Ethiopian government's agricultural extension system and widely utilized by the agriculture extension service providers at all levels to further promote market-oriented extension service in Ethiopia.

Finally, let me express my sincere appreciation to all the agriculture experts at the Federal, Regional, Zonal and Woreda levels for their unreserved efforts to develop, finalize, and disseminate the guideline.

October 2022



Katsuki Morihara (Ph.D.)
Chief Representative
JICA Ethiopia Office

# ምስጋና

This Ethio-SHEP Implementation Guideline was developed as an output of the 1st guideline development committee workshop in June 2021 and was finalized at the 2nd guideline development committee workshop in July 2022. Committee was composed of counterparts of the Ethio-SHEP project, namely Ministry of Agriculture (Horticulture Development & Technology Transfer Directorate and Agricultural Extension Directorate), Amhara Bureau of Agriculture (Horticulture & Irrigation Water Management Directorate and Agricultural Extension Directorate), Oromia Bureau of Agriculture (Crop Development Directorate and Agricultural Extension Directorate), Agriculture Office (Horticulture Team and Extension Team) of Awi zone and West Gojam zone from Amhara region, Agriculture Office (Crop Production & Protection Team and Extension Team) of Arsi zone and Jimma zone from Oromia region, researchers from Melkasa Agricultural Research Center and development partners such as Sasakawa Africa Association (SAA) and IFAD PASIDP-II team. We sincerely appreciate their paramount contribution to development of this Ethio-SHEP Implementation Guideline (English, Amharic and Afaan Oroomo) in line with the Ethiopia National Agricultural Extension Strategy.

We would also like to send special thanks to experts and farmers of respective target woredas & kebeles who are not mentioned in this document but actually exercised the market-oriented agricultural extension by introducing the SHEP approach on the ground and brought tangible evidence of effectiveness of the SHEP approach in Ethiopian context. They are the pioneers of the SHEP approach in Ethiopia, and witness of its success in improving farmers' livelihood.

We, as the Ethio-SHEP project team, strongly believe that this Ethio-SHEP Implementation Guideline will serve as a practical guiding document for agriculture professionals who are mandated to deliver market-oriented & demand-driven extension services and will contribute to the livelihood change of smallholder farmers in Ethiopia nationwide.

November 2022



Fumiaki SASO
Chief Advisor/SHEP Approach
Ethio-SHEP Project

# አስተዋጽኦ ያበረከቱ አካላት ዝርዝር

| # | Organization | Position/Office | Name | Year |
|---|---|---|---|---|
| 1 | MoA | CEO, Horticulture Development | Mr. Abdella Negash | 2021, 2022 |
| 2 | MoA | Horticulturist, HDTTD (Ethio-SHEP focal person) | Mr. Derbew Kebede | 2022 |
| 3 | MoA | Desk Head, HDTTD | Mr. Gutu Mijena | 2022 |
| 4 | MoA | Horticulturist, HDTTD | Ms. Meseret Shiferaw | 2021 |
| 5 | MoA | CEO, Agricultural Extension Directorate | Ms. Yenenesh Egu | 2022 |
| 6 | MoA | Senior Expert, Agricultural Extension Directorate | Mr. Teshome H/Gabriel | 2022 |
| 7 | MoA | Senior Expert, Agricultural Extension Directorate | Mr. Fanta Yimam | 2022 |
| 8 | MoA | Expert, Agricultural Extension Directorate | Mr. Amsalu Geletu | 2021 |
| 9 | EIAR | Researcher, Melkasa Agricultural Research Center | Mr. Fitsum Mirutse | 2021 |
| 10 | ABoA | Expert, Horticulture & Irrigation Water Management Directorate (Ethio-SHEP focal person) | Mr. Girma Bekele | 2021, 2022 |
| 11 | ABoA | Expert, Agricultural Extension Directorate | Mr. Abebe Dessie | 2021 |
| 12 | ABoA | Expert, Agricultural Extension Directorate | Mr. Tigabu Kebede | 2022 |
| 13 | West Gojam zone | Team leader, Horticulture team | Mr. Tamene Fikrie | 2022 |
| 14 | West Gojam zone | Expert, Horticulture team (Ethio-SHEP focal person) | Mr. Degisew Adamu | 2021, 2022 |
| 15 | West Gojam zone | Expert, Agricultural extension team | Mr. Mastewal Mulu | 2022 |
| 16 | Awi zone | Team leader, Horticulture Team | Mr. Addis Alemu | 2022 |
| 17 | Awi zone | Expert, Horticulture Team (Ethio-SHEP focal person) | Mr. Embial Birhan | 2021 |
| 18 | Awi zone | Expert, Horticulture Team (Ethio-SHEP focal person) | Mr. Berihun Mebratie | 2022 |
| 19 | Awi zone | Team Leader, Agricultural Extension | Mr. Girma Tafere | 2022 |
| 20 | OBoA | Horticulture Expert (Ethio-SHEP focal person) | Mr. Sheleme Beyera | 2021, 2022 |
| 21 | OBoA | Horticulture Expert | Mr. Tolessa Woyesa | 2022 |
| 22 | Arsi zone | Team Leader, Crop production & Protection | Mr. Hussein Gemeda | 2022 |
| 23 | Arsi zone | Team Leader, Agricultural Extension | Mr. Tilahun Shambel | 2022 |
| 24 | Arsi zone | Agronomist, Irrigation Development (Ethio-SHEP focal person) | Mr. Dedefi Edaso | 2021, 2022 |
| 25 | Jimma zone | Team Leader, Crop production & protection | Mr. Asfaw Embabo | 2022 |
| 26 | Jimma zone | Team Leader, Agricultural Extension | Mr. Mekonnen Gemmachu | 2022 |
| 27 | Jimma zone | Agronomist, Irrigation Development (Ethio-SHEP focal person) | Mr. Amin Abbabiya | 2021, 2022 |
| 28 | IFAD | National Programme Coordinator, PASIDP-II | Mr. Nuredin Asaro | 2021 |
| 29 | IFAD | Agribusiness specialist, Oromia PASIDP-II | Mr. Antene Nuguse | 2022 |
| 30 | SAA | Crop Productivity Enhancement Theme Coordinator | Mr. Melese Liyhe | 2021 |
| 31 | JICA Ethiopia Office | Program officer<br>Agriculture & rural development sector | Mr. Abera Awano | 2021,2022 |

# መቅድም

ይህ የሼፕ የአሰራር (ትግበራ) መመሪያ የተዘጋጀው በኢትዮጵያ መንግስትና በጃፓን እለማቀፍ ኤጀንሲ ((JICA)) መካከል በተደረገ የሁለትዮሽ ቴክኒካዊ ትብብር ፕሮጀክት፣ ***"የገበያ መር ግብርናን በማስተዋወቅ አነስተኛ መሬት ባላቸው አርሶ አደሮች ሆርቲካልቸር ልማት የአቅም ግንባታ ፕሮጀክት" (ኢትዮ-ሸፕ***) ከተገኙ ልምዶችና ተሞክሮዎች በመነሳት ነው፡፡

የሼፕ ዘዴ ለመጀመሪያ ጊዜ ተግባራዊ የሆነው ከ2006 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ በኬኒያ ውስጥ ሲሆን፣ በጃፓንና እና በኬኒያ መንግስት መካከል በተደረገ ቴክኒካዊ ትብብር አማካይነት የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለማጠናከር ትኩረት አድርጎ ነው፡፡ የፕሮጀክቱ አቀራረብ (ዘዴ) በመስክ ደረጃ ተግባራዊ ልምምድ ሙከራ የፕሮጀክት ትግብራ ዘዴ ከተገኙ ልምዶችና ተሞክሮዎች በመነሳት ድክመቶችን በማረምና ጥሩ ተሞክሮዎች ላይ ማስፋትን መነሻ በማድረግ ነው፡፡

በፕሮጀክቱ በተደረጉት ስራዎች የተገኘው ተሞክሮ እና ልምድ መሰረት አድርጎ የግብርና የኤክስቴንሽን ዘዴነት ጥቅም ላይ እንዲውል በአብዛኛው ትኩረት የሚያደርገው የአነስተኛ መሬት ባለቤት ለሆኑ አርሶ አደሮች አቅም በማሳደግ የአርሶ አደሮችን አስተሳሰብ ወደ ገበያ-ተኮር ግብርና ማሸጋገር ማለትም ከአምርቶ መሸጥ ወደ ለመሸጥ ማምረት ለመቀየር ይሰራል፡፡

በ2022 (እ.ኤ.አ), የሼፕ ዘዴ በ23 አገሮች ውስጥ ተፈጻሚ ሲደረግ፣ ከአፍሪካ በተጨማሪም መካከለኛ ኤስያ እና ላቲን አሜሪካ አገሮች ይህንን ምርጥ ልምድ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ኢትዮ-ሼፕ ዘዴ በኢትዮጵያ ውስጥ የተጀመረው ከ2009 ዓ.ም (2017 እ.ኤ.አ) ጀምሮ ነው፡፡ በተለያዩ ቦታዎች የአነስተኛ መሬት ባለቤት የሆኑ አርሶ አደሮች ገቢ ማሳደግ ነው፡፡

በፕሮጀክት ቡድኑ በስራ ላይ ያለው የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎትን ለማሻሻል የሚያስችሉ ሥራዎች ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ኢትዮ-ሼፕ ፕሮጀችት በኢትዮጵያ ውስጥ ተግባራዊ የተደረገው በኬኒያ ውስጥ ከዳበረው የመጀመርያ ዘዴ (original SHEP approach) በመከለስ እና ከአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ እንዲስማማ ተደርጎ ስለተቀረጸው "ኢትዮ-ሼፕ አቀራረብ"/ Ethio-SHEP Approach/ እውን ሊሆን ችሏል፡፡ በኢትዮጵያ አሁን ካለው የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ስርዓትና የተቋማቱ የትግበራ ሂደት ሁኔታ ጋር በማዋሃድና በማቀናጀት በፕሮጀክቱ ተግባራት ውጤት መሰረት ነው፡፡

**የመመሪያው ዓላማ**

የዚህ የአሰራር (ትግበራ) መመሪያ ዋና አላማ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ሰጪዎች በሼፕ ዘዴ (ገበያ ተኮር የሆኑ) ስልጠና ፕሮግራሞች መቅረጽና መፈጽም እንዲችሉ ድጋፍ መስጠት ነው፡፡ የአሰራር መመሪያው ተጠቃሚዎች በግብርና ኤክስቴንሽን ሥርዓት ውስጥ በማካተት በየደረጃው በሚገኙ ፈፃሚ አካላት ዘንድ በተሟላ መልኩ ተግባራዊ እንዲደረግ ለማገዝ ይረዳ ዘንድ የተዘጋጀ ነው፡፡ ይህ የአሰራር መመሪያ ከፌደራልና ክልል እሰከ ወረዳና ቀበሌ ድረስ በሆርቲካልቸር ሰብሎች ላይ የኤክስቴንሽን አገልግሎትና የሙያ ድጋፍ ለመስጠት ሀላፊነት የተሰጣቸው የግብርና ባለሙያዎችና የልማት ሰራተኞች እንዲያገለግል የቀረበ ጥንቅር ነው፡፡

ይህ የአሰራር መመሪያ በአመታዊ መደበኛ የመንግስት ስልጠና ፕሮግራሞች ከፌደራል ግብርና ሚኒስቴር እስከ ክልል መንግስታት ግብርና ድረስ እንዲሁም በክልል ባለሙያዎች በዞን ለሚሰጡ ስልጠናዎች በተሟላ መልኩ ተግባራዊ እንዲደረግ ለማገዝ ይረዳ ዘንድ የተዘጋጀ ነው፡፡ በተጨማሪም ሌሎች ባለድርሻ አካላት ለግብርና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ስልጠና በማካተት በየደረጃው ድጋፍ ለሚሰጡ የልማት አጋሮች ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡

የመመሪያው ተጠቃሚዎች የ"ኢትዮ-ሼፕ ዘዴ"ን በክልል፣ ዞን፣ ወረዳና ቀበሌ በራሳቸው አቅም ተግባራዊ እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡ ለዚህም አንደ ደጋፊ የትግበራ ማጣቀሻ ይረዳቸው ዘንድ የትግበራ ሥራውን ለማገዝ የሚረዱ ስልቶችን (ናሙና ቅጾችን፣ ማሳያ ሰንጥረዦችን፣ ሞዴል ፕሮግራሞችን) በማካተት ቀርቧል፡፡ ይህ የአሰራር መመሪያ የተዘጋጀው በፕሮጀክቱ ውስጥ በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች በሚገኙ ልምዶች መሰረት ያደረገ ስለሆነ በተለያዩ ክልሎች ለሚገኙ ፈጻሚ አካላት በአካባቢያቸው ባለው ነባራዊ ሁኔታ ላይ መሰረት ያደረገ በሰነዱ የተካተቱትን

ናሙና/ ምዴል ፕሮግራሞች፣ ማሳያ ቅጾችና የስልጠና ቁሳቁሶች ማስተካከያ ማድረግ ኢትዮ-ሼፕ ያበረታታል።

**የመመሪያው አወቃቀር**

ይህ አሰራር (ትግበራ) መመሪያ በሶስት ምዕራፎች የተከፈለ ነው። የመጀመሪያው ምዕራፍ ጠቅለል ያሉ ሀሳቦችን የያዘ ሲሆን በዚህ ክፍል የሼፕ ዘዴ አመጣጥ አጠቃላይ ዳራ፣ የንድፈ ሃሳብ ማዕቀፎችን፣ ኢትዮ-ሼፕ ፕሮጀክት ያስፈለገበት ምክንያቶች ተካተዋል፡፡ ሁለተኛው ምዕራፍ ኢትዮ-ሼፕ" ፕሮጀክት ትግበራ ሂደት ደረጃ በደረጃ ያቀርባል ። በተለይም ይህ ክፍል በተለያዩ ደረጃዎች ለሚገኙ ፈጻሚ አካላት በተጨባጭ ስልጠናዎች፣ ወርክሾፖች፣ ሌሎች ተግባራትን በማዘጋጀት ሂደት ላይ የምንጠቀምባቸውን ዘዴዎች በቅደም ተከተል ይተነትናል፡፡ ሶስተኛው ምዕራፍ አሳታፊ ስልቶች ያካተተ የሼፕ ተግባራት ክትትልና ግምገማን ይዘረዝራል። ሁለቱም፡/ምዕራፍ 2 እና ምዕራፍ 3 /በእያንዳንዱ ተግባር ውስጥ የተመሠረተ አጠቃላይ መግቢያና እንዲሳኩ የሚጠበቁ ዝርዝር አላማዎች ያቀርባል፡፡

ከዚህ የአሰራር መመሪያ በተጨማሪም የኢትዮ-ሼፕ ፕሮጀክት ቡድን ከአጠቃላይ ኢትዮ-ሼፕ ዘዴ መተግበሪያ መመሪያ አንኳር ተግባራት በመውሰድ "ኢትዮ-ሼፕ ቀላል ፓኬጅ" የተሰኘ ቅጂ አዘጋጅቷል። ይህ ሰነድ የተዘጋጀው በአነስተኛ በጀት የሼፕ ዘዴ የአርሶ አደሮችን ወደ ገበያ መር ግብርና ለመደገፍ ተከታታይ የሆኑ ተግባራትን ቀርጿል። ከነዚህም መካከል ካሚሺባይ የኤክስቴንሽን መተግበርያ፣ ተባይ እና በሽታ ክስተትን ለመከታተል፣ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተዘጋጀ መመሪያ፣ የሥርዓተ-ፆታ ሁኔታ ትንተና ማዕቀፍ፣ እንዲሁም በርካታ ፎርሞች፡- የገበያ ጥናት፣ የሰብል መምረጥ ቅጽ፣ የፕሮጀክት መሰረታዊ መረጃና የመጨረሻ ዳሰሳ ጥናት ቅጾች፣ የሰብል የጊዜ ሰሌዳ፣ የምርት አጠቃላይ በጀት ስሌት የመሳሰሉትን መተግበርያ ሰነዶች ተዘጋጅተዋል። እነዚህ ለተጠቃሚ ምቹ የሆኑ መመሪያዎች፣ ማንዋሎች እና ቅጾች የተዘጋጁት በርካታ ፎቶግራፎችና ገላጭ ማሳያዎች በማካተትና በተጨማሪም ከመስክ የተገኘው ተሞክሮን መሰረት ያደረገ አቀራረብ በመሆኑ ተጠቃሚ ህብረተሰብ ክፍሎች በቀላሉ ሊረዱትና ጥቅም ላይ ሊውል እንደሚችል ይታመናል፡፡

ስለሆነም ይህ የአሰራር መመሪያ /ማኑዋል/ በኢትዮጵያ የግብርና ኤክስቴንሽን ሥርዓት ውስጥ በተለያዩ ደረጃ የተሰማሩትን የግብርና ባለሙያዎች ጠቃሚ የሙያ ድጋፍ መመሪያ /ማኑዋል/ ሊሆን እንደሚችል ተስፋ እናደርጋለን። በተጨማሪም በአነስተኛ አርሶ አደሮች ሰብል ልማት ወደ ገበያ-ተኮር የግብርና አሰራር የሚደረገውን ሽግግር ለማሳለጥና ኑሮአቸውን ለማሻሻል አጋዥ የሆኑ ባለድርሻ አካላት ይረዳ ዘንድ ታምኖበታል።

# ምዕራፍ 1: አጠቃላይ ዳራ እና ጽንሰ-ሀሳብ

## አጠቃላይ ጽንሰ-ሀሳባዊ ዳራ እና የፕሮጀክቱ ውጤት መረዳት

# 1. አጠቃላይ ጽንሰ-ሀሳብ እና ተጨባጭ ውጤት መረዳት

## 1.1. የኢትዮ-ሼፕ ፕሮጀክት አካሄድ:- መግቢያ

**<u>የኢትዮ-ሼፕ ፕሮጀክት አጠቃላይ ዳራ</u>**

ግብርና የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ነው። በመሆኑም ከጠቅላላ አመታዊ ምርት መጠን (GDP) ግማሽ አካባቢ ለ85 በመቶ ኢትዮጵያዊ መተዳደሪያና በግምት 90 በመቶ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ በመሆኑ የሀገሪቱ ዋነኛ የኢኮኖሚ መሰረት ቅድሚያ በመስጠት የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ መፍጠር እና ኢኮኖሚውን ማሳደግ ዋነኛ ተግባር ነው።

ኢትዮጵያ ዘላቂነት ያለው የግብርና ልማት ማካሄድ የሚያስችሉ የተለያዩ የስነ-ምህዳር ቀጠናዎች፣ ሰፊና ለእርሻ ተስማሚ መሬት፣ በቂ የዝናብ መጠንና ከፍተኛ የሰው ጉልበት ሀብት እንዳሏት ይታወቃል። ይህንን የተፈጥሮ ሀብቷን በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል መንግስት የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚው ለማዘመን የኤክስቴንሽን አገልግሎቱ ማጠናከር አንዱ የግብርና ፖሊሲን የማሻሻል አካል እንደሆነ ይታወቃል። ምንም እንኳን ከፍተኛ እምቅ አቅምና የመንግስት ሰፊ ጥረት ቢኖርም አሁንም አነስተኛ ይዞታ ባላቸው አርሶ አደሮች የኑሮ ደረጃቸውን ለማሻሻል ፈታኝ ሆኖ ቆይቷል።

በዘርፉ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችን ለመፍታት መንግስት በ2017 (እ.ኤ.አ) የኤክስቴንሽን ስትራቴጂ ቀርጿል። ይህ ስትራቴጂ ትኩረት የሚያደርገው አነስተኛ መሬት ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮች ከባህላዊ አመራረት ስርአት (አምርቶ ከመሸጥ) ወደ ገበያ-ተኮር ግብርና (ለመሸጥ ማምረት) ማሸጋገር ያለውን ጠቀሜታ አመላክቷል። በዚህ ሂደት አነስተኛ መሬት ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮች አስተሳሰባቸውን ወደ ገበያ-ተኮር ግብርና ለማሸጋገር ይቻል ዘንድ የኢትዮጵያ መንግስት ለጃፓን ዓለም ዓቀፍ የልማት ትብብር (JICA) የድጋፍ ጥያቄ አቅርቧል። በመቀጠልም በመንግስትና በጃይካ (JICA) መካከል በተደረገ ምክክር ተከትሎ “አነስተኛ ይዞታ ያላቸውን አርሶ አደሮች ገበያ ተኮር የአትክልት/ፍራፍሬ ልማት አጋዥ ፕሮጀክት” የተሰኘ የስልጠና ፕሮግራም ከ2014 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ መስጠት ተጀመረ።

በጃፓን አገር ስልጠና ከወሰዱ በኋላ የበፊት ተሳታፊዎች በኦሮሚያ ክልል የሙከራ (pilot) ፕሮጀክት ተግባራት ተጀምሯል። ፕሮጀክቱ በትግባራ ሂደት እያለ ቢሆንም በታቀፉት አርሶ አደሮች መካከል በርካታ አዎንታዊ ለውጦች ተስተውለዋል። ለመጥቀስ ያክል ግብዓት በጋራ መግዛትና ምርት በጋራ የመሸጥ ተግባራት እና ተጨማሪ ሰብሎች የማምረት (ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው እንደ ነጭ ሽንኩርት ጨምሮ) ለውጦች ታይተዋል።

ከሙከራ ስራዎች የተገኘው ውጤታማ ተሞክሮ ተከትሎ አሁን በትግበራ ያለው ፕሮጀችት “**አነስተኛ የመሬትይዞታ ያላቸውን አርሶ አደሮች ገበያ ተኮር የአትክልት/ፍራፍሬ ልማት አጋዥ ፕሮጀክት(ኢትዮ-ሼፕ)**” ከ2017 እ.ኤ.አ ጀምሮ በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች በሚገኙ 14 ወረዳዎች ተግባራዊ ተደረገ። ይህ ሰነድ የተዘጋጀው ፕሮጀክቱ ላለፉት ሰባት (7) አመታት በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች የተገኙ ልምዶች መሰረት በማድረግ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

## የፕሮጀክቱ አጭር መግለጫ

**የፕሮጀክት ስም**:- አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮች ገበያ ተኮር የአትክልት/ፍራፍሬ ልማት አጋዥ ፕሮጀክት (ኢትዮ-ሼፕ)

**ፈጻሚ አካል / የፕሮጀክቱ ባለቤት**:- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግብርና ሚኒስቴር፣ የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ እና የኦሮሚያ ክልል የግብርናና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ፣

**የፕሮጀክቱ ቆይታ**:- እ.ኤ.አ ጥር 2017 - ጥር 2023

**ተጠቃሚዎች**:- ሰራተኞች (የግብርና ሚኒስቴር፣ የአማራና ኦሮሚያ ክልሎች የግብርና ቢሮዎች)፣ አነስተኛ መሬት ያላቸው አርሶ አደሮችናቸው፡ ፡ (ጠቅላላ ተጠቃሚዎች[1]: በግምት 6,000 አርሶ አደሮች)

**የተመረጡ ቦታዎች**: በአማራ ክልል በአዊ ዞን እና ምዕራብ ጎጃም ዞኖች በሚገኙ 7 ወረዳዎች፣ በኦሮሚያ ክልል አርሲና ጂማ ዞኖች የታቀፉ 7 ወረዳዎች ናቸው፡፡

**ሰንጠረዥ 1. የፕሮጀክቱ መግለጫ**

| | |
|---|---|
| **የፕሮጀክቱ ስም፡-** | አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮች ገበያ ተኮር የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት አጋዥ ፕሮጀክት (ኢትዮ-ሼፕ) |
| **የፕሮጀክቱ ጊዜ፡-** | ጥር 2017 - ጥር 2023 እ.ኤ.አ.(6 ዓመት) |
| **ፈጻሚ /የፕሮጀክቱ ባለቤት፡-** | የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግብርና ሚኒስቴር፣ የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ እና የኦሮሚያ ክልል ግብርናና የተፈጥሮ ሀብት ቢሮ፣ |
| **በፕሮጀክቱ የሚታቀፉ ቦታዎች፡-** | አስራ አራት (14) ወረዳዎች ፣- ሰባት (7) ከአማራ ክልል፣ ሰባት(7) ከኦሮምያ ክልል, |
| **የፕሮጀክቱ ግብ፡-** | የሼፕ አቀራረብ ገበያ ተኮር ግብርና በኢትዮጵያ መንግስት ተግባራዊ ይደረጋል |
| **የፕሮጀክቱ ዓላማ፡-** | የሼፕ ዘዴን በስኬታማነት ተፈጻሚ ሲደረግ አርሶ አደሩ ከአትክልት ልማት የሚያገኘውን ገቢ መጨመር ሰለሚያስችል ፕሮጀክቱ በሌሎች ቦታዎች የማስፋፋት ተግባር ይቀጥላል |
| **የፕሮጀክቱ ውጤቶች፡-** | **ውጤት 1.** የኤክስቴንሽን አገልግሎት የመስጠት አቅምን በሼፕ ዘዴ መሰረት መገንባት መቻሉ፥<br>**ውጤት 2.** ስኬታማ የኤክስቴንሽን አገልግሎት በሼፕ ዘዴ መሰረት በፕሮጀክቱ ለታቀፉ አርሶ አደሮች መስጠት መቻሉ፥<br>**ውጤት 3.** የሼፕ የተቀናጀ የኤክስቴንሽን ፓኬጆች ማለትም ሙሉ ፓኬጅ በሼፕ ለታቀፉ አርሶ አደር ቡድኖች የሚሰጥ እና ከፊል የሆኑትን ፓኬጆች በተለያዩ ስልጠና እድሎች ላይ ተፈጻሚ ሲደረግ ለቀጣይ ትግበራም ጥቅም ላይ እንዲውሉ እቅድ ይዘጋጃል፡፡ |

[1] ተጠቃሚ አርሶ አደሮች ሁለት ክፍሎችን ያካትታል፡- (1) በፕሮጀችት የታቀፉትን አርሶ አደሮች፣ (2)የፕሮጀቱ ተጠቃሚ አርሶ አደሮች አባል የሆኑባቸው የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት። ፕሮጀክቱ የተቀረጸው ቀጥተኛ ያልሆኑ ተጠቃሚ አርሶ አደሮች በ(2)ኛው ክፍል የታቀፉ ሲሆን፣ ምክንያቱም አንዳንድ የስልጠና እድሎች በቀጥታ ለታቀፉት አርሶ አደሮች ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት አባላት የሆኑትን አርሶ አደሮች ያካትታል።

# 2. የሼፐ ዘዴ ጽንሰ ሃሳብ

## 2.1. የሼፐ ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ


የሼፐ ዘዴ ጽንሰ ሃሳባዊ እድገት ከሁለት (2) አካዳሚያዊ ንድፈ-ሀሳቦች ጋር ትስስር አለው ። እነሱም፡- **"ተመጣጣኝ ያልሆነ መረጃ ላይ የተመሰረተ ግብይቶች"** (markets with asymmetric information) በሚለው የኢኮኖሚ ጽንሰ-ሃሳብ እና **"በራስ መወሰን ንድፈ-ሀሳብ"** (Self Determination Theory) በሚለው የስነ-ልቦና ጽንሰ ሃሳብ ናቸው። ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

### 2.1.1. ያልተመጣጠነ የገበያ መረጃ (Markets with asymmetric information)

ተመጣጣኝ ያልሆነ መረጃ አለ ማለት በገዢና ሻጭ መካከል ተመጣጣኝ ያልሆነ መረጃ ሲኖራቸው እንደ ማለት ነው። ለምሳሌ፣ አርሶ አደሮች በግብይት ዙርያ ያላቸው መረጃ (የምርቶቻቸውን ተፈላጊ ጥራት/ምርት መጠን (ብዛት) የዋጋ መዋዠቅ፣ በገበያ ተፈላጊነትና ከፍተኛ ፍላጎት ያለው የምርት ዝርያ) አናሳ ከሆነ ጅምላ ሻጮች ወይም ነጋዴዎችና ደላሎች የአርሶ አደሮችን የመረጃ ክፍተት አንደ ደካማ ጎን ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ስለሆነም በአምራቾችና በተቀባዮች መካከል የሚደረገው የድርድር ሂደት በአምራቾቹ ያነሰ ተጠቃሚነት ላይ የመጠናቀቁ እድል ከፍተኛ ነው። በዚህም ምክንያት አምራቾች ምርታቸውን በአነስተኛ ዋጋ ለመሸጥ ይገደዳሉ።

**በዚህ ጽንሰ ሃሳብ** መሰረት፣ እጅግ ወሳኝ ከሆኑ ነገሮች ቀዳሚው ትኩረት በተለያዩ የገበያ እሴት ሰንሰለት ተዋንያን መካከል **የጋራ መተማመን** መገንባት ነው። ይህንን ክፍተት ለመሙላት ኢትዮ-ሼፐ በርካታ ተግባራትን ያከናውናል። ከአርሶ አደሮች አንጻር፡- የገበያ ጥናት፣ የሰብል ማምረት የጊዜ ሰሌዳን ማዘጋጀት፣ የወጪና ገቢ የሂሳብ ስሌት (በጀት) ዝግጅት፣ የገበያ ትስስር ፎረም መሰተፍ እና በኤክስቴንሽን ሰራተኞች በኩል ቀጣይነት ያለው ቴክኒካዊ ድጋፍና/ምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ማስቻልን ያካትታል።

***ከምርት ተቀባዮች/ገዢዎች አንጻር ሲታይ*** አምራቾች በቂ ምርት ለማቅረብ ከቻሉ ጅምላ ሻጮች የማምረቻው ቦታ ርቀት ቢኖረውም ከአምራቾቹ ቦታ ደርሶ በመረክብ አትክልትን የመግዛት ፍላጎት ይኖራቸዋል። በሌላ በኩል በአቅራቢያቸው ገበያ ካገኙ አምራቾችም በቂ ምርት ማቅረብ ይችላሉ። ይህ ማለት ምርታቸውን ወደ ማዕከላዊ ገበያ ለማጓጓዝ ከፍተኛ ወጭ የሚጠይቅ በመሆኑ የአርሶ አደሩ የማምረት አቅምና ፍላጎት ይቀንሳል። ጅምላ ሻጮች ከአምራቾች የሚረከቡ ከሆነ ግን ምርታቸውን ማሳደግ ብቻ ሳይሆን የማጓጓዣ ዋጋን ቀንሰው የመሸጥ ፍላጎት ይኖራቸዋል። በሼፐ ዘዴ እሳቤ መሰረት የገበያ ጥናትና የገበያ ትስስር ፎረም (መድረክ) ተግባራት ጅምላ ሻጮችና አርሶ አደሮች ውይይት በማድረግ የመረጃ ክፍተቱን የመሙላት አቅም አለው።




ስዕል 1. ያልተመጣጠነ የገበያ መረጃ የመቅረፍ ጠቃሚነት

### 2.1.2. **የራስ ጉዳይ በራስ መወሰን ንድፈ-ሀሳብ** (self-determination theory)

***ተነሳሽነት ምንድ ነው?***

ተነሳሽነት (Motivation) ስንል “አንድን ነገር አደርገዋለሁ” ብለን ማሰብ እንድንጀምር የሚያነሳሳን ባህሪ ነው ተብሎ ሊገለጽ ይችላል፡፡ የተነሳሽነት አይነቶች በሁለት ሊከፈል ይችላል፡- 1) ውስጣዊ ተነሳሽነት፣ እና 2) ውጫዊ ተነሳሽነት (ስዕል 2 ይመልከቱ) ፡፡

**ውስጣዊ ተነሳሽነት፡-** ውስጣዊ **ተነሳሽነት ያላቸው ሰዎች** አንድ ስራ የሚሰሩበት ገፊ ምክንያት በስራው ውጤት ውስጣዊ ግለ-እርካታ ስለሚያገኙበት ነው ፡፡ ባንጻሩ ደግሞ አንድ ሰው አንድን ነገር እንዲሰራ ያነሳሳው ምክንያት ውጫዊ ተጽዕኖ (ለምሳሌ፡ ሽልማት ለማግኘት ወይም ቅጣትን በመፍራት) ከሆነ ገፊ ምክንያቱ **ውጫዊ ተነሳሽነት** ይባላል፡፡ ተነሳሽነትን በተመለከተ ከውስጣዊ ወይም ውጫዊ ፍላጎት የመነጨ መሆኑን ለመወሰን “የራስን ጉዳይ በራስ መወሰን” (self-determination theory) በሚባለው ንድፈ-ሀሳባዊ ማዕቀፍ ላይ የተመሰረተ የሰው ስነ-ልቦናዊ/ የሳይኮሎጂካል ፍላጎቶች ማዕቀፍ መጠቀም ይቻላል፡፡




ስዕል 2. ሁለት አይነት ተነሳሽነቶች አሉ፡- ውስጣዊ እና ውጫዊ


ይህ በራስ የመወሰን ጽንሰ-ሃሳብ እንደሚገልጸው ሰዎች ተፈጥሮአዊ የሆኑ ሶስት(3) ስነ-ልቦናዊ ፍላጎቶች አላቸው። እነሱም፥ ነጻነት (autonomy)፣ ብቃት (competence) እና ተዛማጅነት (relatedness) ይባላሉ። (ስዕል 2 ይመልከቱ)። በጽንሰ ሃሳቡ እሳቤ መሰረት ሰዎች እያንዳንዱ ፍላጎታቸውን ይበልጥ ባሳኩ መጠን ስራቸውን በውስጣዊ ተነሳሽነት እንደሚሰሩ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ውስጣዊ ተነሳሽነት ስራችንን ይበልጥ እንድንወደው ያደርጋል።

**ነጻነት/በራስ የመመራት አቅም (**Autonomy) ውሳኔ ሰጭነትን ይመለከታል። ይህ ፍላጎት የሚለካው ሰዎች የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸው ፍቃድ ተመስርተው መወሰን ሲችሉ ነው። በንጻሩ ደግሞ፡ በሌሎች ሰዎች ሲነገራቸው/ በውጫዊ ተፅዕኖዎች ምክንያት ከሆነ/ በውሳኔው ደስተኛ አይሆኑም።

**ብቃት (Competence) -** ማለት አንድን ስራ በአግባቡ ለመፈጸም የሚያስችሉ ግለ-ክህሎቶችን ይመለከታል። ብቃትን ለማመልከት የስራው አይነት በጣም ቀላል ወይም በጣም ከባድ/ውስብስብ መሆን የለበትም። ለምሳሌ:- ለአንድ ጀማሪ አርሶ አደር የተሻሻለ የድንች ዝርያ በሰፊ ማሳ ላይ ማምረት ከባድ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የሚያስፈልገውን መነሻ ካፒታል እና የሰው ጉልበት ታሳቢ በማድረግ በአነስተኛ መደብ መጀመር ይቻላል። ምክንያቱም የተሻሻለ ዝርያ መጠቀም ከፍተኛ እንክብካቤን ይፈልጋል። እንደሚታወቀው የተሻሻሉ የሰብል ዝርያዎች ከአካባቢ ዝርያ ይልቅ ብዙ ጊዜ ለተባይና በሽታ ጥቃት ይበልጥ ተጋላጭ በመሆናቸው ነው። በተለይ ስነ-ምህዳሩ ምቹ ካልሆነ ከባቢያዊ ሁኔታዎች (ከፍተኛ እርጥበት አልያም በጣም ደረቅ ሁኔታ) ችግሩን ከባድ ያደርገዋል። ከዚህ አንጻር የኢትዮ-ሼፕ ፕሮጀክት አቀራረብ የአርሶ አደሮችን ችሎታ/ተወዳዳሪነት ለማሳደግ ያላቸውን ክፍተት በመለየት የተመረጡ ሰብሎችን ለማምረት ተግባራዊ ቴክኒካዊ ስልጠናዎችን እና ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የምክር አገልግሎት መስጠት ላይ ትኩረት ያደርጋል።

ለአንዳንድ ሰው ቀላል የሆነ ለሌላ ሰው ከባድ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ የኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ለአርሶ አደሮች ተገቢ መረጃ በመስጠት ተነሳሽነታቸውን ከፍ ለማድረግ ቁልፍ ተግባር ነው።

**ተዛማጅነት (Relatedness) -** ማለት ሰዎች በአካባቢያቸው ያላቸውን የማህበራዊ ትስስር ደረጃ የሚያዩበትን ስሜት ያመለክታል። ***ለምሳሌ፡-*** ጓደኛህ ካንተ ድጋፍ ስትጠይቅ /ሲጠይቅ እሷን/ እሱን ማገዝ ችግር ላይኖርብህ ይችላል። ነገር ግን የማትወደው ሰው ከሆነ ለድጋፍ የጠየቀህ ስሜትህ ምን ሊመስል ይችላል? እሷን/እሱን የማገዝ ፍላጎት አይኖርህም። የዚህ ምሳሌ ቁልፍ የሆነው መልዕክት የኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ከአርሶ አደሮች ጋር ያላቸውን ግንኙነት መገንባት ቀዳሚ ተግባር ነው። ይህን ለማሳካት ኢትዮ-ሼፕ በአርሶ አደሮች እና በባለ ድርሻ አካላት መካከል ያለውን ትስስር ለማጠናከር ዕድል ይፈጥራል።




ስዕል 3. ሰዎች ሶስቱን ስነ-ልቦናዊ ፍላጎቶች (ነጻነት፣ ብቁነት (ችሎታ/ ተወዳዳሪነት) እና ተዛማጅነት) በአንድነት ሲያሳኩ ውስጣዊ ተነሳሽነት ይሰማቸዋል። አንዱ ወይም ሁለቱ ብቻ ግን በቂ አይደለም።

ከላይ ከተዘረዘሩት ፍላጎቶች አንዱም ካላሟሉ አርሶ አደሮች ምንም አይነት ተነሳሽነት የላቸውም። በተቃራኒው ደግሞ ሁሉንም ፍላጎቶች ያሳኩ ከሆነ ሙሉ ውስጣዊ ተነሳሽነት ይኖራቸዋል

## 2.2. የኢትዮ-ሼፕ ትግበራ አራት (4) ወሳኝ ደረጃዎች

የኢትዮ-ሼፕ ዘዴ ከላይ የተገለጹትን ሁለቱ (2) አካዳሚያዊ ንድፈ-ሀሳቦች እውን ለማድረግ፡- የአርሶ አደሮችን ተነሳሽነት ለማሳደግ የሚያስችሉ ተከታታይ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችና የምክር አገልግሎት በጥንቃቄ ተቀርጸው ደረጃ በደረጃ ተፈጻሚ ይደረጋሉ። የኢትዮ-ሼፕ ዘዴ በፕሮጀክት ቀረጻና ትግበራ ሂደት በ4 ዋና ደረጃዎች መሰረት ያደረገ ሆኖ፣ ቁልፍ የሽፕ ፕሮጀክት ተግባራት ከዚህ በታች በቅደም ተከተል ተዘርዝረዋል፡፡

ደረጃ1: የፕሮጀቱ ግብ ከአርሶ አደሮች ጋር መጋራት ደረጃ 2: የአርሶ አደሩን ግንዛቤ ማሳደግ ደረጃ 3. የአርሶ አደሮች የመወሰን አቅም ማጎልበት ደረጃ 4. አርሶ አደሩ ክህሎት ማግኘት (ስዕል 4 ይመልከቱ). እነዚህ አራት ደረጃዎች ከዚህ በታች በቅደም ተከተል ተዘርዝረዋል፡፡

| **አራት (4) ደረጃዎች** | **ዋና ዋና ተግባራት (Activities)** |
|---|---|
| 1. ግቡን እና ዓላማውን ለአርሶ አደርና ለአጋር አካላት ማስተዋወቅ | - የትውውቅ ፕሮግራም ማካሄድ |
| 2. የአርሶአደሮችን ግንዛቤ ማሳደግ | - አሳታፊ መሰረታዊ መረጃ የዳሰሳ ጥናት<br>- የገበያ ጥናት |
| 3. የአርሶአ ደሮችን ውሳኔ ሰጭነት አቅም ማሳደግ | - የሰብል መምረጥ<br>- የሚያጋጥሙ ችግሮችን ልየታ ፣ የሰብል አመራረት የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀትና ማለማመድ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የባለድርሻ አካላት መድረክ ማዘጋጀት |
| 4. የአርሶአደሩን እዉቀትና ክህሎት ማሳደግ | - በገበሬ ማሳ ላይ ስልጠና መስጠት<br>- የስርዓተ ፆታ ስልጠና በመስጠት ግንዛቤ ማሳደግ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የልምድ ልውውጥ እና ጉብኝት ማካሄድ<br>- የመስክ ቀን/ የልምድ ልውውጥ ጉብኝት |
| የክትትልና ግምገማ (አሳታፊ የመጨሻ ውጤት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድን ያካትታል) | |

ስዕል **4**. የሼፕ ትግበራ አራት ደረጃዎች

**ደረጃ 1. የሼፐ ግብ ከአርሶ አደሮች ጋር መጋራት**

ኢትዮ-ሼፐ ፕሮጀክት አቀራረብ የተቀናጀ አሳታፊና ከታች ወደ ላይ አካሄድ መሰረት ያደረገ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መሆኑን ለአርሶ አደሮች ማስተዋወቅ አስፈላጊ ነው። ዓላማውን ገና ከጅምሩ ከአርሶ አደሩ ጋር ውይይት በማድረግ በኢትዮ-ሼፐ ለታቀፉት አርሶ አደሮች ፕሮጀክቱ የሚያስገኝላቸውን ጥቅም ማስተዋወቅ እና በሼፐ ዘዴ የትኞቹ ተግባራት የሚያካትት መሆኑን በግልጽ ማሳውቅ ወሳኝ ምዕራፍ ነው። የዚህ ሂደት ዋና ዕሳቤ ተሳታፊ አርሶ አደሮችን በፍቃደኝነት በመምረጥ፣ አቅማቸውን በመገንባት እና ያላቸውን ሀብት በአግባቡ በመጠቀም ኑሮዋቸውን በዘላቂነት እንዲያሻሽሉ ማድረግ ይቻላል።

**ደረጃ 2፡ የአርሶአደሩን ግንዛቤ ማሳደግ**

ይህ በዋናነት አርሶ አደሩ ነባራዊ ሁኔታውን ለመረዳት ይችል ዘንድ አሳታፊ የሆኑ መሰረታዊ የመረጃ ዳሰሳና የገበያ ጥናት ማካሄድን ያካትታል፡፡ የገበያ ጥናት የሚካሄደው አርሶ አደሮች ያሉትን እድሎች እንዲያውቁና ለአትክልት ሰብል ልማት የሚሆን ዕምቅ ምቹ ሁኔታዎችን እንዲያውቁ የሚረዳ ነው። የአርሶ አደሩን ግንዛቤ ለማሳደግ አርሶ አደሮች በአትክልት ማምረት ዙሪያ ያሉትን ዕድሎች/ አቅም እንዲረዱት የመጀመሪያው ተግባር **“ግብርናንእንደ ንግድ ሥራ”** ማሰብ የሚፈጠርበት ሂደት ነው ።

**ደረጃ 3: የአርሶ አደሮችን የመወሰን አቅም ማጎልበት**




ደረጃ 3 የአርሶ አደሩን የመወሰን አቅም ማሳደግ

የዚህ ተግባር አላማ በደረጃ 2 የገበያ ጥናት ውጤትና የአካባቢውን ስነምህዳር መሰረት በማድረግ አርሶ አደሩ የሚያመርተውን ሰብል እንዲመርጥ ማድረግ ፤አርሶ አደሩን የመወሰን አቅም ማሳደግ ፤ የሰብል ማምረት እቅድ ምርቱን በሚፈለገው ጊዜና በመረጠው ገበያ እንዲያቀርብ የሰብል የጊዜ ሰሌዳ እንዲያዘጋጅ ማድረግ እና የእያንዳንዱን ሰብል በጀት (ወጪ እና የትርፍ ገቢ) ትንተና ከተደረገ በኋላ አርሶ አደሮች አሳታፊ በሆነ መንገድ ለምርት የሚሆኑ ሰብሎችን ይመርጣሉ። አርሶአደሮች ምን መስራት እንዳለባቸው በራሳቸው መወሰን ይችላሉ፤ስለዚህ አርሶ አደሩ እራሱን ለመለወጥ ውሳኔ እንዲወስን እድል ይሰጣል። የኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ሚና የአርሶአደር እቅድ ዝግጅት ላይ ድጋፍ መስጠት ይሆናል።

**ደረጃ 4:** የአርሶ አደሩን እዉቀትና ክህሎት ማሳደግ

በ4ኛውና የመጨረሻው ደረጃ ፍላጎት ላይ መሰረት ያደረገ በኤክስቴንሽን ባለሙዎች ተግባራዊና ሙያዊ ስልጠና ለአርሶ አደሩ ይሰጣሉ። ብዙ ጊዜ የሚነሳው ጥያቄ ፕሮጀክቱ በቀጥታ አስፈላጊ ቴክኒካል የክህሎት ስልጠና ከመስጠት ይልቅ ረጅም ሂደት ቅድሚያ ማከናወን እንዳስፈለገ ግልጽ አይደለም። ምክንያቱም ከላይ በ2.1.1.(ተመጣጣኝ ያልሆነ መረጃ ያላቸው ግብይቶች) እንደተገለጸው አርሶ አደሮች የገበያ ጥናት ከማድርጋቸው በፊት ማምረት የሚፈልጓቸውን ሰብሎች የሚወሰኑት ባላቸው ውስን እና በቂ ያልሆነ መረጃ ስለሚሆን ውሳኔውም የተሳሳተ ይሆናል። በተጨማሪም የኢትዮ-ሺፐ ፕሮጀክት 4ቱም ደረጃዎች በቅደም ተከተል በማለፍ አርሶአደሮች በገበያ ጥናቱ ምን አይነት መረጃ መሰብሰብ እንዳለባቸው እና የተሰበሰበው መረጃ እንዴት መተንተን እንደሚችሉ ይማራሉ። በተለይ ቀጥሎ በሚዘጋጀው የሰብል መረጣ ዝግጅት ማምረት የሚፈልጓቸውን ሰብሎች ከመወሰናቸው በፊት በገበያ ውስጥ ያሉትን እውነታዎች እንዲያውቁ የሚረዳ ክህሎት ያዳብራሉ፡፡



# ምዕራፍ 2: የ“ኢትዮ-ሼፕ” ፕሮጀክት የትግበራ ሂደት መመሪያ

# 2-1: የዝግጅት ሂደት




## 1. ቅድመ-ዝግጅት 1. የግንዛቤ ማሳደግያ ማነቃቂያ ወርክሾፕ እና የመነሻ ዕቅድ ዝግጅት

እዚህ ጋር ነን

| የዝግጅት ሂደት | ተግባራት |
|---|---|
| **ሂደት- 1** | **የሼፕ ዘዴን ለማስተዋወቅ ወርክሾፕ ማካሄድ** (ለአስፈጻሚ አካላት)፣<br>ስለ ተጠቃሚ በታዎች/ቡድኖች አመራረጥ፣ መግቢያ፣ ፍላጎት/መነሻ ዕቅድ አቀራረብ፣ እና የሼፕ ዘዴን ለማስተዋወቅ የግንዛቤ መርሀ-ግብር ማዘጋጀት ሂደት (ለፈጻሚ አካልት) |
| ሂደት- 2 | ለፕሮጀክቱ ምቹ የሆኑ ወረዳዎች አመራረጥ |
| ሂደት- 3 | የሼፕ ዘዴ የአስልጣኞች ስልጠና ፕሮግራም ማዘጋጀት |
| ሂደት- 4 | የሼፕ ዘዴን ለመተግበር ምቹ የሆኑ አርሶ አደሮች/ የአርሶ አደር ቡድኖች አመራረጥ |
| **አራት (4) ደረጃዎች** | **ዋና ዋና ተግባራት (Activities)** |
| 1. ግቡን እና ዓላማውን ለአርሶ አደርና ለአጋር አካላት ማስተዋወቅ | - የትውውቅ ፕሮግራም ማካሄድ |
| 2. የአርሶአደሮችን ግንዛቤ ማሳደግ | - አሳታፊ መሰረታዊ መረጃ የዳሰሳ ጥናት<br>- የገበያ ጥናት |
| 3. የአርሶአደሮችን ውሳኔ ሰጭነት አቅም ማሳደግ | - የሰብል መምረጥ<br>- የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለየታ ፣ የሰብል አመራረት የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀትና ማለማመድ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የባለድርሻ አካላት መድረክ ማዘጋጀት |
| 4. የአርሶአደሩን እዉቀትና ክህሎት ማሳደግ | - በገበሬ ማሳ ላይ ስልጠና መስጠት<br>- የስርዓተ ፆታ ስልጠና በመስጠት ግንዛቤ ማሳደግ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የልምድ ልውውጥ እና ጉብኝት ማካሄድ<br>- የመስክ ቀን/ የልምድ ልውውጥ ጉብኝት |
| የክትትልና ግምገማ (አሳታፊ የመጨሻ ውጤት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድን ያካትታል) | |

### 1.1. መግብያ

የኢትዮ-ሼፕ ፕሮጀክት ቀዳሚ ተግባር የሼፕ ዘዴን የግንዛቤ መርሀ-ግብር በማዘጋጀት ለወረዳና ዞን አመራሮች እንዲሁም ለወረዳ ሆርቲካልቸር ልማት ቡድን እና ልማት ወኪሎች በተገኙበት የማስተዋወቅ አውደ-ጥናት ነው:: ይህ መድረክ ጃይካ ኢትዮ-ሼፕ ፕሮጀክት ለባለድርሻ አካላት አጠቃላይ የኢትዮ- ሼፕ ፕሮጀክት ታሪካዊ ዳራ፣ ቁልፍ የሼፕ ገበያ-መር የኤክስቴንሽን ዘዴና ከፕሮጀክቱ ትግበራ በኋላ የሚጠበቁ ውጤቶችን በማብራራት የጋራ መግባባት በመፍጠር ሂደት ላይ ወሳኝ ሚና አለዉ ፡፡ በዚህ አውደ-ጥናት ስለ ተጠቃሚ ወረዳዎች/ቡድኖች አመራረጥ እና የፍላጎት/መነሻ ዕቅድ አቀራረብ ሂደት በተመለከተ መግቢያ ይቀርባል።

### 1.2. አላማዎች

- የሼፕ አላማ ከእጩ ዞኖችና ወረዳዎች በሚወከሉ የዞን አመራሮች፣ የወረዳ ሆርቲካልቸር ልማት ቡድን እና የቀበሌ አመራሮች በተሳተፉበት ለማስተዋወቅ፣
- በኢትዮ-ሼፕ ፕሮጀክት የሚታቀፉ ተጠቃሚ ማህበራት እና ቡድኖች ለመምረጥ የሚያገለግሉ መስፈርቶችን ማስተዋወቅ፣
- የፍላጎት/መነሻ ዕቅድ አቀራረብ ሂደት በተመለከተ ለፈጻሚ ወረዳዎች እና ቀበሌዎች ማብራሪያ መስጠት፣
- የፍላጎት/መነሻ ዕቅድ ማቅረቢያ/ ማመልከቻ ቅጽ መሰረት መሙላትና ሰነዱን ለዞን ባለሞያ ማስረከብ።

### 1.3. የአውደ ጥናቱ አቀራረብ

#### 1.3.1. ፈፃሚ አካል

- **አዘጋጅ አካል:-** የፌደራል ባለሙያ እና ክልል ግብርና

- **አስተባባሪ**:- የክልል  የፕሮጀክት አማካሪ

**ተሳታፊዎች**:-

**ክልል**:-ምክትል ቢሮ ሀላፊ(ሰብል ልማትና ሃላፊ)፣ እቅድ ዳይሬክተር፣ ሰብል ልማት ዳይሬክተር.፣ ሆርቲከልቸር፣  ልማት ዳይሬክተር፣ የኤክስቴንሽ ዳይሬክተር፣

**በዞን ደረጃ**:- ግብርና ሃላፊና ምክትል ሃላፊ፣ ሰብል ልማት ክፍል ፣ሆርቲከልቸር እና ኤክስቴንሽን ክፍል፣

**ወረዳ**:- ግብርና ሃላፊና ምክትል ሃላፊ፣ ሰብል ልማት ክፍል ፣ሆርቲከልቸር እና ኤክስቴንሽ ክፍል፣

**የተመረጠው ቀበሌ**:- የቀበሌው ግብርና ጽ/ቤት ኃላፊ /አስተባባሪ፣ የመስኖ ልማት ወኪል።

**የሚወስደው ጊዜ**

- **አንድ (1) ቀን**

## 1.3.2. የስብሰባ ቦታ

በመንግስት መሰብሰቢ አዳራሽ ቢሆን ይመረጣል

**ሰንጠረዥ 2. ተግባር የሼፕ ዘዴ የግንዛቤ መፍጠርያ ፕሮግራም እና የመነሻ ዕቅድ አቀራረብ ስርዓት መግቢያ**

| ሰዓት | አጀንዳ |
|---|---|
| 2:00 - 2:30 | የተሳታፊዎች ምዝገባ |
| 2:30 - 2:40 | የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር |
| 2:40 - 2:50 | የወርክሾፕ/ስልጠናው አላማዎች |
| 2:50 - 3:00 | የተሳታፊዎች የእርስ በርስ ትውውቅ ሰዓት |
| 3:00 - 3:40 | ስለ ኢትዮ-ሼፕ ፕሮጀክት አጠቃላይ መግለጫ<br>• የኢትዮ-ሼፕ ፕሮጀክት ዘዴ ጽንሰ-ሀሳብ፣ የትግበራ ማዕቀፍ (አደረጃጀት፣ የትግበራ ስልት (ተግባርና ሃላፊነት)፣ ወዘት<br>• መግቢያ፥ በፕሮጀክቱ በተደረጉት ስራዎች የተገኘው ልምድ ከሌሎች ወረዳዎች የሚገኙ ውጤቶችና አስተዋጽኦ ያደረጉ ቁልፍ የሼፕ ፕሮጀክት ተግባራት |
| 3:40 - 4:00 | የእያንዳንዱ ባለድርሻ አካል ስራና ሀላፊነት መለየት |
| 4:00 - 4:30 | የሻይ እረፍት |
| 4:30 - 5:00 | ከሌሎች ወረዳዎች የተገኘው ልምድ ይዘረዘራል |
| 5:00 - 5:30 | - መግቢያ፡- ፍላጎት/መነሻ ዕቅድ ዝግጅት ስርአት<br>- የፍላጎት/መነሻ ዕቅድ ማቅረቢያ ቅጽ ይዘት<br>- የፕሮፖዛሉ አላማዎች<br>- የፕሮፖዛሉ ቅጽ እና ጥያቄና መልስ<br>- በፕሮጀክት የሚታቀፉ ማህበራት/ቡድኖች ለመምረጥ የሚያገለግሉ መስፈርቶች ማብራራት |
| 5:30 - 6:00 | ጥያቄና መልስ |
| 6:30 - 7:30 | የምሳ እረፍት |
| 7:30 - 9:30 | - በእያንዳንዱ የወረዳ ቡድን መነሻ ዕቅድ መጻፍ<br>- መነሻ ዕቅድ ማስረከብ (ያለቀለት ከሆነ) |
| 9:00 - 9:30 | የሻይ እረፍት |
| 9:30 -10:00 | ለእያንዳንዱ የቀረበው መነሻ ዕቅድ ማወዳደሪያ ነጥብ መስጠት(በአስተባባሪው) |

## 1.4. የአውደ-ጥናቱ ዝግጅት

- የአውደ ጥናቱ ፕሮግራም ማዘጋጀት (ሰንጠረዥ 2)
- ለፕረዘንቴሽን የሚሆኑ ጽሁፎችና የመነሻ ዕቅድ፡ መጻፍያ ቅጽ ማዘጋጀት (እባክዎን ተያያዥ ሰነድ (ዕዝል 1.1 ይጠቀሙ)

## 1.5. የአውደ ጥናቱ ይዘት አቀራረብ

- የኢትዮ-ሼፕ ፕሮጀክት አጠቃላይ ገጽታና አተገባበር ዘዴን በተመለከተ ገለጻ ማድረግ፣

- የመነሻ ዕቅድ አቀራረብ ሂደት በተመለከተ ለፈጻሚ ወረዳዎች እና ቀበሌዎች ማብራሪያ መስጠት፣
- በፕሮጀክቱ የሚታቀፉትን ቡድኖች ለመምረጥ የሚያገለግሉ መስፈርቶች ገለጻ ማድረግ፣
- በተመረጡት ወረዳዎች በኩል ፕሮፖዛሉን በትክክል መሙላት እንዲችሉ ማብራርያ መስጠት፣
- የመነሻ ዕቅድ/ ፕሮፖዛል ማሰረከብያ የመጨረሻው ቀን ማሳወቅ *(የመነሻ ዕቅድ ማሰረከብያ ቀን የምክክር መድረኩ በተካሄደበት ቀን ከሳምንት በኋላ ባለው ቀን ሊሆን ይችላል)።*

**ለትግበራ የሚረዱ ፍንጮች፡ የትውውቅ ፕሮግራም ማዘጋጀት ለምን?**
የትውውቅ ፕሮግራም ማዘጋጀት ስልት፡- በፕሮጀክቱ ዙርያ ለባለድርሻ አካላት ግልጽ ምስል መስጠትና በፈጻሚ አካላት መካከል የጋራ ግንዛቤ ለመፍጠር ይረዳል። (በባለድርሻ አካላት መካከል ድርሻና ሀላፊነት ክፍፍል ማሳወቅ)

## 1.6. በቀጣይ መሰራት ያለባቸው ተግባራት/ ቀጣይ ተግባራት

- በወረዳ ባለሙያዎች የተዘጋጀውን ለዞን ሆርቲከልቸር ልማት ክፍል ያስረክባሉ።
- ተሳታፊዎች አውደ ጥናቱ በተዘጋጀበት እለት ከሰዓት በኋላ ባለው ጊዜ የመነሻ ዕቅድ ቅጹን መሙላት ይችላሉ። ካልተቻለ ግን በሳምንት ጊዜ ውስጥ ጽፈው እንዲያቀርቡ ማመቻቸት ይቻላል።
- ዞን ሆርቲከልቸር ልማት ቡድን ፕሮፖዛሎቹ ስካን (scan) በማድረግ ሰነዱ ለክልል ሰብል ልማት/ ሆርቲከልቸር ዳይሬክቶሬት መላክ ይችላሉ።
- ዋናው ቅጂ (Original) ፕሮፖዛል በዞንና ወረዳ ይቀራሉ።

## 1.7. ፎቶግራፍ



የፕሮጀክት ግንዛቤ ማሳደግያ ፕሮግራም ለክልል፣ ዞን፣ ወረዳና ቀበሌ ተሳታፊዎች



የወረዳ ግብርና ሃላፊና ባለሙያዎች የመነሻ ዕቅድ/ፕሮፖዛል ቅጽ ሲሞሉ

## 1.8. ናሙና ቅጾች

**ስዕል 5. የመነሻ ዕቅድ ማቅረቢያ ናሙና ቅጽ**

ኢትዮ-ሼፕ ፈጻሚ ወረዳዎች ለመምረጥ የሚቀርብ መነሻ ዕቅድ
የዞን ስም: ______________________________
የወረዳ ስም: ______________________________

***የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች ገበያ ተኮር ሆርቲካልቸር ልማት አጋዥ ፕሮጀክት(ኢትዮ-ሼፕ)***

**ኢትዮ-ሼፕ ፈጻሚ ወረዳዎች ለመምረጥ የሚቀርብ መነሻ ዕቅድ**

ኢትዮ-ሼፕ ፈጻሚ ወረዳዎችን ለመምረጥ የሚቀርብ መነሻ ዕቅድ አራት (4) ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ክፍሎች/ ጉዳዮች ያካትታል፡- ተነሳሽነት፣ አስፈላጊ ሀብት መኖር እና ማንቀሳቀስ መቻል፣ ስነ-ምድራዊ ሁኒታዎች እና ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ናቸው። በፍላጎትዎ መሰረት የወረዳዎትን መረጃ እንዲሰጡ እንጠይቃለን ። ለዚህ ይረዳ ዘንድ ቀጥሎ በተሰጠው ቅጽ መሰረት በሳጥኖቹ ምልክት በማድረግ ወይም በክፍት ቦታ በመጻፍ ትክክለኛው መረጃ በመሙላት ያስረክቡ ።

**አጠቃልይ መረጃ**

የዞን ስም ; ------------------------------
የወረዳ ስም ; ------------------------------
የእጩ ቀበሌ ስም/የመስኖ አውታሩ ስም ; ------------------------------
የወረዳው ቆዳ ስፋት ( ኪሜ $^2$) ; ------------------------------
የንዑስ-አስተዳሮች ብዛት፥-
የቀበሌዎች ብዛት ; ------------------------------

**የሆርቲካልቸር ልማት ባለሙያዎች ብዛት**

በወረዳ ደረጃ ; ------------------------------
በቀበሌ ደረጃ ; ------------------------------

**ተነሳሽነት እና አስፈላጊ ሀብት መኖር**

1 ኢትዮ-ሼፕ ዘዴ በወረዳዎቹ ለመተግበር ፍላጎት አላችሁ? አዎ ☐ የለም ☐

መልስዎ አዎን ከሆነ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች ይቀጥሉ፣ የለም ከሆነ ግን መቀጠል አያስፈልግም

እባክዎትን ባቀዳቸሁት መሰረት ውጤት ለመቀዳጀት (በመቶኛ) በጎ አስተዋጾ እና አደናቃፊ/ተግዳሮቶች አስተዋጾ ያደረጉት ምን እንደሆኑ ይጻፉ።

በጎ አስተዋጾ ያበረከቱ ነገሮች
--------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------
----------------------------------------

አደናቃፊ/ተግዳሮት አስተዋጾ ያላቸው ነገሮች
--------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------

2 የኢትዮ-ሼፕ ፕሮጀክት ፈጻሚ ሆናችሁ ከተመረጣችሁ በወረዳችሁ ምን ያህል ስኬት የምታስመዘግቡ ይመስላችኋል? _____%

# ዝግጅት



## 2. ቅድመ-ዝግጅት 2. በፕሮጀክቱ የሚታቀፉ ወረዳዎች መምረጥ

| የዝግጅት ሂደት | ተግባራት |
|---|---|
| ደረጃ 1 | የሼፐ ዘዴን ማስተዋወቅ<br>የምክክር መድረክ ማዘጋጀት ፣ ስለ መነሻ ዕቅድ አቀራረብ መግበ |
| **ደረጃ 2** | **የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ወረዳዎችን መለየት** |
| ደረጃ 3 | የሼፐ አስልጣኞች ስልጠና የምክክር መድረክ ማዘጋጀት |
| ደረጃ 4 | ተጠቃሚ አርሶአደር ቡድን መምረጥ |

እዚህ ጋር ነን

### 2.1. መግቢያ

በፕሮጀክቱ የሚታቀፉትን ወረዳዎች በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት ለመምረጥ፣ የፍላጎት መጠየቂያ መነሻ ዕቅድ እና እያንዳንዱ መነሻ ዕቅድ በመስክ ጉብኝት ግምገማ ድምር ውጤት ይወሰናል። ይህ አሳታፊ የሆነ የወረዳ አመራረጥ ሂደትን በመጠቀም የእያንዳንዱ ወረዳ በፍላጎት ላይ መሰረት ያደረገ በኢትዮ-ሼፐ የሚከናወኑ ተግባራት መነሻ ዕቅድ ያዘጋጃል። የመነሻ ዕቅድ ገምጋሚ ኮሚቴ ከፌደራልና ዘን የመንግስት ሰራተኞች በተውጣጡ ተወካዮች ከተዋቀረ በኋላ በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት ይገመግማሉ። የግምገማ መስፈርቶችና ሂደቱ ፍትሀዊነትና ግልጽነት የሚያረጋግጥ መሆኑን ግንዛቤ ተወስዷል።

### 2.2. አላማዎች

ተጠቃሚ ወረዳዎች ለመምረጥ በፍላጎት መሰረት የተዘጋጀው መነሻ ዕቅድ እና በተጨባጭ በመስክ ጉብኝት በሚያገኙት መረጃ መሰረት አማካኝነት እያንዳንዱ መነሻ ዕቅድ ገምግሞ በድምር ውጤት መሰረት የተሻለ/ተወዳዳሪ ወረዳዎች ለመምረጥ ነዉ

### 2.3. ተጠቃሚ ወረዳዎች ለመምረጥ የሚዋቀር ኮሚቴ አደረጃጀትና አሰራሮች

#### 2.3.1. ተሳታፊ አካላት

- **አዘጋጅ አካል፥-** የክልል ሆርቲከልቸር (ሰብለ ልማት) ዳይረክቶሬት እና የዞን ሆርቲከልቸር (ሰብል ልማት) ቡዱን በመተባበር፣
- **አስተባባሪ፥-** የዞን ሆርቲከልቸርና ኤክስቴንሽ ቡድን፣
- **የመረጣ አባላት**:- የሚመለከታቸው ከፌደራል፣ ክልል፣ ዞን እና ወርዳ ግብርና የተውጣጡ አባላት።

#### 2.3.2. የሚወስደው ጊዜ

አንድ (1) ቀን

**ሰንጠረዥ 3. የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ወረዳዎች ለመምረጥ የኮሚቴ ስብሰባ ማዘጋጀት (ምሳሌ)**

| ሰዓት | ተግባራት |
|---|---|
| 7:00 - 7:30 | መግቢያና የመክፈቻ ንግግር በዞን ባለሙያ |
| 7:30 - 8:15 | የመነሻ ዕቅድ ስርአቱና መምረጫ መስፈቶቹ መገምገም፤<br>የፕሮፖዛሎችን ነጥብ አሰጣጥ እና የመስክ ቅኝት ነጥብ አሰጣጥ<br>ሰለ ነጥብ አሰጣጥ ስልቶች ማብራርያ ፤ጥያቄና መልስ |
| 8:15 - 8:30 | የግምገማ ውጤቶች ይፋ ማድረግ/ፕረዘንቴሽን |
| 8:30 - 10:00 | ከፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ወረዳዎች ጋር ውይይት |
| 10:00 - 10:30 | የወደፊቱ አቅጣጫ (ዞን ህጋዊ ደብዳቤ ለተመረጠው ፈጻሚ ወረዳ ይጽፋል)<br>የመዝግያ ንግግር |

#### 2.3.3. የስብሰባ ቦታ

በዞን ግብርና ስብሰባ ኣዳራሽ ቢሆን ይመረጣል።

### 2.4. የተጠቃሚ ወረዳዎች መረጣ ከሚቴ ስብሰባ ፕሮግራም ማዘጋጀት

- የወረዳ ባለሙያዎች በወረዳው የተዘጋጁ ፕሮፖዛሎች ለዞን ያስረክባሉ።

- የኮሚቴ ስብሰባ ፕሮግራም ማዘጋጀት (በሰንጠረዥ 3 መሰረት)።
- የማስፈጸሚያ መሰሪያዎች ማዘጋጀት (ነጥብ መስጫ ቅጽ/ሸት) ለተሰብሳቢዎች ማዘጋጀት(ዕዝል1.1.3 ተመልከቱ)።
- ፕሮፖዛሎችን ነጥብ መስጠት እና በመስፈርቶች መሰረት መገምገም
- የመስክ ቅኝት መገምገምያ ቅጽ ማዘጋጀት (ሰንጠረዥ 4 (ዕዝል 1.2.1))።

## 2.5. የተጠቃሚ ወረዳዎች መረጣ ኮሚቴ ስብሰባ አተገባበር

- የክልልና ዞን ሰራተኞች በግምገማ ኮሚቴው በተሰጠ ውጤት መሰረት የተወዳዳሪ ወረዳዎች ፕሮፖዛሎችን ደረጃ ይሰጣሉ።
- በፕሮፖዛሎች ነጥብ መሰረት፣ የመስክ ጉብኝት በማድረግ በተጨባጭ በቦታው ያለውን ሁኔታ (ለአትክልት ሰብል ምቹ መሆኑ) እንዲሁም የአርሶአደሮች (በመስኖ) ሰብል ማምረት ያላቸው ልምድ መቃኘት።

**ለትግበራ ፍን<u>ጮች</u>: የመስክ ቅኝት ማድረግ ለምን አስፈለገ?**

በተጨባጭ በቦታው ያለውን ሁኔታ ከፕሮፖዛሉ ጋር በማመሳከር ትክክለኛ ቦታና ተጠቃሚ ቡድን ለመምረጥ ስህተትና ወገንተኝነት ያስቀራል።

## 2.6. ቀጥሎ መሰራት ያለባቸው ተግባራት

- በፕሮፕዛል ገምጋሚ ኮሚቴው በተሰጠ ውጤትና የመስክ ግኝት ውጤት ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ተጠቃሚ ወረዳዎች ከመረጣ ኮሚቴው ጋር ውይይት ማድረግ፣
- ዞን ህጋዊ (ይፋዊ) ለተመረጠው ወረዳ በደብዳቤ ያሳውቃል፣
- የመዝጊያ ንግግር።

**ሰንጠረዥ 4.** በመስክ ግምገማ በመስኖ ልማት ቦታዎች ውስጥ መሰረታዊ ጉዳዮችን መከተታቸውን የምናረጋግጠበት ነጥቦች (ናሙና)

| ነጥቦች | የወረዳ ስም: ______________________ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ቀበሌ 1 | ቀበሌ 2 | ቀበሌ 3 | ቀበሌ 4 |
| የቀበሌው ስም፥- | | | | |
| የቦታው ስም/ የመስኖ አውታር ስም | | | | |
| በመስኖ የሚለማ መሬተ ስፋት | | | | |
| ከፍታ ከባህር ወለል በላይ | | | | |
| የተጠቃሚዎች ቁጥር (ቤተሰብ)፡<br>ወንዶችና ሴቶች አርሶ አደሮች | | | | |
| የውሀ ተቃሚዎች ማህበር መኖር | | | | |
| ከወረዳ ከተማ ያለው ርቀት | | | | |
| ከዋናው መንገድ ያለው ርቀት | | | | |
| የመስኖውን መሰረተ ልማት አሁናዊ ሁኔታ | | | | |
| ከመስኖ አውታሩ በተለያዩ ወቅቶች ውሃ የመኖር ሁኔታ | | | | |
| በመስኖ የሚመረትባቸው ወቅቶች (ወራት) | | | | |
| አርሶ አደሮች በአትክልት ሰብል ያላቸው ልምድ | | | | |
| በቦታው የሚመረቱ ዋና ዋና አትክልቶች | | | | |
| የግብአት አቅርቦት (አቅራቢዎች) | | | | |
| የዋናው ገበያ (ርቀት ጨምሮ) | | | | |
| የስልጠና ቦታ መኖር (ያሉት አማራጮች) | | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የአርሶ አደሮች ዋና የገቢ ምንጭ | | | | |
| አነስተኛ አርሶ አደሮች በሆርቲካልቸር ሰብሎች ምርት እና ግብይት ላይ ያላቸው ዋና ዋና ችግሮች | | | | |
| ሌሎች መረጃዎች | | | | |

## 2.7. ፎቶግራፎች



የመነሻ ዕቅድ ሰነድ(ፕሮፖዛል) በመረጣ ኮሚቴ ሲገመገም


የመረጣ ኮሚቴ አባላት በመነሻ ዕቅድ መሰረት የመስክ ዳሰሳዊ ቅኝት ሲያደርጉ

## 3. ቅድመ-ዝግጅት 3: የሼፕ የአሰልጣኞች ስልጠና ሒደት

| የዝግጅት ሂደት | ተግባራት |
|---|---|
| ሂደት- 1 | የፕሮጀችት ማስተዋወቅ/ቅስቀሳ የምክክር መድረክ እና የፍላጎት ማቅረብያ |
| ሂደት- 2 | የፕሮጀክቱን ተጠቃሚ ወረዳዎች መረጣ |
| **ሂደት- 3** | **የሼፕ አሰልጣኞች ስልጠና የምክክር መድረክ** |
| ሂደት- 4 | ተጠቃሚ አርሶ አደሮች ማህበራትን መምረጥ |

| አራት (4) ደረጃዎች | ዋና ዋና ተግባራት (Activities) |
|---|---|
| 1. ግቡን እና ዓላማውን ለአርሶ አደርና ለአጋር አካላት ማስተዋወቅ | - **የትውውቅ ፕሮግራም ማካሄድ** |
| 2. የአርሶአደሮችን ግንዛቤ ማሳደግ | - **አሳታፊ መሰረታዊ መረጃ የዳሰሳ ጥናት**<br>- **የገበያ ጥናት** |
| 3. የአርሶአደሮችን ውሳኔ ሰጭነት አቅም ማሳደግ | - **የሰብል መምረጥ**<br>- **(እንደ አስፈላጊነቱ) የባለድርሻ አካላት መድረክ ማዘጋጀት**<br>- የሚያጋጥሙ ችግሮችን ልየታ ፣ የሰብል አመራረት የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀትና ማለማመድ |
| 4. የአርሶአደሩን እዉቀትና ክህሎት ማሳደግ | - በገበሬ ማሳ ላይ ስልጠና መስጠት<br>- የስርዓተ ፆታ ስልጠና በመስጠት ግንዛቤ ማሳደግ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የልምድ ልውውጥ እና ጉብኝት ማካሄድ<br>- የመስክ ቀን/ የልምድ ልውውጥ ጉብኝት |
| የክትትልና ግምገማ (አሳታፊ የመጨሻ ውጤት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድን ያካትታል) | |

እዚህ ጋር ነን

ሸፕ አሰልጣኞች ስልጠና

የሚከተሉትን የኢትዮ-ሸፕ ተግባሮች

### 3.1. መግቢያ

የሼፕ የአሰልጣኞች ስልጠና ለሼፕ ዘዴ ተግባራዊነት ቁልፍ ሚና ስላለው ተሳታፊዎች ዋና ትኩረት የሚሰጣቸው (አካላት ናቸው። ስልጠናው ለልማት ሰራተኞች ትኩረት የሰጠው በሸፕ ዘዴ በመተግበር ውጤቶችን ለማምጣት የሚያስችሉ መሳሪያዎች ናቸው። ከክልል፣ ዞንና ወረዳ የግብርና ጽ/ቤቶቹ ጋር በመተባበር በእነሱ የሚከናወን በመሆኑ አቅማቸው ለመገንበት የሚዘጋጅ መርሃ-ግብር ነው። የወረዳ ሆርቲካልቸር ልማት ቡድን እና የስነ-ጾታ ባለሞያ ለልማት ሰራተኞች ድጋፍ እንደሚያደርጉ ይጠበቃል። የሥርዐተ-ፆታ ግንዛቤን ማሳደጊያ በአሰልጣኞች ስልጠናው ማካተት ያስፈለገበት ምክንያት የኢትዮ-ሸፕ ዘዴ አሳታፊ የተቀናጀ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት በመሆኑ በአርሶ አደሮች ተግባራዊ ቴክኒካዊ ስልጠናዎችና የምክር አገልግሎት ማዕቀፎች ውስጥ ለጾታዊ ጉዳዮች ምላሽ መስጠት ወሳኝ ትኩረት ያሻዋል በሚል እምነት ነው። የሥርዓተ-ፆታን ማካተት ሥራ ካልተደረገ የሸፕ ዘዴ ትግበራ ውጤት ውስን መሆኑ እርግጥ ነው።

### 3.2. የስልጠናው አላማ

- የክልል፣ ዞንና ወረዳ የግብርና ባለሞያዎችና የቀበሌ ልማት ሰራተኞች የሸፕ ዘዴ አላማዎች፣ መርሆዎችና ተግባራት እንዲረዱ ማድረግ፣
- በኢትዮ-ሸፕ ዘዴ መሰረታዊ ሥርዓተ-ፆታ እውቀት በማስጨበጥ፡ ሥርዓተ-ፆታን በማካተት ሥራ ላይ ያሉ የንድፈ ሃሳብ ማዕቀፎችን፣ የሥርዓተ-ፆታ ትንተናና መተግበሪያ መሳሪያዎችን ማስተዋወቅ፣
- በኢትዮ-ሸፕ ዘዴ ትግበራ ሂደት ላይ ከክልል፣ዞንና ወረዳ እስከ ቀበሌ ድረስ ተሳታፊ የሚሆኑትን ባለሙያዎች እንደ አዘጋጅ አካል ተግባራቸውንና ሀላፊነታቸውን እንዲረዱት ማድረግ ።

## 3.3. ለስልጠናው ትግበራ የሚደረግ ቅድመ-ዝግጅት

### 3.3.1. የመድረክ አዘጋጅና ተሳተፊዎች

- **የመድረኩ አዘጋጅ:-** ክልል እና ዞን (የሆርቲከልቸር፣ ከኤክስቴንሽን፣ ስነ-ጾታ ባለሙያ ያካተተ ቡድን)

  **ተሳታፊዎች፥ ፌደራል**:- ሆርቲከልቸር፣ ኤክስቴንሽን፣ ስነ-ጾታ ባለሙያ
- **ዞን**:- ሆርቲከልቸርና ሰብል ልማት ስራ ሂደት ፣ ሆርቲከልቸር ባለሙያ እና ስነ-ጾታ ባለሙያ
- **ወረዳ:-** ሆርቲከልቸርና ሰብል ልማት ስራ ሂደት ፣ ሆርቲከልቸር ባለሙያ እና ስነ-ጾታ ባለሙያ
- **ቀበሌ**: የቀበሌ ግብርና ሃላፊና ሌሎች የግብርና ባለሙያዎች (መስኖ፣ አግሮኖሚስት፣ ወዘተ)

### 3.3.2. የሚወስደው ጊዜ

አራት (4)

### 3.3.3. ስልጠናው የሚሰጥበት ቦታ

የሚዘጋጀው መሰብሰቢያ የተሳታፊዎችን ቁጥር ለማስተናገድና ልምምድ ለማድረግ በቂ ስፋት ያለው መሆን አለበት።

| ሰዓት | 1ኛ ቀን | 2ኛ ቀን | 3ኛ ቀን | 4ኛ ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 2:30 - 3:00 | የተሳታፊዎች ምዝገባ | | | |
| 3:00 - 4:30 | 3:00 የመክፈቻ ንግግር<br>3:10 - 3:30 መግቢያ ንግግር ለተሳታፊዎች<br>**3:30 - አጠቃላይ መግብያ**: የኢትዮ-ሼፕ ፕሮጀችት ዘዴ (ጽንሰ-ሀሳብ፣ 4ቱ ደረጃዎች፣ የትግበራ አካሄድ፣ ወዘተ.) | **መሰረታዊ የሥርዓት-ፆታ ጉዳዮች ትንተና (ትምህርታዊ ገለጻ)** | **ትምህርታዊ ገለጻ:-** የሸፕ ዘዴ ማስተዋወቅ፣ የትኩረት ቡድን መረጣ፣ የመነሻ ዳሰሳ ጥናት (የሰብሎች አመራረና ገቢ ትንተና መረጃ (ሆሰአ እና ድምአቴ) እና ጂ/G24 ቅጾች) | **ትምህርታዊ ገለጻ:-** ገበያ-ተኮር ሰብል መረጣ (45 ደቂቃ)<br>የሰብል መረጣ ልምምድ (45 ደቂቃ) |
| 4:30 - 5:00 | የሻይ እረፍት | | | |
| 5:00 - 6:30 | የሥርዓተ-ፆታ ስልጠና:- ሥርዓተ-ፆታን በግብርና ዘርፍ ማካተት ለምን አስፈለገ? | የቡድን ልምምድ: (45 ደቂቃ)<br>ፕ በቡድን ልምምድ ውጤት መሰረት፣ የክለሳ ጊዜ (45 ደቂቃ) | የቡድን ልምምድ: መነሻ ዳሰሳ ጥናት ቅጽ (45 ደቂቃ)<br>በቡድን ልምምድ ውጤት መሰረት የክለሳ ጊዜ (45 ደቂቃ) | ን ሰብል መረጣ ክለሳ (45 ደቂቃ)<br>ትምህርታዊ ገለጻ:- በገበያ ትስስር መድረክ ላይ ትግበራ ኡደት፣ ስራና ሀላፊነት ማብራሪያ |
| 6:30 - 7:30 | የምሳ ዕረፍት | | | |
| 7:30 - 9:00 | ስርዓተ-ፆታን በሸፕ (የቡድን ስራ) | ልምምድ፡ መሰረታዊ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና መሳሪያ (tool -2 (45 ደቂቃ)<br>የክለሳ ክፍለ ጊዜ (45 ደቂቃ)) | **የገበያ ጥናትን በተመለከተ ትምህርታዊ ገለጻ)** (45 ደቂቃ)<br>የቡድን ልምምድ ተግባር (45 ደቂቃ) | የሥርዐተ-ፆታ ድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት 9 |
| 9:00 - 9:30 | የሻይ እረፍት | | | |
| 9:30 - 10:45 | እና የቡድን ውይይት | የሥርዓተ-ፆታ ትንተና መሳሪያ/ቱል፡3. (40 ደቂቃ)<br>የክለሳ ክፍለ ጊዜ (40 ደቂቃ) | የክለሳ ክፍለ ጊዜ በገበያ ጥናት ልምምድ ተግባር መሰረት (45 ደቂቃ)<br>ጥያቄና መልስ (15 ደቂቃ) | ሥርዐተ-ፆታ ድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት ጥያቄና መልስ |
| 10:45 - 11:00 | የዕለቱ ማጠቃለያ | የዕለቱ ማጠቃለያ | የዕለቱ ማጠቃለያ | 16:00 የስልጠና መዝጊያ |

## 3.4. ስልጠናው እንዴት ማዘጋጀት እደሚቻል

- ከሚመለከታቸው የክልል፣ ዘን እና ወረዳ ባለሙያዎች በመመካከር የስልጠናው ቀንና ቦታ መወሰን፡
- የስልጠናው መርሃ-ግበር ማዘጋጀት (ናሙና ፕሮግራም ተመልከቱ)፣
- ለስልጠናው የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት (ዝርዝር ለማየት ዕዝል1.3)፣
- ለስልጠናው የሚያስፈልጉ ጽሁፋዊ ይዘቶች ማዛጋጀችት (ሥርዓተ-ፆታን በማካተት).

## 3.5. ስልጠናው እንዴት መተግበር እደሚቻል

➢ የስልጠናው ይዘት ለክልል፣ ዘን፣ ወረዳ ሆርቲካልቸር ልማት ባለሙያዎች እና ልማት ሰራተኞች ገለጻ ማድረግ፡ ስለዚህ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናሉ።

- የኢትዮ-ሼፕ ፕሮጀችት ዘዴ ገጽታ ገለጻ
- የእያንዳንዱ ተግባርና ሀላፊነት ማብራራት
- የአርሶ አደሮች ቡድን መምረጫ መስፈርት እና የመረጣ ሂደት ማብራራት
- ለእያንዳንዱ ክፍለ-ጊዜ የስልጠና ይዘት በ"ኢትዮ-ሼፕ ፕሮጀክት ዘዴ" ማእቀፍ ማዘጋጀት

**የትግበራ ፍንጭ: - የአሰልጣኞች ስልጠናው ማከናወን ለምን?**
የኢትዮ-ሼፕ አስልጣኞች ስልጠና ፣ የክልል፣ ዘንና ወረዳ የግብርና ባለሙያዎች ስለ ሼፕ ዘዴ በቂ እውቀትና ክህሎት ለማስጨበጥ እንዲሁም ስነ-ጾታ ስልጠና ማዘጋጀት እንዲችሉ ስልጠናው ወሳኝ ሚና አለው ።የኢትዮ-ሼፕ የአስልጣኞች ስልጠና ገበያ ተኮር ግብርናን ለመተግበር የሽፕ ዘዴን (አምርቶ ከመሸጥ ወደ ለገበያ ማምረት አስተሳሰብ) ለመቀየር ይረዳል።

## 3.6. በቀጣይ መሰራት ያለባቸው ተግባራት

ቀጣዩ ደረጃ ይመልከቱ: (ዝግጅት-ደረጃ 4) ተጠቃሚ አርሶ አደሮች ማህበራትን መምረጥ

## 3.7. ፎቶግራፍ



የወረዳና ቀበሌ ባለሞያዎች ተሳታፊዎች በሽፕ ዘዴ የተዘጋጀ ስልጠና ላይ ትምህርታዊ ገለጻ ሲከታተሉ ይታያል

## 3.8. ናሙና ቅጾች

የመሰረታዊ መረጃ ዳሰሳ ጥናት፡- የሰብሎች አመራረትና ገቢ ትንተና መረጃ መሰብሰቢያ ቅጽ

**የሰብል ምርት እና ገቢ ትንተና (CP&IA)መረጃ ቅጽ (rev.1-2)**

ዞን/ወረዳ ስም ____________ የቀበሌ ስም ____________ ቀን -----------------------

የአርሶ አደር ስም: ____________ ወንድ/ሴት: ____________ የአርሶ አደር ቡድን ስም ------------------

ስልክ ቁጥር ____________

| የሰብል ስም (ዝርያ) | የማሳ ስፋት መለኪያ (ሄክታር፣ ጥማድ) | የምርት መጠን (በባህላዊ ልኬት) | የሽያጭ መጠን (በባህላዊ ልኬት) | አማካይ ዋጋ (ብር/ልኬት) | ጠቅላላ ገቢ (ብር) | ጠቅላላ የማምረቻ ወጭ (ብር) | የተጣራ ገቢ (ብር) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በመስኖ የተዘራ 1 | | 1( ) = ( )ኪግ | | | | ዳፕ /ኤንፒኤስ<br>ዩሪያ<br>ዘር<br>ኬሚካል<br>ጉልበት<br>ሌሎች | |
| በመስኖ የተዘራ 2 | | 1( ) = ( )ኪግ | | | | ዳፕ /ኤንፒኤስ<br>ዩሪያ<br>ዘር<br>ኬሚካል<br>ጉልበት<br>ሌሎች | |
| በዝናብ የተዘራ 1 | | 1( ) = ( )ኪግ | | | | ዳፕ /ኤንፒኤስ<br>ዩሪያ<br>ዘር<br>ኬሚካል<br>ጉልበት<br>ሌሎች | |

የሰብሎች አመራረትና የድህረ ምርት አያያዝ ዘዴ ጠቅላላ እዉቀት (አሰአ እና የድምአቴ24

**የአትክልት ሰብሎች አመራረት እና የድህረ ምርት አየያዝ ዘዴ በተመለከተ ጠቅላላ እውቀት (አሆሰአ እና የድምአቴ ) 24**

ክልል: ____________ ዞን ____________

የወረዳ ስም: ____________

የቡድኑ ስም/ቀበሌ: ____________

የአርሶ አደሩ ስም: ____________ ወ / ሴ: ____________ ቀን: / / ስልክ ቁጥር.: ____________

| ከቅደም ምርት እስከ ድህረ ምርት ተግባራት | | ጥያቄዎች | ለሆርቲከልቸር ሰብሎች አመራረት እንዲለመዱና ተግባራዊ እንዲደረጉ የተለዩ ዘዴዎች | አዎ | የለም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቅድመ ምርት ዝግጅት | ጥ1 | የሚያመርቱትን ሰብል የገበያ ፍላጎት ለማወቅና ለማስተካከል የገበያ ጥናት በማካሄድ መረጃ ይሰበስባሉ ? | | |
| | | ጥ2 | ከገበያ ቅኝት ወይም ጥናት በሚያገኙት መረጃ መሰረት የሚያመርቱትን ሰብል እቅድና የማምረቻ የጊዜ ሰሌዳ ያዘጋጃሉ ? | | |
| | | ጥ3 | ከማሳዎ ካገኙት ምርት፤በማሳዉ ላይ ከሚበቅሉ የአረም አይነቶችና የአፈሩ ሁኔታ በመቃኘት ወይም በማየት የመሬትዎን አፈር ለምነት ይገምታሉ? | | |
| | | ጥ4 | በማሳዎ ላይ ለሚተከሉ ሰብሎች የሚያስፈልጉ ትክክለኛ ንጥረ ነገሮች (ናይትሮጅን፤ፎስፈረስና ፖታሲየም) እንዲያገኙና የአፈር ለምነት ለመጠበቅ በትክክልና በምክረ - ሃሳቡ መሰረ ት የተዘጋጀ ከምፖስት ይጠቀማሉ? | | |
| | | ጥ5 | ጥራቱን የጠበቀ ዘር የሚጠቀሙ ከሆነ ከሚከተሉት የዘር ጥራት መመዘኛ መስፈርቶች ዉስጥ እርስዎ በምክረ ሃሳቡ መሰረት ተግባራዊ የሚያደርጉት የትኛዉን ነዉ? በሽታን የሚቋቋሙ? ከፍተኛ ምርት የሚሰጡ? ቀድመዉ የሚደርሱ? ጥሩ ጣዕም ያላቸዉን? በገበያ ተፈላጊ የሆኑትን ? ለረጅም ጊዜ ሳይበላሹ በመጋዘን መቆየት የሚችሉትን? (ከስሩ በማስመር ምልክት ያድርጉ) | | |
| 2 | ማሳ ዝግጅት | ጥ6 | በሰብልዎ ላይ የተባይና በሽታ ክስተትን ለመቀነስ ወይም ለመከላከል አስቀድመዉ በማሳ ዝግጅት ወቅት ምን ምን ተግባራትን ያከናዉናሉ ? አፈሩን በሙቀት ማከም? በወቅቱ ማረስ? በጥልቀት ማረስ? ከማሳ ላይ በሽታና ተባይ ክስተት ሊያመጡ የሚችሉ ቃርሚያዎችን ማስወገድ? የሰብል ፈረቃ መጠቀም ? (ከስሩ በማስመር ምልክት ያድርጉ) | | |
| | | ጥ7 | የአፈርን ለምነት ለማሻሻል ዘር ከመዝራትዎ ቢያንስ አንድ ወር አስቀድመው ጠቃሚ የሰብል ቅሪቶችን ከአፈር ጋር ይቀላቅላሉ/ይጨምራሉ? | | |
| | | ጥ8 | ከዘር በፊት ቢያንስ ሁለት ሳምንትና ከዚያ በፊት አስቀድመው በማሳዎ ላይ የተፈጥሮ ማዳበሪያ (ፍግ፡ኮምፖስት ወዘተ) በመበተን ከአፈር ጋር መቀላቀል ተግባራዊ ያደርጋሉ ? | | |

የገበያ ዳሰሳ ጥናት - ቅጽ

**የገበያ መረጃ መሰብሰብያ መጠይቅ**

ቀን፤ _____/________/______

የዞኑ ስም: ____________ ክልል ____________

<u>የገበያ መረጃ የሰበሰበው ስም (የአርሶ አደሮች ስም ዝርዝር)</u> ወረዳ ____________

| የነጋዴው ስምና አድራሻ | ተፈላጊ ምርት መጠንና አይነት | አቅርቦት መጠንና ተፈላጊው ጥራትና መስፈርቶች | ከፍተኛ ገበዪአ ፍላጎት ያለበት (ወራት) | የምርትቱ በአንድ ጊዜ የሚቀርበው መጠንና ድግግሞሽ (እለታዊ፣ ሳንታዊ፣ ወዘተ ) | የተመረተ በት ቦታ | የአንዱ ዋጋ (ብር/ኪግ) | የከፍያ መንገድ | የአከፋፈል ሁኔታ | የግብይት ተግዳሮቶ ች | ነጋዴው ከቡዱኑ ለመግዛት ያለው ፍላጎት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |

ሰብል መምረጫ ቅጽ

**ገበያ ተኮር የሆኑ ሰብሎች መምረጫ ቅጽ**

**ቀን፤** _____/________/______

**የዞኑ ስም:** ____________ **ክልል** ____________

**የአርሶ አደሮች ቡዱን ስም፦** ____________ **ወረዳ** ____________

| የሰብል ስም/ዝርያ | የአካባው ነዋሪዎች ይጠቀሙታል ወይስ አይጠቀሙትም | ሰብሉን የማምረት ልምድ | የአተካከል ዘዴ/ ለመድረስ የሚያስፈልገው ጊዜ | ሰብሉን ለማምረት ዋና ዋና ተግዳሮቶች | በአማካይ ከ1ሄክታር ለገበያ ሊቀርብ የሚችል ምርት መጠን ( ኪግ) | የአንዱ መለኪያ ዋጋ (ብር/ኪግ) | ጠቅላላ ሽያጭ ገቢ በ1ሄክታር (ብር) | ጠቅላላ ማምረቻ ወጭ በ1ሄክታር (ብር) | የተጣራ ዓመታዊ ገቢ በ1ሄክ (ብር) | ዋና መሸጫ ገበያ (ዎች) | ገዢ የሚጠይቃቸው መስፈርቶች (ጥራት፣ ብዛት ----) | ጠቃሚ ማስታወሻ | የሰብሉ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | |

# 4. ቅድመ-ዝግጅት 4: ተጠቃሚ አርሶ አደሮችና ማህበራትን መምረጥ

| ቅድመ- ዝግጅት | ተግባራት |
|---|---|
| ደረጃ 1 | የሼፕ ዘዴን የማስተዋወቅ (Sensitization) የምክክር መድረክ ማዘጋጀት፣ ስለ መነሻ ዕቅድ አጻጻፍ መግብያ ገለጻ |
| ደረጃ 2 | የፕሮጀክቱን ተጠቃሚ ወረዳዎች መረጣ |
| ደረጃ 3 | የሼፕ አሰልጣኞች ስልጠና የምክክር መድረክ ማዘጋጀት |
| **ደረጃ 4** | **ተጠቃሚ አርሶአደሮች ቡድን መምረጥ** |

እዚህ ጋር ነን

| አራት (4) ደረጃዎች | ዋና ዋና ተግባራት (Activities) |
|---|---|
| **1.** ግቡን እና ዓላማውን ለአርሶ አደርና ለአጋር አካላት ማስተዋወቅ | - የትውውቅ ፕሮግራም ማካሄድ |
| 2. የአርሶአደሮችን ግንዛቤ ማሳደግ | - አሳታፊ መሰረታዊ መረጃ የዳሰሳ ጥናት<br>- የገበያ ጥናት |
| 3. የአርሶአደሮችን ውሳኔ ሰጭነት አቅም ማሳደግ | - የሰብል መምረጥ<br>- የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለየታ ፣ የሰብል አመራረት የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀትና ማለማመድ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የባለድርሻ አካላት መድረክ ማዘጋጀት |
| 4. የአርሶአደሩን እዉቀትና ክህሎት ማሳደግ | - በገበሬ ማሳ ላይ ስልጠና መስጠት<br>- የስርዓተ ፆታ ስልጠና በመስጠት ግንዛቤ ማሳደግ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የልምድ ልውውጥ እና ጉብኝት ማካሄድ<br>- የመስክ ቀን/ የልምድ ልውውጥ ጉብኝት |
| የክትትልና ግምገማ (አሳታፊ የመጨሻ ውጤት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድን ያካትታል) | |

## 4.1. መግቢያ

የሼፕ ዘዴ ትኩረቱ አነስተኛ የሆርቲካልቸር አምራች አርሶአደሮች ገበያ ተኮር ሰብል ለመተግበር ማነሳሳትና ማብቃት ነው። በርካታ የአርሶአደር ቡድኖች በመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት ስር ይገኛሉ። ቢሆንም በፕሮጀክቱ የሚታቀፉ የአርሶአደር ቡድኖች ሲመረጡ ከኢትዮ-ሼፕ ዘዴ መጠቀም የሚችሉ መሆናቸው ማረጋገጥ ሊሰመርበት ይገባል። ተጠቃሚ የአርሶአደር ቡድኖች የሚመረጡት በሚቋቋመው የመረጣ ኮሚቴ የሚዘጋጅ መስፈርቶች መሰረት በማድረግ ነው። መስፈርቶቹ እንደ ቀበሌው ሁኔታ በዞንና በወረዳ ፈጻሚ ቡድን አባላት የሚስተካከል ይሆናል። ይህ አሰራር ፍትሃዊና ተቀባይነት ያለው የተሳታፊ ቡድን ለየታ ማረጋገጥ ነው።

## 4.2. ዓላማ

ከታች (ሰንጠረዥ) በተዘረዘሩ መስፈርቶች መሰረት በፕሮጀክቱ የሚታቀፉ የአርሶ አደር ቡድኖች መለየት።

## 4.3. መስፈርቶች ለአርሶ አደር ቡድኖች መረጣ

ቀጥሎ የተሰጠው ሰንጠረዥ በፕሮጀክቱ ትግበራ ምቹ የሆኑ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት እና የአርሶ አደር ቡድኖች ለመመልመል የተዘረዘሩ መስፈርቶች ያመለክታል።

**ሰንጠረዥ 5.** በፕሮጀክቱ ስለሚታቀፉ የአርሶ አደር ቡድኖች መምረጫ መስፈርቶች

| # | መስፈርት | መስፈርቶች |
|---|---|---|
| 1 | **የቡድን ብዛት** | እያንዳንዱ የመስኖ አውታር **አንድ ተሳታፊ የአርሶአደር ቡድን** ይመለምላል ። እጩዎች ሲመረጡ የኢትዮ-ሼፕ ዘዴ እንዲተገብሩ በመሆኑ እጨዎችን በመመልመል ሂደት የተቀመጠውን መስፈርት መጠቀምን ከግምት ውስጥ ያስገቡ። |
| 2 | **የቡድን ሁኔታ** | የተሳታፊ አርሶአደር ቡድኖችን **ከመደበኛ እና ኢ-መደበኛ** ቡድኖች በማሰባጠር **መምረጥ** |

| # | መስፈርት | መስፈርቶች |
|---|---|---|
| | | የኢትዮ-ሼፕ ሲባል **አዲስ ቡድን መቋቋም የለበትም፣** ይልቅ **በስራ ካሉ** ቡድኖች መሆን አለበት |
| 3 | **አባልነት** | የቡድን አባላት ቁጥር **በ30 እና 40** መካከል መሆን አለበት |
| | | ተጠቃሚ ቡድኖችን በማዋቀር ሂደት የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበር ሊቀመንበር ወይም ተመሳሳይ ተገቢ ሰው ለምሳሌ በመመስረት ካሉ በራሳቸው ማሳ (ተከራይተው የሚያርሱትን አይጨምርም) የሆርቲካልቸር ሰብል አምራች አርሶ አደሮችን ማካተት ይጠበቃል። |
| 4 | **ዕድሜ** | ከትምህርት ገበታ ውጭ ያሉ ወጣቶችና ጎልማሶች (ከተቻለ የሚበዙት አባላት ወጣቶች ቢሆኑ ይመረጣል) |
| 5 | **ትምህርት** | ከቡድን አመራሮች መካከል የተወሰኑት ትምህርት ያላቸው ወይም በከፊል መሃይምነት ያጠፉ ሊሆኑ ይገባል። ምክንያቱም በስልጠናው ጊዜ ማንበብና መጻፍ መቻል ያስፈልጋል። በተጨማሪም የስልጠና ጽሁፎች ወደ አከባቢው ቋንቋ ይተረጉማሉ (አስፈላጊ ሲሆን) |
| 6 | **ስራ** | እያንዳንዱ የቡድን አባል **የሆርቲካልቸር ሰብል አምራች** መሆን አለበት |
| 7 | **የቡድን መሪዎች ተግባር** | **ዋና የገቢ** ምንጫቸው **ከሆርቲካልቸር ሰበል** ምርት የሆኑ አባላት **ይመለምላሉ።** |
| | | አማራጭ የገቢ ምንጫቸው **በከሆርቲካልቸር ል**ማት **አሉታዊ ተጽእኖ የሌለው** የሆኑ አባላት ይመለምላሉ። |
| | | የገበያ መስመራቸው አሁን ካሉት ነጋዴዎች/ደላሎች ይልቅ በሌላ አማራጭ ገበያ ፍልጎት ያላቸው አባላት ይመለምላሉ (አሁን ባለው የገበያ መስመሮች የረኩ (ደስተኛ) ከሆኑ መመረጥ የለባቸውም) |
| | | በጋራ(በህብረት) ግብአት መግዛት/ምርት መሸጥ የጀመሩ ወይም ፍላጎት ያላቸው **ቡድኖች ይመርጣሉ** |
| 8 | **የቡድን ባህሪ** | **ለ**ኤክስቴንሽን አገልግሎት "**ጤናማና አዎንታዊ አመለካከት**" ያላቸው ቡድኖች ይመርጣሉ፤ ምክንያቱም እርስበርስ በደንብ ለመግባባት ያስችላቸዋል ። |
| | | "**ከፍተኛ ተነሳሽነት**" ያላቸው ቡድኖች ይመረጣሉ። ምክንያቱም አዲስ ሀሳብና ቴክኖሎጅዎች ለመማር ዝግጁ ናቸው። |
| | | **በራሳቸው ሀብት ለመስራት ችሎታውና ፍላጎቱ** ያላቸው ቡድኖች **ይመረጣሉ ።** የውጭ ነጻ ድጎማ ወይም ግብአት የሚጠብቁ ቡድኖችን ማስቀረት። |
| 9 | **ተጠቃሚ ቦታዎች ተደራሽነት** | ተጠቃሚ ቦታዎችን በመምረጥ ሂደት ላይ ተመሳሳይ ስርጭት (ሽፋን) እድል በመስጠት ከተለያዩ የሆርቲካልቸር ሰብል አምራች አርሶ አደሮችን በማካተት መምረጥ ይመከራል። **ከአንድ ቦታ** ብቻ ከመምረጥ መታቀብ ። |
| | | **የጸጥታ ስጋት** ካለባቸው ቦታዎች ከመምረጥ መታቀብ። በፕሮሮጀችቱ ተግባራዊነት አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል/። |
| | | ተጠቃሚ የመስኖ አውታሮች የሚመረጡት ፄሚ ውሀ/ አመት ሙሉ /ፍሰት ካላቸው ቦታዎች መካካል ነው። |
| 10 | **የልማት ሰራተኞች (DAs) መኖር** | ተነሳሽነትና ጠንካራ የስራ ባህል ያላቸው የልማት ሰራተኞች ከሚገኝበት ቦታ ቡድኖች **መምረጥ።** (የመስኖ ሙያ ያላት/ያለው ቢሆን ይመረጣል)፣ አለያም አንዱን መመደብ ወይም ክፍት ቦታ ካለ መቅጠር የሚቻል ከሆነ ። |

## 4.4. የአርሶ አደር ተወካዮች እንዴት መምረጥ እደሚቻል

- የወረዳ ሆርቲካልቸር ባለሙያዎች እና የልማት ሰራተኞች በመተባበር በአርሶአደር ቡድን እጩዎች (የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት) መርጠው ለዞን ገምጋሚ ኮሚቴ ቡድን ያስረክባሉ (ለዝርዝሩ ሰንጠረዥ 5 ይመልከቱ)
- የዞን መረጣ ኮሚቴ ከወረዳ ቡድን ጋር በመቀናጀት በልማት ሰራተኞች አመቻችነት እጩ አርሶ አደር ቡድኖችን (የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራትን) እና መስኖ አውታሮችን ለመቃኘት የመስክ ጉብኝት ያደርጋሉ።
- በቅድሚያ ግን የወረዳ ባለሙያዎች እና የልማት ሰራተኞች ከታቀፉ ቦታዎች መካከል ከ40 በላይ አባላት ያላቸው የመስኖ ውሃ

ተጠቃሚ ማህበራት ይለያሉ። በነዚህ ማህበራት ቅስቀሳ በማድረግ በፍቃደኝነት በፕሮጀክቱ የሚታቀፍ ቡድን ተወካዮች እንዲያዘጋጁ ይደርጋል።

- ከመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት (መ/ው/ተ/ማ) አባላት ጋር በመወያየት ሞዴል አርሶአደሮችን ይመርጣሉ። ይህ ቡድን የተለያዩ የኢትዮ-ሼፕ ተግባራትን በተግባር ግብረ-መልስ ለመ/ው/ተ/ማ ማስተላለፍ ሀላፊነት ይኖረዋል።

**የትግበራ ፍንጭ፡-የተጠቃሚ አርሶ አደር ቡድን መምረጫ መስፈርት ለምን ያስፈልጋል?**

መምረጫ መስፈርት መጠቀም አዲስ አሰራር ለመቀበል (ለመማር) ፍላጎት ያላቸውን፣ ከፍተኛ ተነሳሽነትና ቁርጠኛ የሆኑ አርሶ አደሮችን ለመለየት ያስችላል። በዚህ መመሪያ የተጠቀሱትን መስፈርቶች መሟላት ደግም ለኢትዮ-ሼፕ ዘዴ ስኬታማ ትግበራ ወሳኝ ሚና እንዳለው ታሳቢ ተደርጓል።

# 2-2: የአርሶ አደሮች አቅም የማሳደግ ስልጠና



## 1. ደረጃ 1: የአርሶ አደር ተወካዮች የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም ማዘጋጀት

ደረጃ በደረጃ የሚሰሩ ክንውኖች እንደሚከተለው ይገለፃሉ

| ቅድመ- ዝግጅት | ተግባራት |
|---|---|
| ደረጃ 1 | የሼፕ ዘዴን የማስተዋወቅ (Sensitization) የምክክር መድረክ ማዘጋጀት፣ ስለ መነሻ ዕቅድ አጻጻፍ መግብያ ገለጻ |
| ደረጃ 2 | የፕሮጀክቱን ተጠቃሚ ወረዳዎች መረጣ |
| ደረጃ 3 | የሼፕ አሰልጣኞች ስልጠና የምክክር መድረክ ማዘጋጀት |
| ደረጃ 4 | ተጠቃሚ አርሶአደሮች ቡድን መምረጥ |

| አራት (4) ደረጃዎች | ዋና ዋና ተግባራት (Activities) |
|---|---|
| **1. ግቡን እና ዓላማውን ለአርሶ አደርና ለአጋር አካላት ማስተዋወቅ** | **- የትውውቅ ፕሮግራም ማካሄድ** |
| 2. የአርሶአደሮችን ግንዛቤ ማሳደግ | - አሳታፊ መሰረታዊ መረጃ የዳሰሳ ጥናት<br>- የገበያ ጥናት |
| 3. የአርሶአደሮችን ውሳኔ ሰጭነት አቅም ማሳደግ | - የሰብል መምረጥ<br>- የሚያጋጥሙ ችግሮችን ልየታ ፣ የሰብል አመራረት የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀትና ማለማመድ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የባለድርሻ አካላት መድረክ ማዘጋጀት |
| 4. የአርሶአደሩን እዉቀትና ክህሎት ማሳደግ | - በገበሬ ማሳ ላይ ስልጠና መስጠት<br>- የስርዓተ ፆታ ስልጠና በመስጠት ግንዛቤ ማሳደግ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የልምድ ልውውጥ እና ጉብኝት ማካሄድ<br>- የመስክ ቀን/ የልምድ ልውውጥ ጉብኝት |
| የክትትልና ግምገማ (አሳታፊ የመጨሻ ውጤት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድን ያካትታል) | |

አዚህ ጋር ነን

### 1.1. መግቢያ

ይህ መድረክ የ "ኢትዮ-ሼፕ አቀራረብ" ለአርሶ አደሮች ማስተዋወቅና ግልጽ ግንዛቤ በመፍጠር ፕሮጀክቱ ስለሚሰጠው አገልግሎት ግንዛቤን ያስጨብጣል። በፕሮጀክቱ ቀጣይ ሂደቶች የጋራ ግንዛቤ ለመያዝ የትውውቅ ፕሮግራሙ ማዘጋጀት አስፈላጊ ተግባር ነው።

### 1.2. ዓላማ

- ስለ "ኢትዮ-ሼፕ አቀራረብ" እና ዋና ዋና ተግባራት ከአርሶ አደሩ ጋር የትውውቅ ፕሮግራም ማካሄድ።
- በፕሮጀክቱ ከታቀፉት የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት (የመ. ው.ተ.ማ.) (የማህበሩ አባላት ቁጥር ከ35 በላይ ከሆነ) ወካይ አርሶ አደሮች መምረጥ፣
- ስለ ኢትዮ-ሼፕ አቀራረብ ጽንሰ ሃሳባዊ ማዕቀፎች ማስተዋወቅና ፍላጎትን መፍጠር።

  ኢትዮ-ሼፕ አቀራረብ የአርሶ አደሮችን አመለካከት ከ **"ማምረት እና መሸጥ"** ወደ **"ለመሸጥ ማምረት"** ለመለወጥ የሚያስችሉ የአቅም ግንባታ አካሄድ ይከተላል። ስለሆነም ለተጠቃሚ አርሶ አደሮች ማንኛውም የግብዓት (የማዳበርያ፣የዘር፤የኬሚካል፤ የመስኖ አዉታር/ካናል ግንባታ) የገንዘብ ድጋፍ፣ አያደርግም።

### 1.3. የፕሮግራሙ ዝግጅት ሂደቶች

#### 1.3.1. ተሳታፊዎች

- አዘጋጅ/ፈጻሚ አካል፥- የወረዳ ባለሙያ እና የቀበሌ ባለሙያዎች
- አርሶ አደር ተሳታፊዎች:- የተጠቃሚ አርሶ አደሮች ወካይ አባላት (ከመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት የተመረጡ)

### 1.3.2. የሚወስደው ጊዜ

- ግማሽ ቀን

**ሰንጠረዥ 6.** ለተጠቃሚ አርሶ አደሮች የግንዛቤ ማሳደጊያ ቅስቀሳ መርሃ-ግብር

| ሰዓት | ተግባራት |
|---|---|
| 2:30 - 3:00 | የተሳታፊዎች ምዝገባ፣<br>የመክፈቻ ንግግር |
| 3:00 - 3:20 | ስለ ኢትዮ-ሼፕ ፕሮጀክት አቀራረብ የተመለከተ አጠር ያለ ገለጻ ማድረግ (ማድረግ የምንችለው እና ማድረግ የማንችለው)<br>የተወካይ አርሶ አደሮችን ተግባራት ገለጻ ማድረግ፣ |
| 3:20 - 3:40 | ፕሮጀክቱ ከበፊቶቹ ስራው ያሳካቸው ግቦች ማስተዋወቅ (ለተሳታፊ አርሶ አደሮች ምን ኣይነት ለውጥ ማሳካት እንደሚችሉና ይህንን ግብ እውን ለማድረግ ከፕሮጀክቱ ምን እንደሚጠብቁ ማስገንዘብ)። |
| 3:40 - 4:00 | ስለ ኢትዮ-ሼፕ አቀራረብ ዋና ዋና ክፍሎች በትግበራ ሂደት ቅደም ተከተል በአጭሩ መዘርዘር |
| 4:00 - 4:30 | የተወካይ አርሶ አደሮችን ተግባራት ገለጻ ማድረግ፣<br>ተወካይ አርሶ አደሮች መምረጥ |
| 4:30 - 5:00 | የጥያቄና መልስ ጊዜ |
| 5:00 - 5:30 | የወደፊት አቅጣጫ<br>የመዝግያ ንግግር |

### 1.3.3. የስብሰባ ቦታ

በተጠቃሚዎች አቅራቢያ የሚገኝ አማካይ ቦታ መሆን አለበት፡- ዛፍ ጥላ ስር ወይም በገበሬዎች ማሰልጠኛ (FTC)

## 1.4. ናሙና የበጀት እቅድ መመዝገቢያ ሠንጠረዥ/ ቅጽ

| የክፍያ ዓይነት | የቀን ብዛት | የሰው ብዛት |
|---|---|---|
| አበል (ለወረዳ ባለሙያ) | 1 | 2 |
| አበል (ለዞን ባለሙያ) | 1 | 1 |
| አበል (ለዞን ባለሙያ ሹፌር) (እንደአስፈላጊነቱ) | 1 | 1 |
| የትራንስፖርት/የነዳጅ ወጭ (ለወረዳ ባለሞያ) | 2 | የሚወሰን |
| የነዳጅ ወጭ ለዞን ባለሞያ | 1 | 1 |
| የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች (ተገላጭ ቻርት• እስክርቢቶ) | 1 | 1 |

**ከላይ የተዘረዘሩትን ቁጥሮች ግምታዊ ማሳያ ስለሆኑ አስፈጻሚ አካላት የእያንዳንዱ ወረዳ ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት በትግበራ ጊዜ ማስተካከል ይችላሉ።*

## 1.5. ዓላማውን ለአርሶ አደሮች የማስተዋወቅ አውደ ጥናት ማዘጋጀት

- የወረዳ ባለሞያዎች እና የልማት ሰራተኞች በመተባበር የትግበራ መርሃ-ግብር ያዘጋጃሉ (ሰንጠረዥ 66 ተመልከቱ)
- የወረዳ ባለሙያዎች እና የልማት ሰራተኞች በመመካከር ቀንና ቦታ ወስነው ለተሳታፊዎች ያሳውቃሉ።
- በተወሰነው ቀንና ቦታ መሰረት ህበረተሰቡን እንዲሰባሰብ ያደርጋሉ።

## 1.6. የአውደ ጥናት ዓላማውን ለአርሶ አደሮች ማስተዋወቅ ትግበራ

- የወረዳ እና ቀበሌ ባለሞያዎች መርሃ-ግብሩን ይፈጽሙታል

**የትግበራ ፍንጭ:- ዓላማውን ለአርሶ አደሮች ማስተዋወቅ ለምን?**

አዘጋጆች አርሶ አደሩን ስለ ኢትዮ-ሼፕ ዘዴ፣ ጽንሰ-ሀሳቦች/መርሆች በግልጽ ማስረዳት የሚጠቅመው በተጠቃሚዎችና ፈጻሚ አካላት የሚኖረውን መልካም ግንኙነት መገንባት እንዲቻል ማስተዋወቅ አስፈላጊ ነው።

## 1.7. በቀጣይ መሰራት ያለባቸው ተግባራት

- በአውደ ጥናት ፕሮግራሙ የተካፈሉ የአርሶ አደር ተወካዮች የቀሰሙትን እውቀት ለተቀረው አባል የማነሳሳት ስራ (በአትክልት ማምረት ዙሪያ ያሉትን እድሎች እና አቅም እንዲረዱትና ከገበያ ጋር አስተሳስሮ የማምረት ግንዛቤያቸውን ማሳደግ) ይሰራሉ፡፡
- የቀበሌ ባለሙያዎችና የአርሶ አደር ተወካዮች ቀጣይ ኢትዮ-ሼፐ ተግባራት ደረጃ በደረጃ ይተገብራሉ።

## 1.8. ፎቶግራፎች



የግንዛቤ ማሳደጊያ ቅስቀሳ ስብሰባ በአርሶ አደሮች አቅራቢያ ሲካሄድ



**ነጥቦች፡- ስነ-ጾታ በማስረጽ ላይ**

የግንዛቤ ማስተዋወቂያ ወርክ ሾፕ ሲካሄድ ብዙ ጊዜ ተሳታፊዎችን የአማከለ ቦታ ባለመሆኑ ፣ የዉይይት ቀኑ ሴቶች በቤት ስራ የማይበዛባቸዉን ቀኖች ከግምት ስለማይገባ የሴቶች ተሳትፎ ዝቅተኛ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም የተወሰኑ ሴቶች ወደ ስብሰባዉ ቢመጡም ሃሳባቸዉን በመግለጽና አስተያየት በመስጠት በኩል ተሳትፎአቸዉ ዝቅተኛ ነዉ፡፡ ስለዚህ የተሳታፊ ሴቶችን ቁጠር ከፍ ለማድረግ ስብሰባዉ የሚካሄድበት ቦታ ለሁሉም አማካይና አቅራቢያ የሆነ ፣ የስብሰባዉ ቀን ቢቻል ሴቶች ብዙ ስራ የማይሰሩበት የአካባቢ በዓል ቀንና ቢቻል ልጆቻቸዉ ሴቶችን ተክተዉ የቤት ጥበቃሁንና ህፃናትና የመንከባከብ ስራ የሚሸፍኑበት ቀን ቢሆን ይመረጣል፡፡

በስብሰባዉ ላይ የተገኙ ሴቶችም ከወንዶች ጋር እኩል ሃሳባቸዉን የመግለፅ አቅማቸዉ እንዲያድግ ስብሰባዉን የሚመራዉ አካል ሴቶች ከወንዶች በሚነሱት ሃሳቦች ላይ ተነስተዉ አሰተያየት እንዲሰጡ የመጋበዝና የማበረታታት ስራ መሰራት አለበት፡፡

**ድምጽ ከኢትዮጵያ መስክ**

**ለሰዎች ዓሳን እንዴት እንደሚመገቡ ከማስተማር እንዴት እንደሚያጠምዱ ማስተማር በህይወት ዘመናቸዉ እንዲመገቡ የሚያስችል እዉቀት እንዳስተማርህ ይቆጠራል፡፡**



“ኢትዮ ሼፐ ፐሮጅከት እንደሌሎች ፕሮጀክቶች ገንዘብ ወይም ቁሳቁስ አይሰጥም ፤ ነገር ግን ገንዘብ ወይም ሃብት እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ያስተምራል ፤ የሙያ ድጋፍ ያደርጋል ፡፡ ከመጀመሪያዉ አርሶአደሮችን ከጠባቂነት ለማላቀቅ የሚሰሩ ስራዎች ከባድ ቢሆንም በራሳቸዉ ተነሳሽነትና አቅም መስራት የሚያስችል ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ በመጀመሪያ በቂ ግንዛቤ ከተፈጠረላቸዉና በማሳ ላይ የትግበራ ስልጠና ከተሰጣቸዉ በኋላ በሚያገኙት ዉጤት ቀስ በቀስ እየተለወጡ እዉቀታቸዉና ክህሎታቸዉ እያደገ ሲሄድ የገንዘብ ወይም ቁሳቁስ ድጋፍ ጥያቄ አላስፍላጊነትን ይረዳሉ፡፡ በአሁኑ ወቅትም እየሆነ ለዉ ይህ ነዉ ፤ ከፐሮጅከቱ ገንዘብ ወይም ዉሳቁስ ድጋፍ አይፈልጉም፡፡ በአገኙት ዕዉቀትና ሙያ ድግፍ መሰረት ሰርቶ የመለወጥ ግንዛቤያቸዉ አድኋል፡፡”

**አቶ. ፀጋዬ ማሞ** (አግሮኖሚስት፤ የፐሮጀክቱ ፎካል ፤ ጥዮ ወረዳ ፤ አርሲ ዞን፤ ኦሮሚያ ክልል)

# የአርሶ አደሩን አቅም የማሳደግ ስልጠና

## 2. ደረጃ 2: አሳታፊ መነሻ ጥናት

| አራት (4) ደረጃዎች | ዋና ዋና ተግባራት (Activities) |
|---|---|
| 1. ግቡን እና ዓላማውን ለአርሶ አደርና ለአጋር አካላት ማስተዋወቅ | - የትውውቅ ፕሮግራም ማካሄድ |
| **2. የአርሶአደሮችን ግንዛቤ ማሳደግ** | - **አሳታፊ መሰረታዊ መረጃ የዳሰሳ ጥናት**<br>- የገበያ ጥናት |
| 3. የአርሶአደሮችን ውሳኔ ሰጭነት አቅም ማሳደግ | - የሰብል መምረጥ<br>- የሚያጋጥሙ ችግሮችን ልየታ ፣ የሰብል አመራረት የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀትና ማለማመድ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የባለድርሻ አካላት መድረክ ማዘጋጀት |
| 4. የአርሶአደሩን እዉቀትና ክህሎት ማሳደግ | - በገበሬ ማሳ ላይ ስልጠና መስጠት<br>- የስርዓተ ፆታ ስልጠና በመስጠት ግንዛቤ ማሳደግ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የልምድ ልውውጥ እና ጉብኝት ማካሄድ<br>- የመስክ ቀን/ የልምድ ልውውጥ ጉብኝት |
| የክትትልና ግምገማ (አሳታፊ የመጨሻ ውጤት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድን ያካትታል) | |

አዚህ ጋር ነን

### 2.1. መግቢያ

- በማንኛውም ፕሮጀክት/ፕሮግራም ትግበራ ሂደት የተጠቃሚዎችን መነሻ መረጃ መሰብሰብ በፕሮጀክቱ የመጣዉን ለውጥ/ መሻሻል ለመመዘን /ለመለካት ይቻል ዘንድ ወሳኝ ተግባር ነው። በተጨማሪም፡-
- የኤክስቴንሽን ሰራተኞችና ተጠቃሚ አርሶአደሮች ነባራዊ ሁኔታዎችን ይማሩበታል፣
- አርሶአደሮች የሂሳብ አያያዝ ጠቀሜታን ይረዳሉ፣ ቀላል ዘዴ በመጠቀም የእያንዳንዱን ሰብል ወጪ እና ገቢ ትንተና ከተደረገ በኋላ አርሶአደሮችን የተጣራ ትርፍ የሚያስገኝ ሰብል ለማወቅ ሰለሚረዳቸው ነዉ፡፡
- የወረዳ ባለሙያዎችና የቀበሌ ሰራተኞች የተጠቃሚ አርሶአደሮችን መነሻ እውቀትና ገቢ መጠን እንዲያውቁ ይረዳቸዋል።
- የወረዳ ባለሙያዎች እና ቀበሌ ሰራተኞች አሳታፊ ዳሰሳዊ ጥናት ለማካሄድ የሚያስችሉ መሰረታዊ እውቀት እና ክህሎት ይማሩበታል።

- በኢትዮ-ሼፐ ፕሮጀክት፣ ሁለት(2) መሳሪያዎች በመጠቀም መነሻ መረጃ ይሰበሰባል፡-

i) *የተጠቃሚ አርሶአደሮችን ሰብል ምርት /ሰም/እና ገቢ ትንተና መረጃ/ገትመ/ መመዝገቢያ ቅጽ።*

‘ሰም እና ገትመ’ ቅጽ፣- የአርሶ አደሮች ምርት መጠንና የሚያገኙት ገቢ ለመለካት ያገለግላል። በሚሰጣቸው ቅጽ በመጠቀም አርሶ አደሮች የእያንዳንዱን ሰብል ወጪ እና ገቢ ትንተና ከተደረገ በኋላ፣ አሳታፊ በሆነ መንገድ ለምርት የሚሆኑ ሁለት ተገቢ ሰብሎችን መምረጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ii) *የሆርቲካልቸር ሰብሎች አመራረትና የድህረ ምርት አያያዝ ዘዴ ጠቅላላ እዉቀት 24 (አሆሰአ እና ድምአቴ 24)*

‘አሆሰአ እና ድምአቴ 24’ ቅጽ፡- የአርሶ አደሮች መሰረታዊ መገምገሚያ መሳሪያ (መጠይቅ) ሲሆን ዋና አላማው ተጠቃሚ አርሶ አደሮችን በተመረጡ ሰብሎች ላይ የተሻሻሉ የአመራረት ቴክኒኮች ምን ያህል እንደተረዱትና ተግባራዊ እንዳደረጉት መገምገም ነው። መጠይቁ በተመረጡ አትክልቶች ላይ አመራረትና ግብይት ለማሻሻል እንዲረዳ አርሶ አደሮችን በማሳተፍ የማላመድና የማምረት ስልጠና በስፋት ከተሰራ በኋላ ከቅድመ ምርት ዝግጅት፣ ማሳ ዝግጅት፣ ዘር መዝራት/ችግኝ ማዛመት፣ ሰብል እንክብካቤ፣ ምርት መሰብሰብ ድህረምርት አያያዝ፣ የገቢና ወጪ መረጃ መያዝና መተንተን የመሳሰሉትን ዕውቀትና ክህሎትን በተመለከተ አጠቃላይ መረጃ ከተጠቃሚ አርሶ አደሮች ለመሰብሰብ ያስችላል። በተጨማሪም ከአርሶአደሮች በቡድን ደረጃ ስለ ግብይት (ግብዓት መግዛት/ ምርት መሸጥ) እንዲሁም ስርዓተ-ጾታ መካተት የተመለከቱ መረጃዎች ይሰበሰባሉ።

### 2.2. ዓላማዎች

- በተጠቃሚ አርሶአደር ደረጃ ከሆርቲካልቸር ሰብሎች የሚያገኙትን ምርትና የገቢ መጠን ለማወቅ፣
- በተጠቃሚ አርሶአደር ደረጃ ከተመረጡ ሰብሎች አንጻር የተሻሻሉ የአመራረት ቴክኒኮች ምን ያህል እንደተረዱትና ተግባራዊ እንዳደረጉት ለመገምገም ፣

- የአርሶ አደሮች በቡድን ደረጃ ግብይት (ግብአት መግዛት/ ምርት መሸጥ) መቻላቸውን ለማወቅ፣
- አሁናዊ የስርዓተ-ጾታ ጉዳዮች ሁኔታ ለማወቅ።

## 2.3. የመነሻ መሰረታዊ መረጃ/ ጥናት ቅንጅትና አተገባበር

### 2.3.1. ተሳታፊዎች

**አመቻች**:- የልማት ሰራተኞችና የወረዳ (የሆርቲካልቸር ሰብሎች ልማት ቡድን /ሰብል ልማት ቡድን/፣ ኤክስቴንሽን ቡድን፣ እና በዞን ደረጃ የፕሮጀችቱ ተውካይ (focal person)።

**ተሳታፊዎች**:- ከያንዳንዱ ቡድን የተውጣጡ የአርሶአደር ተወካዮች።

### 2.3.2. የሚወስደው ጊዜ

አንድ (1)ቀን

**ሰንጠረዥ 7.** አሳታፊ መሰረታዊ መረጃ / መነሻ ዳሰሳዊ ጥናት ተግባራዊ ልምምድ ለማካሄድ የሚያገለግል መርሀ-ግብር

| ሰዓት | ተግባራት |
|---|---|
| 2:30 - 3:00 | የተሳታፊዎች ምዝገባ<br>የመክፈቻ ንግግር |
| 3:00 - 3:20 | መነሻ ዳሰሳ ጥናት መተግበርያ ቅጽ 1:- የተጠቃሚ አርሶአደሮች ሰብል ምርት እና ገቢ ትንተና መረጃ (ሰም እና ገትመ) መመዝገብያ ቅጽ።<br>መሰረታዊ መረጃ ጥናት መተግበሪያ ቅጽ 2: የሆርቲካልቸር ሰብሎች አመራረትና የድህረ ምርት አያያዝ ዘዴ ጠቅላላ እዉቀት (አሆሰአ እና ድምአቴ) ጂ-24 |
| 3:20 - 3:30 | በቀጣይ መሰራት ያለባቸው ተግባራት<br>የመዝጊያ ንግግር |

### 2.3.3. መሰብሰቢያ ቦታ

በተጠቃሚ አርሶ አደሮች አቅራቢያ የሚገኝ አማካይ ቦታ ፡- በዛፍ ጥላ ስር ወይም በገበሬዎች ማሰልጠኛ ማዕከል (FTC) ፣ ትምህርት ቤቶች ፣በቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት ሊሆን ይችላል

## 2.4. ናሙና በወረዳ ደረጃ ግምታዊ በጀት ለማዘጋጀት የሚረዳ ቅጽ

| የክፍያ ዓይነት | የቀን ብዛት | የሰው ብዛት |
|---|---|---|
| አበል (ለወረዳ ባለሙያ) | 1 | 2 |
| የትራንስፖርት/የነዳጅ ወጭ (ለወረዳ ባለሙያ) | 2 | 2 |
| የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች (የመሰረታዊ መረጃ ቅጽ፣ የጽህፈት መሳሪያዎች) | 1 | 45 |

**ማስታወሻ፡- ከላይ የተዘረዘሩትን ቁጥሮች ግምታዊ ማሳያ ስለሆኑ አስፈጻሚ አካላት የእያንዳንዱ ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት በትግበራ ጊዜ ማስተካከል ይችላሉ።*

**በዞን ደረጃ ግምታዊ በጀት ለማዘጋጀት የሚረዳ ናሙና ቅጽ**

| የክፍያ ዓይነት | የቀን ብዛት | የሰው ብዛት |
|---|---|---|
| (ለዘን ባለሙያ) | 1 | 1 |
| (ለዘን ባለሙያ ሹፌር) (እንደአስፈላጊነቱ) | 1 | 1 |
| የነዳጅ ወጭ ለዘን ባለሙያ | 1 | 1 |

## 2.5. የመሰረታዊ መረጃ /መነሻ ዳሰሳዊ ጥናት ተግባራዊ ልምምድ የዝግጅት ሂደት

- የዞን እና የወረዳ ሆርቲካልቸር እና ኤክስተንሽን ቡድን አስፈላጊ የትግበራ ቅጾች (ሰም እና ገትመ ቅጾች፣ አሆሰአ እና ድምአቴ፡ ጂ-24)፣ እና ሌሎች መረጃ መሰብሰያ ቅጾች፡-የአባልነት ዝርዝር እና የተሳታፊዎች ዝርዝር ) ማዘጋጀት (እባክዎን ዕዝል 2.2 ይመልከቱ)፣
- የወረዳ ሆርቲካልቸር (ሰብል ልማት እና ኤክስቴንሽን ቡድን የጥናቱ ጊዜ ሰሌዳ ያዘጋጃሉ ።

## 2.6. መነሻ ዳሰሳዊ ጥናት እንዴት በተግባር መፈጸም እንደሚቻል

የወረዳ ባለሞያ እና ልማት ሰራተኛ የዳሰሳ መጠይቆች ለአርሶ አደሮች አስፈላጊ ገለጻ ማድረግ፣ በመቀጠልም መጠይቆችን ማሰራጨት። ትምህርት ያላቸዉ አርሶ አደሮች በልማት ሰራተኞች ድጋፍ መጠይቁን እንዲሞሉ ይደረጋል።  በተለይ በመጀመሪያ አርሶ አደሮች መጠይቁን በትክክል መረዳታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

**የትግበራ ፍንጭ፡-አሳታፊ መሰረታዊ መረጃ/ መነሻ ዳሰሳዊ ጥናት ለምን?**

ይህ ልምምድ የልማት ሰራተኞች፣ የወረዳ ባለሙያዎች ተጠቃሚ አርሶ አደሮች በተመለከተ አሁናዊ የአርሶ አደሮች ገቢ፣ እውቀት፣ ክህሎትስነ- ጾታዊ ምልከታ ላይ መረዳት ያስችላቸዋል። ተጠቃሚ አርሶ አደሮች በበኩላቸው የራሳቸውን አሁናዊ ገቢ፣ እውቀት፣ ክህሎት የመሳሰሉት ለማወቅ/ለመመዘን ይጠቅማቸዋል።

## 2.7. የወደፊት አቅጣጫ

የገበያ ጥናት አካሄድን በተመለከተ ከአርሶ አደሮች ጋር ውይይት ማድረግ

## 2.8. ፎቶግራፍ



በቀበሌ ባለሙያ ድጋፍ ያልተማሩ አርሶ አደሮች መሰረታዊ መረጃ የመነሻ ዳሰሳ መረጃ መሰብሰብያ ቅጽ መስክ ላይ ሲሞሉ



**ነጥቦች፡- ስነ-ጾታን በማስረፅ ላይ**

የሆርቲካለቸር ሰብሎች አመራረትና ግብይት መሰረታዊ መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት ብዙ ጊዜ ሴቶች አይሳተፉም፡፡ ምክንቱም መረጃ የመስጠት ተግባር የወንዶች ነዉ ብለዉ ስለሚገምቱና ወንዶችም ሴቶችን በስብሰባ ወቅት ወንዶችን ተክተዉ ተገኝተዉ ሃሳብ እንዲሰጡ ስለማያደርጉ ነዉ፡፡ ስለዚህ መሰረታዊ መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት በተቻለ መጠን ሴቶችም (ቢቻል ባልና ሚስት) የሆርቲካለቸር ሰብሎች አመራረትና ግብይት መሰረታዊ መረጃ ቢሰበሰብበት ወቅት ተገኝተዉ መረጃ እንዲሰጡ ማደረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህም የሴቶችን ከወንዶች ጋር በእኩልነት ስሜት ሃሳበቻዉን የመግለጽ ልምድ

## 2.9. ናሙና ቅጾች

**ስዕል 6.** የፕሮጀክት መጨረሻ ዳሰሳዊ ጥናት መረጃ መሰብሰብያ ቅጽ

**የሰብል ምርት እና ገቢ ትንተና (CP&IA)መረጃ ቅጽ (rev.2)**

ዞንወረዳ ______ ኮድ: ተበር/WUA Name: ______ መረጃ የተሰበሰበት ቀን: ______

የአርሶ አደር ስም: ______ ወንድ/ሴት: the official list: ______

የወረቀት ቁጥር/# of sheet: ______

| የሰብል ስም (ዝርያ) | የማሳ ስፋት መለኪያ (ሄክታር፣ ጥማድ) | የምርት መጠን (በባህላዊ ልኬት) | የሽያጭ መጠን (በባህላዊ ልኬት) | አማካይ ዋጋ (ብር/ልኬት) | ጠቅላላ ገቢ (ብር) | ጠቅላላ የማምረቻ ወጭ (ብር) | የተጣራ ገቢ (ብር) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በምስና የተዘራ 1 | | | | | | ዳፕ /ኤንፒኤስ<br>ዩርያ<br>ዘር<br>ኬሚካል<br>ጉልበት<br>ሌሎች | |
| በምስና የተዘራ 2 | | | | | | ዳፕ /ኤንፒኤስ<br>ዩርያ<br>ዘር<br>ኬሚካል<br>ጉልበት<br>ሌሎች | |
| በዝናብ የተዘራ 1 | | | | | | ዳፕ /ኤንፒኤስ<br>ዩርያ<br>ዘር<br>ኬሚካል<br>ጉልበት<br>ሌሎች | |
| በዝናብ የተዘራ 2 | | | | | | ዳፕ /ኤንፒኤስ<br>ዩርያ<br>ዘር<br>ኬሚካል<br>ጉልበት<br>ሌሎች | |

**ስዕል 7.** የመሰረታዊ መረጃ / መነሻ ዳሰሳ ጥናት የተሞላ ቅጽ - ምሳሌ

**የሰብል ምርት እና ገቢ ትንተና (CP&IA)መረጃ ቅጽ (rev.2)**

ቀን XXXX/XX/XX **ምሳሌ**

የወረዳ ስም XXXXXXXXXX የቀበሌ ስም XXXXXXXXXX

የአርሶ አደር ስም: XXXXXXX ወንድ/ሴት: ወንድ/ሴ የአርሶ አደር ቡድን ስም XXXXXXXXXX

ስልክ ቁጥር XXXXXXXXXX

| የሰብል ስም (ዝርያ) | የማሳ ስፋት መለኪያ (ሄክታር፣ ጥማድ) | የምርት መጠን (በባህላዊ ልኬት) | የሽያጭ መጠን (በባህላዊ ልኬት) | አማካይ ዋጋ (ብር/ልኬት) | ጠቅላላ ገቢ (ብር) | ጠቅላላ የማምረቻ ወጭ (ብር) | የተጣራ ገቢ (ብር) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በምስና የተዘራ 1<br>ድንች | 3 ጥማድ | 1(ኩ/ል)=(100)ኪ.ግ 100ኩ/ል | 90 ኩ/ል | 500 ብር | 45,000.00 | ዳፕ /ኤንፒኤስ 1,890 ብር/135 ኪ.ግ<br>ዩርያ 1,260 ብር/90 ኪ.ግ<br>ዘር 1,0500 ብር/150 ኪ.ግ<br>ኬሚካል 600 ብር/2 ጠርሙስ<br>ጉልበት 600 ብር<br>ሌሎች 300 ብር | 29,850 |
| በምስና የተዘራ 2<br>ጥቅል ጎመን | 2 ጥማድ | 1(ኩ/ል)=(75)ኪ.ግ 210ኩ/ል | 210 ኩ/ል | 200 ብር | 36,000.00 | ዳፕ /ኤንፒኤስ 1,600 ብር/100 ኪ.ግ<br>ዩርያ 700 ብር/50 ኪ.ግ<br>ዘር 1,100 ብር/200 ኪ.ግ<br>ኬሚካል 1,200 ብር/2 ጠርሙስ<br>ጉልበት 300 ብር<br>ሌሎች | 29,820 |
| በዝናብ የተዘራ 1<br>ስንዴ | 2 ጥማድ | 1(ኩ/ል)=(110)ኪ.ግ 80ኩ/ል | 11 ኩ/ል | 800 ብር | 8,800.00 | ዳፕ /ኤንፒኤስ 1,600 ብር/120 ኪ.ግ<br>ዩርያ 700 ብር/50 ኪ.ግ<br>ዘር 1,600 ብር/200 ኪ.ግ<br>ኬሚካል 1,200 ብር/2 ጠርሙስ<br>ጉልበት 1,000 ብር<br>ሌሎች | 3,900 |
| በዝናብ የተዘራ 2 | | | | | | | |

**ስዕል 8.** የመሰረታዊ/ መነሻና መጨረሻ ዳሰሳ ጥናቶች ላይ የግብርና ዘዴ ክህሎቶች መረጃ መሰብሰብያ ቅጽ-ጂ-24

## የሆርቲካልቸር ሰብሎች አመራረትና የድህረ ምርት አየያዝ ዘዴ ጠቅላላ እዉቀት (አሆሰአ እና የድምአቴ ) 24

ክልል: ____________ ዞን ____________

የወረዳ ስም: ____________

የቡድኑ ስም/ቀበሌ: ____________ ቀን: ___ / ___ / ___

የአርሶ አደሩ ስም: ____________ ወ / ሴ: ______ ስልክ ቁጥር.: ____________

| | ከቅደም ምርት እስከ ደህረ ምርት ተግባራት | ጥያቄዎች | የሆርቲካለቸር ሰብሎች አመራረት ዘዴዎች | አዎ | የለም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቅድመ ምርት ዝግጅት | ጥ1 | የሚመርቱትን ሰብል የገበያ ፍላጎት ለማወቅና ለማስተካከል የገበያ ጥናት በማካሄድ መረጃ ይሰበስባሉ ? | | |
| | | ጥ2 | ከገበያ ቅኝት ወይም ጥናት በሚያገኙት መረጃ መሰረት የሚያመርቱትን ሰብል አቅድና የማምረቻ የጊዜ ሰሌዳ ያዘጋጃሉ ? | | |
| | | ጥ3 | በማሳዉ ላይ የሚበቅሉ አረም አይነትና አፈሩ ሁኔታ በመቃኘት ወይም በማየት የመሬትዎን አፈር ለምነት ይገምትሉ? | | |
| | | ጥ4 | በማሳዎ ላይ የሚዘሩት ሰብል የሚያስፈልገዉን ጥከክለኛዉን ንጥረ ነገር (ናይትሮጅን፣ ፎስፈረስና ፖታሲየም) እንዲያገኝ /አፈር ልምነት ለመጠበቅ/ በትክክና በምክረ ሃሳቡ መሰረ የተዘጋጀ ኮምቦስት ይጠቀማሉ? | | |
| | | ጥ5 | ጥራቱን የጠበቀ ዘር የሚጠቀሙ ከሆነ ከሚከተሉት የዘር ጥራት መመዘኛ መስፈርቶች ዉስጥ እርስዎ በምክረሃሳቡ መሰረት ተግባራዊ የሚያደርጉት የትኛዉን ነዉ? በሽታን የሚቋቋሙ ዝርያ መጠቀም? ከፍተኛ ምርታማነት ያለዉን ዝርያ መጠቀም? ቀድመዉ የሚደርሱ ዝርያዎች መጠቀም ? ጥሩ ጣዕም ያላቸዉን መጠቀም? በገበያ ተፈላጊ የሆኑትን ? ለረጅም ጊዜ ሳይበላሹ በመጋዘን መቆየት የሚችሉትን ዝርዎች መጠቀም? (ከስሩ በማስመር ምልክት ያደርጉ) | | |
| 2 | ማሳ ዝግጅት | ጥ6 | በሰብልዎ ላይ የተባይና በሽታ ክስተትን ለመቀነስ ወይም ለመከላከል አስቀድመዉ በማሳ ዘግጅት ወቅት ምን ምን ተጋባራትን ያከናዉናሉ ? አፈሩን በሙቀት ማከም ? በወቅቱ ማረስ? በጥልቀት ማረስ? ከማሳ ላይ በሽታና ተባይ ክስተት ሚያመጡ የሚችሉ ቃርሚያዎችን ማስወገድ ? የሰብል ፈቀረቃ መጠቀም ? (ከስሩ በማስመር ምልክት ያደርጉ) | | |
| | | ጥ7 | የአፈርን ለምነት ለማሻሻል ዘር ከመዝራትዎ ቢያንስ አንድ ወር አስቀድሞ ጠቃሚ የሰብል ቅሪቶችን ከአፈር ጋር ይቀላቅላሉ/ይጨምራሉ? | | |
| | | ጥ8 | ከዘር በፊት ቢያንስ ሁለት ሳምንትና ከዚያ በላይ አስቀድሞ በማሳዎ ላይ የተፈጥሮ ማዳበሪያ (ፍግ፣ኮምፖስት ወዘተ) በመበትን ከአፈር ጋር መቀላቀል ተግባራዊ ያደርጋሉ ? | | |
| 3 | ዘር መዝራት ወይም ማዛመት | ጥ9 | ለአትክልት ችግኝ ለማዘጋጀት በምክረ ሃሳቡ መሰረት የተቀመጡ አሰራሮችን ተግባራዊ ያደርጋሉ? | | |
| | | ጥ10 | ዘር ሲዘሩና ችግኝ ሲያዛምቱ በምክረ ሃሳቡ መሰረት አርቀቱን ጠብቀዉ ይዘራሉ ወይም የዛምታሉ ? | | |
| | | ጥ11 | ለሚዘሩት ሰብል የሚያስፈልገዉን ማዳበሪያ ዓይነትና መጠንና ወቅት በትክክል በምክረ ሃሳቡ መሰረት ይጨምራሉ ? | | |
| 4 | ሰብል እንክብካቤ | ጥ12 | ለእያንዳንዱ ሰብል የሚያስፈልገዉን የመስኖ ዉሃ መጠንና ድግግሞሽ ፡ የሰብሉን የእድገት ደረጃ ከግምት በማስገባት የመስኖ ዉሃ ይጠቀማሉ ? | | |
| | | ጥ13 | ሰብልዎን በወቅቱ በማረምና በትክክለኛ መሳሪያ በመኮትኮት አረም ይቆጣጠራሉ ? | | |
| | | ጥ14 | ከዘር ወይም ተከላ በኋላ ተጨማሪ ማዳበሪያ ዓይነትና መጠን በወቅቱ .....ይጨምራሉ ? | | |
| | | ጥ15 | ከሚከተሉት የተባይና በሽታ መከላከያ ዘዴዎች ውስጥ እርስዎ የትኞችን ተግባራዊ አድርዋል ? በባህላዊ መከላከያ ዝዴዎች መጠቀም፡ ስነ ህይወታዊ መከላከያ ዘዴዎች መጠቀም፡ አካላዊና ኬሚካል በመጠቀም( የሰብል ፈረቃ መጠቀም፡ በበሽታ የተጠቁትን ማስወገድ ፡ አመድ መጠቀም) (ከስሩ በማስመር ምልክት ያደርጉ) | | |
| | | ጥ16 | ኬሚካል በሚጠቀሙበት ወቅት ትክክለኛዉን የፀረ ተባይ አጠቃቀም ዘዴዎችን ይከተላሉ ?( ትክክለኛ ፀረ ተባይ አይነትና መጠቀም፡ መጠኑን በምክረሃሳቡ መሰረት መጠቀም ፡ ምርት ከመሰብሰቡ በፊት ለዉን የርጨት ቆይታ ጊዜ ጠብቆ ምርት ይሰበስባሉ ፡ (ከስሩ በማስመር ምልክት ያደርጉ) | | |
| 5 | ምርት መሰብሰብ | ጥ17 | ሰብል ለመስብሰብ መድረሱን የሚያሳዩ ምልክቶችን ያዉቃሉ ? ( የፍረዉን መጠንከር፣ መልኩን፣ ቅርፅና መጠኑን፣ ጊዝዉን በማየት፣ (ከስሩ በማስመር ምልክት ያደርጉ) | | |
| 6 | ድህረምርት አየያዝ | ጥ18 | ለገበያ ሚሆኑ ሰብሎችን በሚሰበስቡበት ወቅት ተገቢዉን የድህረ ምርት አዩያዝ ምክረ ሃሳቦችን ከግምት ያስገባሉ ? ( ከማጓጓዝ በፊት ማድረቅ ወይም ማጠዝዘዝ፡ የሽንኩርትን ግንድ የሚቆረጥበት ቦታ ለይቶ መቁረጥ፡ ምርቱ በቀዝቃዛና ጥላ ቦታ ማቆየት (ቲማቲም ድንች) (ከስሩ በማስመር ምልክት ያደርጉ) | | |
| | | ጥ19 | ምርት በሚሰበስቡበት ወቅት የማጥራት፣ በደረጃ፣ የመለየት ፣ እሴት መጨመር ተግባራት ያካሂዳሉ? | | |
| 7 | የገቢና ወጪ መረጃ መያዝና መተንተን | ጥ20 | የሚያመርቱትን ሰብል የማምረቻ ወጪና ገቢ በትክክል በመመዝግብ የገቢ ስሌት ሂሳብ ይሰራሉ? | | |
| 8 | ሌሎች ተግባራት | ጥ21 | ምርትዎን ለማን እንደሚሸጡ፡ እንዴት እንደሚሸፁ፡ የገበያ ትስስር እንዴት እንደሚፈጠር አዉቀዋል ተዥዎችዎን ለይተዉል? (ጅምላ ገዥዎችን፡ ደላላለዎችን፡ ግብዓት አቅራቢዎችን ፡ የምክር አገልግሎት የሚሰጡዎትን ድርጅቶችን (ምርምር ግብርና ማህበራት ዘር አቅራቢዎችን ወዘተ) ? | | |
| | | ጥ22 | ለማምረት የሚያስፈልገዎን ዘር፡ ማዳበሪያ ወይም ኬሚካል በቡድን ወይም በጋራ ይገዛሉ? | | |
| | | ጥ23 | ምርትዎን ለመሸት በቡድን በጋራ ወደ ገበያ ያጓጉዛሉ ወይም የሸጣሉ? | | |
| 9 | ሥርዓተ ፆታ | ጥ24 | ምን ማምረት እንዳለብዎትና እንዴት ማምረት እንዳለብዎ ከባለቤትዎ ጋር በጋራ ተወያይተዉ ያቅዳሉ? | | |

* በመልስ መስጫዉ ቦታ(ለትክከለኛ ✓) ትክክል ላልሆነዉ ) X) ምልክት ያደርጉ ወይም "አዎ" or "የለም ". ተጨማሪ መረጃ ካለ ምርመራ ላይ የግለፁ

# የአርሶ አደሩን አቅም የማሳደግ ስልጠና



## 3. ደረጃ 3: የገበያ ጥናት

| አራት (4) ደረጃዎች | ዋና ዋና ተግባራት (Activities) |
|---|---|
| 1. ግቡን እና ዓላማውን ለአርሶ አደርና ለአጋር አካላት ማስተዋወቅ | - የትውውቅ ፕሮግራም ማካሄድ |
| 2. **የአርሶአደሮችን ግንዛቤ ማሳደግ** | - አሳታፊ መሰረታዊ መረጃ የዳሰሳ ጥናት<br>- **የገበያ ጥናት** ⬅ እዚህ ጋር ነን |
| 3. የአርሶአደሮችን ውሳኔ ሰጭነት አቅም ማሳደግ | - የሰብል መምረጥ<br>- የሚያጋጥሙ ችግሮችን ልየታ ፣ የሰብል አመራረት የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀትና ማለማመድ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የባለድርሻ አካላት መድረክ ማዘጋጀት |
| 4. የአርሶአደሩን እዉቀትና ክህሎት ማሳደግ | - በገበሬ ማሳ ላይ ስልጠና መስጠት<br>- የስርዓተ ፆታ ስልጠና በመስጠት ግንዛቤ ማሳደግ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የልምድ ልውውጥ እና ጉብኝት ማካሄድ<br>- የመስክ ቀን/ የልምድ ልውውጥ ጉብኝት |
| የክትትልና ግምገማ (አሳታፊ የመጨሻ ውጤት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድን ያካትታል) | |

### 3.1. መግቢያ

ከኢትዮ-ሼፕ ዋና ዋና አላማዎች አንዱ በፕሮጀክቱ የታቀፉ አርሶ አደሮችን ክህሎት ማሳደግ ነው። ስለዚህ የገበያ ጥናት የሚከናወነው በኤክስቴንሽን ባለሞያዎች ወይም ቅጥር አማካሪዎች ሳይሆን በራሳቸው በአርሶ አደሮቹ ነው። የገበያ ጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ አርሶ አደሩ የሚያመርተውን ሰብል የገበያ ፍላጎት፣ ምርቱን በሚፈለገው ጊዜ ማቅረብ ፣ ተፈላጊ ብዛትና ጥራት ማወቅ ያስችለዋል። ጅምላ ነጋዴዎች ከአምራቾች ምን አይነት ምርት መግዛት እንደሚፈልጉ፣ በምን ምክንያት ከሌላ ቦታና ከሌሎች አርሶ አደሮች መግዛት እንደማይፈልጉ ይረዳሉ። ይህም ከጅምላ ነጋዴዎች ጋር በሚደረግ የሀሳብ ልውውጥ አማካኝነት በመካከላቸው **ጥሩ የንግድ አጋርነት ትስስር** እንዲመሰረት ያስችላል።

### 3.2. አላማዎች

- በአርሶአደሮችና በገበያ እሴት ሰንሰለቱ ላይ ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት (ግብዓት አቅራቢዎች፣ ነጋዴዎች፣ ደላሎች፣ አቀናባባሪዎች፣ ማህበራት፣ ብድር አቅራቢ ተቋማት እና የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት) መካከል ያለውን የግንኙነት ክፍተቶች ለመረዳት፣
- በአርሶ አደሮችና ጅምላ ነጋዴዎች መካከል ትስስር ለማጠናከር፣
- በመረጧቸው አትክልቶች/ሰብሎች ዙሪያ ያሉትን እድሎች አስፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ።

### 3.3. የገበያ ጥናት ለማካሄድ የሚሰሩ ስራዎች

#### 3.3.1. ተሳታፊዎች

**አመቻች አካል**:- የወረዳው የአትክልት/ፍራፍሬ ልማት ክፍል (ወይም ሰብል ልማት ክፍል) ወረዳ ንግድ ጽ/ቤት እና የዞን የአትክልት/ፍራፍሬ (ሰብል ልማት) ቡድን።

**ተሳታፊዎች**:- የተጠቃሚ አርሶአደሮች ተወካዮች እና የልማት ሰራተኛ

#### 3.3.2. የሚወስደው ጊዜ

➢ ግማሽ ቀን

**ሰንጠረዥ 8.** ናሙና የገበያ ዳሰሳ ጥናት ተግባራትና የጊዜ ሰሌዳ

| ሰዓት | ተግባራት |
|---|---|
| 1:30 - 2:00 | የተሳታፊዎችን ምዝገባ፣<br>ከገበያ ተዋናዮች (ነጋዴዎች) ጋር እንዴት መግባባት እንዳለባቸው አጠር ያለ ማብራሪያ መስጠት |
| 2:00 - 4:00 | የገበያ ቅኝት ማከናወን፣ |

| | |
|---|---|
| | በእያንዳንዱ ቡድን የተሰበሰበው መረጃ ማደራጀት ይቀጥላል፣ |
| 4:00 - 5:50 | የጥናቱ ግኝቶች (የነጋዴዎች አድራሻ መለዋወጥ፣ መረከቢያ ዋጋ፣ ከፍተኛው የምርት ፍላጎት ያለበት ወር፣ ሌሎች ግኝቶች) መረዳት፣ |
| 5:50 - 6:00 | ማጠቃለያና የወደፊቱ ተግባራት |
| 6:00 - 7:00 | የምሳ እረፍት (እንደ አስፈላጊነቱ) |

### 3.3.3. ቦታ

የሚዘጋጀው ቦታ በገበያ አቅራቢያ መሆን አለበት (ቅርብ በሆነ አካባቢያዊ ገበያ ተመራጭ ነው)

## 3.4. በጀት ለማዘጋጀት የሚረዳ የናሙና ቅጽ

| የበጀት ዓይነት/ Budget Category | የቀን ብዛት | የሰው ብዛት |
|---|---|---|
| አበል (ለልማት ሰራተኞች) | 1 | 3 |
| አበል (ለወረዳ ባለሞያ) | 1 | 2 |
| የትራንስፖርት ወጭ (ለልማት ሰራተኞች) | 1 | 3 |
| የትራንስፖርት/ የነዳጅ ወጭ (ለወረዳ ባለሞያ) | 2 | 2 |
| የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች (የገበያ ጥናት ቅጽ፤ ተገላጭ ቻርት፤ መፃፊያ ማርከር፤ክሊፕ ቦርድ) | 1 | 1 |

**ከላይ የተዘረዘሩት ቁጥሮች ግምታዊ ማሳያ ስለሆኑ አስፈጻሚ አካላት የእያንዳንዱ ወረዳ ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት በትግበራ ጊዜ ማስተካከል ይችላሉ።*

## 3.5. የገበያ ጥናት ለማካሄድ የቅድመ-ዝግጅት ተግባራት

- የወረዳ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ቡድን (ሰብል ልማት ክፍል) ከወረዳ ንግድ ጽ/ቤት ባለሙያዎች ጋር አንድ ላይ በመሆን የገበያ ጥናት መርሃ-ግብር ያዘጋጃሉ። በጥናቱ ቀን/ሰዓት መሰረት ከነጋዴዎች ጋር ቀጠሮ ይይዛሉ።
- አመቺ ጊዜ በመመደብ ለነጋዴዎች (ጅምላ ሻጮችና ቸርቻሪ ነጋዴዎች) ማብራሪያ/ ገለጻ ማድረግ።
- የገበያ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያ ቅጽ ወደ አካባቢው ቋንቋ መተርጎም (እንደአስፈላጊነቱ) እና ማተም (ማገናዘብያ ሰንድ ዕዝል 2.3 ተመልከቱ)

## 3.6. የገበያ ጥናት የማካሄጃ ስልቶች

- ወደ ገበያ ከመሄድ በፊት ተሳታፊዎችን በንዑስ ቡድን መክፈል። ከ4 እስከ 6 ሰው አንድ ላይ ሲሆኑ ሂደቱን ለማስተባበር ቀላል ሊሆን ይችላል።
- ከቡድን መሪዎች ጋር በመመካከር የሚከተሉትን ተግባርና ሃላፊነቶች መመደብ፦ ቃለ-መጠይቅ አድራጊ፣ ማስታወሻ ያዥ፡ ሰዓት ያዥ (ሰንጠረዥ 9)
- የእያንዳንዱን አርሶ አደሮች ቡድን በባለሞያዎች ድጋፍ(ዕገዛ) ማመቻቸት። ነገር ግን ባለሞያዎች ድጋፍ ያደርጋሉ እንጂ እራሳቸው ፈጻሚ እንዳልሆኑ ሊታወቅ ይገባል።
- አርሶ አደሮች በራሳቸው እንዲጠይቁ ማበረታታት አንርሳ፤

**የትግበራ ፍንጭ: የአርሶ አደሮች የገበያ ጥናት ለምን?**

በሼፕ ዘዴ የገበያ ጥናት የሚካሄደው በአርሶ አደሮች በራሳቸው አማካይነት በአቅራቢያ በሚገኙ ገበያዎች ውስጥ የገበያ መረጃ (ከፍተኛ የምርት ፍላጎት ጊዜ) በመሰብሰብ በአምራችና ነጋዴዎች ያለው **ክ**ፍተት ለመሙላት ነው። በመካከላቸውም መተማመን እንዲፈጠር ያስችላል።

**ሰንጠረዥ 9.** የጥናት ቡድን ተግባርና ሃላፊነቶች

| ቁጥር | ሚና | ተግባር |
|---|---|---|
| 1 | የቡድን መሪ | መግቢያ ሰላምታና ስለ ጥናቱ ማብራሪያ ንግግር ለጅምላ ነጋዴዎች ማቅረብ |

| | | |
|---|---|---|
| 2 | ቃለ-መጠይቅ አድራጊ | እያንዳንዱ ጥያቄ መጠየቅ |
| 3 | ማስታወሻ ያዥ | የቃለ-መጠይቁ ቅጽ መሙላት |
| 4 | ሰዓት ያዥ | ባጠቃላይ በ 14 ደቂቃ ለመጨረስ ይሞክሩ።<br>የነጋዴው ደንበኞች በሚመጡበት ሰዓት ቃለ-መጠይቁ መቆም አለበት |

**የልማት ሰራተኞች ሚና፡- አርሶ አደሮች በቅጹ መሰረት መረጃውን በትክክል እንዲመዘግቡ ድጋፍ (እገዛ) ማድረግ ነው።*

## 3.7. ቀጣይ ተግባር

የአርሶአደሮች ተወካዮች ከገበያ ጥናቱ ስለተማሩት ነገር ለቡድን አባላት ግብረ-መልስ ይሰጣሉ፣ እንዴት እንዳከናወኑት ይገልጻሉ።

## 3.8. ፎቶግራፎች



አርሶ አደሮች ጅምላ ነጋዴዎችን የገበያ መረጃ ሲጠይቁ



አርሶ አደሮች የገበያ ጥናት ቅጽ በሞሙላት ላይ



**ነጥቦች፡- ስነ-ቶታን በማስረፅ ላይ**

የገበያ ጥናት በሚካሄድበት ወቅት ብዙ ጊዜ ለገበያ ኮሚቴ አባልነት የሚመረጡት ወንዶች ናቸዉ፣ ሴቶች ቢኖሩም በቁጥርና በተሳተፎ ደረጃ ዉስንነት አለበት።ስለዚህ በገበያ ጥናት /የገበያ መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት የሴቶች ተሳተፎ ማደግ አለበት ። ምክንቱም ሴቶች በተከታታይ ገበያ የመሄድ ልምድና ለሆርቲካልቸር ሰብሎች (ጥራት ፤ ጣዕም ፣ መጠን ወዘተ) ተፈላጊነትና ግብይቱ ላይ ቅርበት ስለአላቸዉ በገበያ ጥናት ቡድን ዉስጥ የወንዶችንና የሴቶችን ቁጠር ማጣጣመን በአባልነት እንዲሳተፉ ማድረግ ያስፈልግል ።

በጥናት ቡድን ዉስጥ የሚገቡትም ቢሆን የገበያ መረጃ ሲሰበስቡ በመጠየቅ ፣ ሃሳብ በመስጠት በኩል

## 3.9. ናሙና ቅጾች

**ስዕል 9.** የገበያ ጥናት መጠይቅ

### የገበያ መረጃ መሰብሰብያ መጠይቅ

ቀን፡ ______/__________/_______

የዞኑ ስም: ____________________ ክልል ________________

የገበያ መረጃ የሰበሰበው ስም (የአርሶ አደሮች ስም ዝርዝር) ወረዳ ________________

| የነጋዴው ስምና አድራሻ | ተፈላጊ ምርት መጠንና አይነት | አቅርቦት መጠንና ተፈላጊው ጥራትና መስፈርቶች | ከፍተኛ ገበዩአ ፍላጎት ያለበት (ወራት) | የምርትቱ በአንድ ጊዜ የሚቀርበው መጠንና ድግግሞሽ (እለታዊ፣ ሳንታዊ፣ ወዘት ) | የተመረተ በት ቦታ | የአንዱ ዋጋ (ብር/ኪግ) | የክፍያ መንገድ | የአከፋፈል ሁኔታ | የግብይት ተግዳሮቶ ች | ነጋዴው ከቡዱኑ ለመግዛት ያለው ፍላጎት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |

**ስዕል 10.** የገበያ ጥናት የተሞላ መጠይቅ ማሳያ ምሳሌ

### ምሳሌ፥ የገበያ ጥናት መረጃ መሰብሰብያ መጠይቅ

ቀን፡ ______/__________/_______

የዞኑ ስም: ____________________ ክልል ________________

የገበያ መረጃ የሰበሰበው ስም (የአርሶ አደሮች ስም ዝርዝር) ወረዳ ________________

| የነጋዴው ስምና አድራሻ | ተፈላጊ ሰብል (ዝርያ አይነት) | አቅርቦት መጠንና ተፈላጊው ጥራትና መስፈርቶች | ከፍተኛ ገበዩአ ፍላጎት ያለበት (ወራት) | የምርትቱ በአንድ ጊዜ የሚቀርበው መጠንና ድግግሞሽ (እለታዊ፣ ሳንታዊ፣ ወዘት ) | የተመረተ በት ቦታ | የአንዱ ዋጋ (ብር/ኪግ) | የክፍያ መንገድ | የአከፋፈል ሁኔታ | የግብይት ተግዳሮቶች | ነጋዴው ከቡዱኑ ለመግዛት ያለው ፍላጎት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አቶ አብደላ ቃሲም (0917-ጆጆጆጆጆጆ) | ድንች (በለጠ) | ትልቅ ኮረት | የካቲት --- መጋቢት | 120 ኩንታል/በሳምንት (1ኩንታል=110ኪግ) | ወሊሶ | 3.6 | ከረዲት | በሳምንት ምርት ከተረከቡ በኋላ | ዝቅተኛ ጥራት (አበስበስ በሽታ) | በሱቃቸው ከቀረበላቸው ለግዛት ፍቃደና ናቸው |
| አቶ ከማል ሁሴን(0911-ጆጆጆጆጆጆ) | ድንች (በለጠ) | ከትናንሽ --- መካከልኛ መጠን | ከጥር --- የካቲት | 10 ኩንታል/በየቀኑ (1ኩንታል=100ኪግ) | ሸዋ ሮቢት | 2.5 | በከፍያ (ካሽ) | በምርት ማስረከብያ ሰዓት | ቀጣይነት ያለው አቅርቦት | ከማሳው ለመግዛት ፍቃደኛ ናቸው |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |

# የአርሶ አደሩን አቅም የማሳደግ ስልጠና

## 4. ደረጃ 4: የሚመረተው ሰብል መረጣ

| አራት (4) ደረጃዎች | ዋና ዋና ተግባራት (Activities) |
|---|---|
| 1. ግቡን እና ዓላማውን ለአርሶ አደርና ለአጋር አካላት ማስተዋወቅ | - የትውውቅ ፕሮግራም ማካሄድ |
| 2. የአርሶአደሮችን ግንዛቤ ማሳደግ | - አሳታፊ መሰረታዊ መረጃ የዳሰሳ ጥናት<br>- የገበያ ጥናት |
| 3. **የአርሶአደሮችን ውሳኔ ሰጭነት አቅም ማሳደግ** | - **የሰብል መምረጥ**<br>- የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለዮታ ፣ የሰብል አመራረት የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀትና ማለማመድ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የባለድርሻ አካላት መድረክ ማዘጋጀት |
| 4. የአርሶአደሩን እዉቀትና ክህሎት ማሳደግ | - በገበሬ ማሳ ላይ ስልጠና መስጠት<br>- የስርዓተ ፆታ ስልጠና በመስጠት ግንዛቤ ማሳደግ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የልምድ ልውውጥ እና ጉብኝት ማካሄድ<br>- የመስክ ቀን/ የልምድ ልውውጥ ጉብኝት |
| የክትትልና ግምገማ (አሳታፊ የመጨሻ ውጤት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድን ያካትታል) | |

አዚህ ጋር ነን

### 4.1. መግቢያ

ከሼፕ ዘዴ ውስጥ፣ የሰብል መረጣ ዓላማ፡- የአርሶ አደር ቡድኖች ማምረት የሚፈልጓቸውን ሰብሎች በገበያ ተፈላጊነት ያላቸው ሰብሎች በመለየት ለቡድን አባላት ለማሳወቅ ነው። የሰብል መረጣ በገበያ ጥናት መሰረት የአርሶ አደሮች ቡድን አባላት በገበያ ውስጥ ያሉትን እውነታዎች እንዲያውቁ የሚረዳ ነው፡- ከፍተኛ ፍላጎት ያለበትን ጊዜ፣ የጥራት መስፈርት፣ ከፍተኛ እና ዝቅተኛ ዋጋ እና የዋጋ መዋዠቅ የሚኖርበትን ጊዜ፣ የክፍያ ሁኔታዎች፣ ተግዳሮቶች ወዘተ የመሰሰሉትን የምርት የገበያ መስፈርቶች ያካትታል።

ከገበያ ጥናት በኋላ የሚያመርቱት ሰብል ከመወሰናቸው በፊት አርሶ አደሮች በቡድን ሆነው ለገበያው ማቅረብ የሚያስፈልጉ የተለያዩ የገበያ መስፈርቶችን በሚመለከት፣ የበፊቱ ልምዳቸውን፣ አሁን ያሉትን አጋጣሚዎች እና እድሎች ላይ ይወያያሉ።

### 4.2. አላማዎች

- ለገበያ ማቅረብ የሚያስፈልጉ የተለያዩ የገበያ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ሰብሎች በሚመለከት ከሌሎች ቡድን አባላት ጋር መረጃ ለመለዋወጥ፣
- በእያንዳንዱየገበያ ጥናት ያደረጉበትን ሰብል አብዛኞቹ አርሶ አደሮች እስኪረዱት ድረስ ወጪ እና ገቢ ስሌት/ትንተና ለማድረግ፣
- በገበያ ፍላጎት መሰረት የምርት እቅዳቸውንና የበፊቱ ልምዳቸው ላይ ለመወያየት።
- ሰብል ለመምረጥ አስፈላጊ የሆኑ የስነ-ምህዳር ተስማሚነት በተያያዘ ነባራዊ ሁኔታ ተገቢ ሙያዊ ምክር ለመስጠት፣
- በአቅራቢያቸው ካሉ ሌሎች ቡድን አባላት ጋር ልምድና መረጃ ለመለዋወጥ እንዲሁም ጠቃሚ ልምድ ለመቅሰም ይረዳል።

### 4.3. በአርሶ አደሮች ሰብል የመምረጥ አሰራር

- **አዘጋጅ/ ፈጻሚ አካል፡-** የልማት ሰራተኞችና የወረዳ ሆርቲካልቸር ቡድን
- **ተሳታፊዎች፡-** ሁሉም ተጠቃሚ አርሶ አደሮች ከትዳር አጋሮቻቸው ጋር ሰብሎችን መምረጥ እንዲችሉ ያበረታታል።

**ሰንጠረዥ 10.** የሰብል መምረጥ ልምምድ ናሙና እቅድ

| ሰዓት | ተግባራት |
|---|---|
| 2:30 - 3:00 | የተሳታፊዎችን ምዝገባ<br>የመክፈቻ ንግግር |
| 3:00 - 3:30 | ጠቃሚ የገበያ መረጃዎችና ልምዶች ከአርሶ አደር ተወካዮች ጋር መለዋወጥ |
| 3:30 - 5:20 | የሰብል መምረጫ ቅጽ ከተሳታፊ አርሶ አደር ተወካዮች ጋር በመሆን ቅጽ መሙላት |

| | |
|---|---|
| 5:20 - 5:30 | የወደፊት አቅጣጫ ማመላከት፣<br>የመዝግያ ንግግር |

#### 4.3.1. መሰብሰቢያ ቦታ

በተጠቃሚ አርሶ አደሮች አቅራቢያ የሚገኝ አማካይ ቦታ ፡- በዛፍ ጥላ ስር ወይም በገበሬዎች ማሰልጠኛ ማዕከል (FTC) ፣ትምህርት ቤቶች ፣በቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት ሊሆን ይችላል

### 4.4. በጀት ለማዘጋጀት የሚረዳ ናሙና ቅጽ

| የክፍያ ዓይነት | የቀን ብዛት | የሰው ብዛት |
|---|---|---|
| የምሳ አበል (ለወረዳ ባለሙያ) | 1 | 2 |
| የመጓጓዣ/ነዳጅ ወጪ (ለወረዳ ባለሙያ) | 1 | 2 |
| ቁሳቁስ፡- የሰብል መረጣ ቅጽ፣ ተገላጭ ቻርት፣ እስክርቢቶ) | 1 | 5 |

**ከላይ የተዘረዘሩት ቁጥሮችግምታዊ ማሳያ ስለሆኑ አስፈጻሚ አካላት የእያንዳንዱን ወረዳ ተጨበጭ ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት በትግበራ ጊዜ ማስተካከል ይችላሉ።*

### 4.5. አርሶ አደሮች ሰብል ሲመርጡ የምክክር መድረክ ዕቅድ ማዘጋጀት

- ሰብል ሲመርጡ የምክክር መድረክ የሚደረግበት ቀን ከአርሶ አደሮች ጋር በመመካከር መወሰን፤ ቀኑ ሲወሰን ሁሉም ተጠቃሚ አርሶ አደሮች ከትዳር አጋሮቻቸው ጋር እንዲገኙ የተመቸ ቢሆን ይመረጣል፡፡
- የምክክር ቀን ከመድረሱ በፊት ተገላጭ ቻርትና እስክርቢቶ ማዘጋጀት ፤የተዘጋጀውን ሰብል መረጣ ቅጽ በተገላጭ ቻርት ላይ መጻፍ ፡፡ (ለተጨማሪ ዕዝል 2.4 ተመልከቱ)

*ማስታወሻ፡- ወንዶች ሰብል ሲመርጡ ትርፋማነት ላይ ያመዘነ ውሳኔ ላይ የመድረስ እድላቸው ከፍተኛ ነው። ሴቶች በአንጻሩ ሁለንተናዊ መስፈርት፡ የልጆቻቸውን ምግብ ፍጆታ፣ የእንስሳት መኖ፣ ቀጣይነት ያለው ምርት መኖር/አለመኖር ከግምት ውስጥ በማስገባት የመወሰን ዕድላቸው ከፍተኛ ነው። ስለዚህ ሰብል ሲመረጥ ወንድና ሴት አርሶ አደሮች(የትዳር አጋሮች) በምክክር መድረኩ ላይ በመገኘት በጋራ ትክክለኛ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ወሳኝ ነው፡፡*




### 4.6. የአርሶ አደሮች ሰብል መረጣ የምክክር መድረክ አተገባበር

- የአርሶ አደር ተወካዮች የገበያ ጥናቱ ውጤት ለአባሎቻቸው መረጃ ያካፍላሉ፤
- የልማት ሰራተኞችና የአርሶ አደር ቡድን ተወካዮች የሰብል መረጣ ቅጽ ለመሙላት ያመቻቻሉ (ስዕል 11)፤

- የልማት ሰራተኞች የአርሶ አደር ቡድን አባላት በመረጡዋቸው ሰብሎች መካከል ያለውን ጥቅምና ጉዳት እንዲወያዩ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፤ የሚመረጠው ሰብል በአብዛኛው አባላት በቀላሉ ሊመረት የሚችል መሆን ይገባዋል። ማሳቸው ለሚመረጠው ሰብል ተስማሚ መሆንና ፣በጥሩ ዋጋ የግብርና ግብአቶች መገኘት ሰብሎች መምረጥ እንዲችሉ ያበረታታል።
- እያንዳንዱ አርሶ አደር ራሱ/ራሷ በሚመርጠዉ /በምትመርጠው ሰብል ላይ ድምጽ ይሰጣል/ትሰጣለች (አይን በመጨፈን ድምጽ የመስጠት አሰራር)። በ1ኛ እና 2ኛ ደረጃ የተመረጡ ሰብሎች ሰማቸውን በድምጽ መስጫ ወረቀቱ ላይ ይመዘገባል።
- በርካታ አርሶ አደሮች ልምድ የሌላቸው ከሆነ ግን፣ አይናቸውን ጨፍነው ወደ መሬት እንዲያጎነብሱ ይጠየቃሉ። ይህም ከመካከላቸው ከፍተኛ ተጽዕኖ ፈጣሪ የሆኑ አባላት (የቡድን መሪዎች፣ ነጋዴ ወይም የተማረ ሰው) ባልተማሩት ሰዎች ውሳኔ ላይ ተጽዕኖ እንዳያሳድሩ በማሰብ ነው። (ቀጥሎ የተሰጠው ስዕል ተመልከቱ)

**ለትግበራ የሚያግዙ ፍጮች: -አርሶ አደሮች ለምን በራሳቸው ሰብል ይመርጣሉ?**

የሰብል መረጣ ምክክር መድረክ አርሶ አደሮች በገበያ ጥናት ውጤት መሰረት እና በራሳቸው አቅም (እውቀትና ልምድ፣ በእጃቸው ያለ ሃብት፣ የስነ-ምዳር ተስማሚነትን፣ የገበያ ፍላጎት፣ ትርፋማነት ወዘተ) መሰረት የሚያመርቷቸውን ሰብሎች መምረጥ እንዲችሉ ያስችላል። በምክክር መድረኩ ተሳታፊዎች/ አርሶ አደሮች ምን ማምረት እንዳለባቸው ከመወሰናቸው በፊት በሚመረጡት ሰብሎች ዙርያ አስፈላጊ መረጃ ማወቅ አለባቸው።

## 4.7. በቀጣይ መሰራት ያለባቸው ተግባራት/ቀጣይ ዕቅድ

- ከአርሶ አደሮች ጋር በመወያየት የልማት ሰራተኞች ስልጠና የሚሰጡበት ቀን መወሰን።

## 4.8. ፎቶግራፍ



የአርሶ አደር ተወካዮች የገበያ ጥናት ውጤት በመግለጽ ላይ



አርሶ አደሮች ሚስጥራዊ ሰብል መረጣ ሲያካሂዱ



**ነጥቦች:- ስነ-ጾታን በማስረጽ ላይ**

በሰብል መረጣ ወቅት ሴቶች የማይሳተፉና በወንዶች ብቻ የሚካሄድ ከሆነ የሴቶች ዉሳኔ የመስጠትና የባለቤትነት ስሜት አይኖራቸዉም። ስለዚህ ሴቶች በሰብል መረጣ ወቅት እንዲገኙና ሀሳባቸዉን እንዲያካፍሉ ፣ ወንዶችም ከሴቶች ሃሳብ የመቀበልና በጋራ ተወያይቶ የመወሰን ልምድ እንዲዳብር ማበረታታት ያስፍልጋል።

በተጨማሪም በሰብል መረጣ ወቅት የሚመረጠዉን ሰብል ለማምረት የሚጠይቀዉ ጉልበት በሴቶች ላይ ተጨማሪ ጫና የሚያስክትል ከሆነ በምን መልክ ችግሩን/ጫናዉን መቀነስ እንደሚችሉ የጋራ ዉይት በማደረግ የመፍትሄ አቅጣጫ ማሰቀመጥ እንዳለባቸዉ ከግምት ዉስጥ መግባት አለበት።

## ድምጽ ከኢትዮጵያ መስክ

### የተለያዩ ሰብሎች ማምረት የገበያ ስጋትን ቀንሶልኛል



“ሼፕ ፕሮጀክት ለእኔና ለቡድኑ አባላት ያመጣልን ዋናዉ ቁልፍ ለዉጥ የተለያዩ የሰብል ዓይነትና ዝርያዎችን በመምረጥ ፤ በትከክለኛ ወቅት በማምረት በግብይት ላይ ሊያጋጥም የሚችለዉን የዋጋ ዉጣ ዉረድ ችግሮችን የማቃለያ መፍትሔ መሆኑን ግንዛቢያችን እንዲያድግ አድርጎልናል፡፡ የተለያዩ ሰብሎችን ማምረት የአንዱ ሰብል ገበያ ዋጋ ዝቅ ቢል በሌላ ሰብል ዋጋ ከፍ ማለት እንዲካካስ በማድግ ከኪሳራ ላይ እንዳንወድቅ የተሻለ አማራጭ መሆኑን ተምረናል፡ ፡”

**አቶ ኢሊያ እርጥባን.** (አርሶ አደር፤ ሶስቱ ጥርባ ቀበሌ ፤አንከሻ ወረዳ ፤ አዊ ዞን ፤አማራ ክልል)

## 4.9. ናሙና ቅጾች

**ስዕል 11.** የሰብል መረጣ ቅጽ

**ገበያ ተኮር የሆኑ ሰብሎች መምረጫ ቅጽ**

ቀን፡ ______/_________/_______
የዞኑ ስም: ____________________ ክልል _________________
የአርሶ አደሮች ቡዱን ስም፦ ____________________ ወረዳ _________________

| የሰብል ስም/ዝርያ | የአካቢው ነዋሪዎች ይጠቀሙታል ወይስ አይጠቀሙትም | ሰብሉን የማምረት ልምድ | የአተካከል ዚዴ/ ለመድረስ የሚያስፈልገው ጊዜ | ሰብሉን ለማምረት ዋና ዋና ተግዳሮቶች | በአማካይ ከ1ሄክታር ለገበያ ሊቀርብ የሚችል ምርት መጠን ( ኪግ) | የአንዱ መለኪያ ዋጋ (ብር/ኪግ) | ጠቅላላ ሽያጭ ገቢ በ1ሄክታር (ብር) | ጠቅላላ ማምረቻ ወጭ በ1ሄክታር (ብር) | የተጣራ ዓምታዊ ገቢ በ1ሄክ (ብር) | ዋና መሸጫ ገበያ (ዎች) | ገዥ የሚጠይቃቸው መስፈርቶች (ጥራት፣ ብዛት ----) | ጠቃሚ ማስታወሻ | የሰብሉ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | |

**ስዕል 12.** የሰብል መረጣ ቅጽ -ምሳሌ

**ምሳሌ** **ገበያ ተኮር የሆኑ ሰብሎች መምረጫ ቅጽ**

ቀን፡ ______/_________/_______
የዞኑ ስም: ____________________ ክልል _________________
የአርሶ አደሮች ቡዱን ስም፦ ____________________ ወረዳ _________________

| የሰብል ስም/ዝርያ | የአካቢው ነዋሪዎች ይጠቀሙታል ወይስ አይጠቀሙትም | ሰብሉን የማምረት ልምድ | የአተካከል ዚዴ/ ለመድረስ የሚያስፈልገው ጊዜ | ሰብሉን ለማምረት ዋና ዋና ተግዳሮቶች | በአማካይ ከ1ሄክታር ለገበያ ሊቀርብ የሚችል ምርት መጠን ( ኪግ) | የአንዱ መለኪያ ዋጋ (ብር/ኪግ) | ጠቅላላ ሽያጭ ገቢ በ1ሄክታር (ብር) | ጠቅላላ ማምረቻ ወጭ በ1ሄክታር (ብር) | የተጣራ ዓምታዊ ገቢ በ1ሄክ (ብር) | ዋና መሸጫ ገበያ (ዎች) | ገዥ የሚጠይቃቸው መስፈርቶች (ጥራት፣ ብዛት ወዘተ) | ጠቃሚ ማስታወሻ | የሰብሉ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ድንች/ጉደኔ | አዎን | አዎን | ሚያዝያ/ 4 ወራት | በሽታ (ሌት ብላይ | 5,000 | 5.0 | 25,000 | 7,610 | 17,390 | ገበያ ሀ እና ገበያ ለ | ገበያ ሀ፡ 50ኩ/ል በአርብ ቀን፣ ገበያ ለ፡ 1ኩ/ል በየቀኑ | የአከባቢው ገበያ ትንሽ ምርት ይገዛል | 1 |
| ሽንኩርት/ አዳማ ሬድ | አዎን | አዎን | ነሐሴ / 4 ወራት | በሽታ ( አመዳይ) | 4,000 | 12.0 | 48,000 | 6,230 | 41,770 | ገበያ ሐ እና ገበያ መ | ገበያ ሐ፡ 100ኩ/ል በማክሰኞ ቀን፣ ገበያ መ፡ 5ኩ/ል በየቀኑ | በገበያ ሐ ጠቆር ያለ ቀይ መልክና መጠኑ መካከለኛ ይመረጣል | 3 |
| ጥቅል/ጎመን ዩሮ | አዎን | አዎን | ጥቅምት / 4 ወራት | ተባይ (ክሽክሽ) | 10,000 | 2.7 | 27,000 | 5,290 | 21,710 | ገበያ ሀ እና ገበያ መ | ገበያ ሀ፡ 120ኩ/ል በእለተ ቅዳሜ፣ ገበያ መ፡ 5ኩ/ል በየቀኑ | | 2 |
| | | | | | | | | | | | | | |

# የአርሶ አደሩን አቅም የማሳደግ ስልጠና

ዝግጅት | መፈጸም | ክትትልና ግምገማ

## 5. ደረጃ 5: የገበያ ትስስር መድረክ

| አራት (4) ደረጃዎች | ዋና ዋና ተግባራት (Activities) |
|---|---|
| 1. ግቡን እና ዓላማውን ለአርሶ አደርና ለአጋር አካላት ማስተዋወቅ | - የትውውቅ ፕሮግራም ማካሄድ |
| 2. የአርሶአደሮችን ግንዛቤ ማሳደግ | - አሳታፊ መሰረታዊ መረጃ የዳሰሳ ጥናት<br>- የገበያ ጥናት |
| 3. **የአርሶአደሮችን ውሳኔ ሰጭነት አቅም ማሳደግ** | - የሰብል መምረጥ<br>- የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለየታ ፣ የሰብል አመራረት የጊዜ ሰለ ማዘጋጀትና ማለማመድ<br>- **(እንደ አስፈላጊነቱ) የባለድርሻ አካላት መድረክ ማዘጋጀት** |
| 4. የአርሶአደሩን እዉቀትና ክህሎት ማሳደግ | - በገበሬ ማሳ ላይ ስልጠና መስጠት<br>- የስርዓተ ፆታ ስልጠና በመስጠት ግንዛቤ ማሳደግ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የልምድ ልውውጥ እና ጉብኝት ማካሄድ<br>- የመስክ ቀን/ የልምድ ልውውጥ ጉብኝት |
| የክትትልና ግምገማ (አሳታፊ የመጨሻ ውጤት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድን ያካትታል) | |

እዚህ ጋር ነን

### 5.1. መግቢያ

በኢትዮ-ሼፕ ፕሮጀክት የገበያ ትስስር ፎረም/መድረክ የሚዘጋጀው አርሶ አደሮች ሰብል ከመረጡ በኋላ ሲሆን በአርሶ አደሮቹና በገበያ የዕሴት ሰንሰለቱ ላይ ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት (ግብዓት አቅራቢዎች፣ ነጋዴዎች፣ ደላሎች፣ አቀናባሪዎች፣ ማህበራት፣ ብድር አቅራቢ ተቋማት እና የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት) ጋር ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር ነው:: የባለድርሻ አካላት ፎረሙ በገበያ ትስስር ዙሪያ በአምራቾችና በተቀባዮች መካከል ቀጥተኛ ትስስር እንዲደረግ እና በሆርቲካልቸር ግብይት ዙሪያ (የግብዓት እና የምርት) አሁን ያለውን የግብይት ሂደት በማሻሻል እና አዳዲስ እድሎች ለመፍጠር ይጠቅማል።

### 5.2. የፎረሙ ዓላማዎች

- በተጠቃሚ አርሶ አደር ቡድኖችና በባለድርሻ አካላት መካከል ግንኙነት ለመፍጠር/ ማመቻቸት።
- በተጠቃሚ አርሶ አደር ቡድኖችና በባለድርሻ አካላት መካከል የንግድ (የግብዓት/የምርት) ትስስር ለማጠናከር ።
- በወረዳ ባለሙያዎች አመቻችነት በማበረታታት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የገበያ ትስስር ፎረም /መድረክ በማመቻቸት አዳዲስ ዕድሎች እንዲፈጥሩ እና በአርሶ አደሮችና በገበያ ባለድርሻ አካላት መካከል ያለው የግብይት ስርዓት ማጠናከር ይጠቅማል።

### 5.3. የመድረኩ ዝግጅት

#### 5.3.1. ተሳታፊዎች

- አዘጋጅ/ፈጻሚ አካል፡ የክልል ግብርና፣ ህብረት ስራ ማህበር፤ የዞን ንግድ ጽ/ቤትና የወረዳ ሆርቲካልቸር ቡድን
- ክትትልና ድጋፍ፡ የክልል ቡድን
- **<u>ተሳታፊዎች:</u>**

**ፈዴራል**:- የሆርቲከልቸር ሰብሎች ልማት ዋና ሰራ አስፈጻሚ ፡ የግብዓት ሰራ አስፈጻሚግብይት ክፍል።

**ክልል**:- የህብረት ስራ ማህበር ማደራጃና ማስፋፊያ ሀላፊ/ምክትል ሀላፊ፣ የህብረት ስራ ማህበር ማደራጃና ማስፋፊያ ጽ/ቤት ተወካዮች፣ የንግድ ጽ/ቤት ተወካዮች፣ የግብርና ግብዓት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን፣ የዓምራች ማህበራት፣ ዩንየኖችና ግብዓት አቅራቢ ነጋዴዎች ተወካዮች።

**ዞን**:- የግብዓት አቅርቦት ባለሞያ፣ ህብረት ስራ ማህበር ማደራጃና ማስፋፊያና ንግድ ተወካዮች።

**ወረዳ**:- ከግብዓት አቅርቦት ባለሙያ፣ ከህብረት ስራ ማህበርማደራጃና ማስፋፊያ ና ከንግድ ተወካዮችና ወረዳ የሆርቲካልቸር ልማት ቡድን።

**ቀበሌ**:- አንድ (1) የቀበሌ አመራር ከእያንዳንዱ የፕሮጀክቶች አካባቢ።

### 5.3.2. የሚወስደው ጊዜ

አንድ (1) ቀን

**ሰንጠረዥ 11**. የገበያ ትስስር መድረክ መርሀ-ግብር (ናሙና)

| ሰዓት | ተግባራት |
|---|---|
| 2:30 - 3:00 | የተሳታፊዎች ምዝገባ |
| 3:00 - 3:10 | የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር |
| 3:10 - 3:40 | የአርሶ አደር ቡድኖች መረጃ መለዋወጥ (የግብኣት ፍላጎት፣ የማምረት አቅም) |
| 3:40 - 4:10 | የተሳታፊ ነጋዴዎች መረጃ መለዋወጥ (ግብዓት አቅራቢዎች፣ ጅምላ ሻጮች፣ ህብረት ስራ ማህበራት፣ ...ወዘተ) |
| 4:10 - 4:30 | የሻይ ዕረፍት |
| 4:30 - 4:45 | ከበፊቶቹ ቡድኖች የፕሮጀክት ተግባራት ውጤቶች መሰረት ጥሩ ልምድ ማጋራት |
| 4:45 - 6:00 | የቡድን ውይይት |
| 6:00 - 6:20 | የቡድን ውይይት ለተሳታፊዎች ማቅረብ |
| 6:20 - 6:30 | የመዝጊያ ንግግር |
| 6:30 - | የምሳ ዕረፍት |

### 5.3.3. መሰብሰብያ ቦታ

የመሰብሰቢያ ቦታ ሲዘጋጅ ለተሳታፊዎች ምቹ መሆኑን፡ ማለትም ከርቀት፣ ወጭ፣ አንጻር ታይቶ ቢሆን። የመሰብሰብያ አዳራሽ መኖር (ከተቻለ የመንግስት አዳራሽ ቢሆን ይመረጣል)።

## 5.4. በጀት ለማዘጋጀት የሚረዳ ናሙና ቅጽ

| የክፍያ ዓይነት | የቀን ብዛት | የሰው ብዛት |
|---|---|---|
| የምሳ አበል (ለአርሶ አደሮች) | 1 | 16 |
| የምሳ አበል (ለልማት ሰራተኞች) | 1 | 12 |
| የምሳ አበል (ለወረዳ ባለሙያዎች) | 1 | 8 |
| የምሳ አበል (ለዞን ባለሙያዎች) | 1 | 2 |
| የምሳ አበል (ለክልል ባለሙያዎች) | 1 | 1 |
| የመጓጓዣ ወጪ (የህዝብ ትራንስፖርት) (ለወረዳ ባለሙያ፤ለልማት ሰራተኞች ፣የአርሶ አደሮች ተወካዮች፤ ከእያንዳንዱ ቦታ]) | 1 | 36 |
| የስልጠና ቦታ እና ቁሳቁሶች | 1 | 1 |
| ነዳጅ ለክልል መኪና | 1 | 1 |
| ነዳጅ ለዞን መኪና | 1 | 1 |
| የምሳ ፕሮግራም | 1 | 50 |

** ከላይ የተዘረዘሩትን ቁጥሮች ግምታዊ ማሳያ ስለሆኑ አስፈጻሚ አካላት የእያንዳንዱን ወረዳ ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት በትግበራ ጊዜ ማስተካከል ይችላሉ።*

## 5.5. የምክክር መድረክ የዝግጅት ሂደት

### 5.5.1. ከባለድርሻ አካላት ጋር የቅድመ-ዝግጅት ስብሰባ ማካሄድ

- የክልልና ዞን ባለድርሻ አካላት ከወረዳ ጋር በመናበብ የመድረኩ ተግባርና ኃላፊነት ክፍፍል ያደርጋሉ፣
- ግብርና ልማት የክልል፣ ዞን እና ወረዳ ቡድን (የባለሙያዎች ቡድን) ድጋፍ መሰረት ባድርሻ አካላት የራሳቸው የቢዝነስ እቅድ መግለጫ ሰነድ ያዘጋጃሉ።

- ከልማት ሰራተኞች በሚሰጣቸው ድጋፍ መሰረት ተጠቃሚ የአርሶ አደር ቡድኖች የቡድናቸውን ሁኔታ የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ ያዘጋጃሉ፣
- የባለሙያዎች ቡድን (ክልል፣ ዞን እና ወረዳ) በምክክር መድረኩ ምን አይነት መረጃ መቅረብ እንዳለበት ለባድርሻ አካላት ባሉበት አድራሻ ማብራሪያ ይሰጣል፣
- በወረዳ ባለሞያና ቀበሌ ልማት ሰራተኞች ድጋፍ መሰረት አርሶ አደሮች የቡድናቸውን ዝርዝር መረጃ ለፈጻሚ ባለድርሻ አካላት እንዲያጋሩ/እንዲያዘጋጁ ይነገራቸዋል፣
- የዞን እና ወረዳ ባለሙያዎች ለምክክር መድረኩ አመቺ ቦታ እና ጊዜ በመለየት ለባለድርሻ አካላት እንዲያውቁት ያደርጋሉ።
- የክልል፣ ዞን እና ወረዳ ባለሞያዎች በባለድርሻ አካላት የተዘጋጀውን ዝርዝር መረጃ ይሰበስባሉ።

### 5.5.2. ከተጠቃሚዎች ጋር ስብሰባ በማካሄድ በመድረኩ የሚሳተፉ የአርሶ አደሮች ተወካዮች መምረጥ

- የልማት ወኪሎች በመድረኩ የሚሳተፉ አርሶ አደሮች በተመለከተ ዝርዝር ማስታወሻ በማዘጋጀት መረጃን በሰፊው ለማሰራጨት እና በቡድኖቹ አባላት ውይይት በማመቻቸት፣ በገበያ ተዋንያን ዙርያ የሚያውቁትን ነገር እና ተወካዮቻቸው ምን አይነት መረጃ መሰብሰብ እንደሚፈልጉ መለየት፣
- የባለሙያዎች ቡድን (ክልል፣ ዞን እና ወረዳ) የባለድርሻ አካላትን መረጃ ተዘጋጅቶ የምክክር መድረክ ቀን ከመድረሱ ቢያንስ ከሳምንት በፊት(ለአዘጋጁ) መቅረብ አለበት፣
- ተጠቃሚ አርሶ አደሮች በእነዚህ ስብሰባዎች/መድረኮች የሚሳተፉ ተወካዮቻቸውን በዲሞክራሲያዊ መንገድ ይመርጣሉ። የሚመርጧቸውን አባላት ብዛት እስከ 4 ሰዎች (2 ወንድ፡ 2 ሴት) የጾታ ተዋጽኦ ታሳቢ በማድረግ ባለአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮችና የውሃ ተጠቃሚዎች ቡድን አባላት ናቸው።

### 5.5.3. ሌሎች ዝግጅቶች

- በክልል፣ ዞን እና ወረዳ ባለሙያዎች ለምክክር መድረክ ቦታ ያዘጋጃል፣
- በክልል, ዞን እና ወረዳ ባለሙያዎች የምክክር መድረክ ዝርዝር የጊዜ ሰሌዳ ያዘጋጃሉ (ዝርዝሩን በ ሰንጠረዥ 11 ተመልከቱ)፣
- አስፈላጊ ጽሁፎች፣ ቅጾች እና የተሳታፊ አርሶ አደር ቡድኖች እና የባለድርሻ አካላትን መረጃ ማደራጀት (እባክዎን ዕዝል 2.5 ይመልከቱ)።

## 5.6. የገበያ ትስስር ፎረም እንዴት በአግባቡ መተግበር ይቻላል?

### 5.6.1. የባለድርሻ አካላት የግንኙነት መድረክ/ ፎረም ማመቻቸት፡፡

የሚከተሉት ተግባራት መመቻቸታቸውን ማረጋገጥ፡-

- **የተሳታፊዎች አቀማመጥ**:- የተሳታፊዎች አቀማመጥ በተቻለ መጠን እያንዳንዱ ሰው የብዙ ሰዎችን ፊት ለመመልከት በሚችልበት ሁኔታ መቀመጫዎቹ መዘጋጀት አለባቸው። ለምሳሌ:- በተሳታፊዎች ቁጥር መሰረት፣ በመማሪያ ክፍል መልክ ወይም በክብ አደራደር ሊሆን ይችላል፡፡
- አዘጋጆች የተመደበው የጊዜ ሰሌዳን በመከተል በአግባቡ በመጠቀም ለውይይት የሚሆን ሰዓት በመስጠት ዕቅዱን መተግበር ይኖርባቸዋል፡፡
- **የተሳታፊዎችን መረጃ ማሰባሰብ** ፡- አርሶ አደር ቡድኖች እና ባድርሻ አካላት ዝርዝር መረጃ ይዘው አንዲመጡ ቀደም ብሎ ሊነገራቸው ይገባል።
- የፎረሙ ተሳታፊ የአርሶ አደር ቡድን ተወካዮች ከሌሎች ቡድኖች በውይይት ጊዜ በንቃት እንዲሳተፉ ከልማት ሰራተኞች ድጋፍ ማድረግ ይጠበቃል። ይህ ሂደት አርሶ አደሮች አዳዲስ አሰራሮችንና ቴክኖሎጂዎችን ለመቀበል ፈጣን ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ እና የቢዝነስ ትስስር/ድርድር ጉዳዮች ድጋፋዊ ክትትል ለማድረግ ያግዛል።

### 5.6.2. የአርሶ አደር ቡድን አውደ- ትርዒት/ ናሙና ማሳያዎች

- የአርሶ አደር ተወካዮች፣ ማለትም ወደ ገበያ ትስስር ፎረም የሚጋበዙ አርሶ አደሮች ከሚያመርቱት የአትክልት ናሙና ይዘው እንዲመጡ ይበረታታሉ። ይህ መድረክ ለተሳታፊ ባለድርሻዎች ምርቶቻቸውን ለማሳየት እድል ይፈጥራል። ለምርት ተቀባዮች (ጅምላ ሻጮች) እና አርሶ አደሮች መካከል ጠለቅ ያለ ውይይት ለማድረግ እና መረጃ ለመለዋወጥ ይመቻቻል።
- ጅምላ ሻጮች በተለይ፣ የሚፈልጉት ምርት ላይ የጥራት (እና ብዛት) መስፈርቶች አርሶ አደሮች ባቀረቡት ማሳያ ናሙና አትክልቶች

መሰረት ማብራሪያ ይሰጣሉ።

**የትግበራ ፍንጭ:- የገበያ ትስስር ፎረም ትግበራ ለምን?**
የገበያ ትስስር ፎረም በአርሶ አደሮች እና ባለድርሻ አካላት መካከል በቀጥታ ውይይት ለማድረግ እና መረጃ በመለዋወጥ ለቀጣይ ግንኙነት መንገድ ይከፍትለታል።

## 5.7. ከፎረሙ ውይይት ቀጥሎ መሰራት ያለባቸው ተግባራት

- በገበያ ትስስር መድረኩ የተሳተፉትን አርሶ አደሮች ከመድረኩ የታዘቡትን መረጃ ለሌሎች አርሶ አደሮች ማስተላለፍ ይጠበቅባቸዋል።
- በቀጣይነት ያለው ድጋፋዊ ክትትል፣ አንዳስፈላጊነቱ፣ በአርሶ አደሮች ቡድኖችና ባለድርሻ አካላት መካከል የጋራ መድረክ በመፍጠር ያላለቁ ጉዳዮችን ዳር ለማድረስ ተገቢ ትኩረት ይደረጋል። በዚህ የክትትል መድረኮች የልማት ሰራተኞችና የአርሶ አደር ቡድን ተወካዮች በአንድ ላይ አንዲገኙ ይመከራል።
- በሌላ በኩል ህበረት-ስራ ማህበራት ጽ/ቤትና ንግድ ጽ/ቤት ለአምራች አርሶ አደሮች አስፈላጊ ድጋፍ በመስጠት ከግል ኩባንያዎች፣ ለምሳሌ ከምግብ አምራች ኩባንያዎች ጋር ትስስር መፍጠር ይጠበቅባቸዋል።

## 5.8. ፎቶግራፍ




ግብዓት አቅራቢዎች ምርቶቻቸውን እያስተዋወቁ




ጅምላ ሻጬችና አርሶ አደሮች የንግድ ውይይት ሲያደርጉ



**ነጥቦች፡- የስነ-ጾታ ስርፀት ላይ**

በገበያ ትስስር ፎረም/መድረክ ላይ ብዙ ጊዜ ሴቶች አይገኙም ። ቢገኙም ቁጥራቸዉ ዉስን ሲሆን በዉይይቱ ላይ ከወንዶች ጋር ሃሳብ የመስጠት ተሳተፎ አያደርጉም፡፡ ይህ ደግሞ ስለ ሆርቲካልቸር ሰብሎ ግብዓቶች አቅረቦት እና ምርት ግብይት በቂ መረጃ እንዳይኖራቸዉ ያደርጋል፡፡ በግብይት ወቅት ከገበያ ሸሪኮቻቸዉ ጋር የመደራደር ልምድ አይኖራቸዉም፡፡ ስለዚህ ሴቶች ከአጋር አካላት ጋር በሚኖረዉ የገበያ ትስስር ዉይይት መደረክ ላይ ቁጥራቸዉ ከፍ እንዲል ማድረግ፣ የሚገኙትም ሃሳባቸዉን ከወንዶች በእኩልነት ስሜት የማካፍልና ሃሳብ የመለዋወጥ መብት እንዳላቸዉ የማሰረዳትና የማበረታታት ስራ




**ስዕል 13.** እቶ ፍቃዱ በገበያ ትስስር ፎረም የገበያ ዕድል አግኝተዋል *(ከአርሶ አደሮች ድምፅ, 2013 ዓ.ም። የተወሰደ)*

# 6. ደረጃ 6: ኢትዮ-ሸፕ ቴክኒካዊ የአሰልጣኞች ስልጠና (ቴ.አ.ስ) (ሸፕ ቴክኒካዊ አ.ስ)

| አራት (4) ደረጃዎች | ዋና ዋና ተግባራት (Activities) |
|---|---|
| 1. ግቡን እና ዓላማውን ለአርሶ አደርና ለአጋር አካላት ማስተዋወቅ | - የትውውቅ ፕሮግራም ማካሄድ |
| 2. የአርሶአደሮችን ግንዛቤ ማሳደግ | - አሳታፊ መሰረታዊ መረጃ የዳሰሳ ጥናት<br>- የገበያ ጥናት |
| 3. **የአርሶአደሮችን ውሳኔ ሰጭነት አቅም ማሳደግ** | - የሰብል መምረጥ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የባለድርሻ አካላት መድረክ ማዘጋጀት<br>- **የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለየታ ፣ የሰብል አመራረት የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀትና ማለማመድ** |
| 4. **የአርሶአደሩን እዉቀትና ክህሎት ማሳደግ** | - **በገበሬ ማሳ ላይ ስልጠና መስጠት**<br>- **(እንደ አስፈላጊነቱ) የልምድ ልውውጥ እና ጉብኝት ማካሄድ**<br>- የስርዓተ ፆታ ስልጠና በመስጠት ግንዛቤ ማሳደግ<br>- የመስክ ቀን/ የልምድ ልውውጥ ጉብኝት |
| የክትትልና ግምገማ (አሳታፊ የመጨሻ ውጤት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድን ያካትታል) | |

ቴ.አ.ስ

አዚህ ጋር ነን

## 6.1. መግቢያ

ኢትዮ-ሸፕ ቴክኒካዊ የአሰልጣኞች ስልጠና (ቴ.አ.ስ) ለአሰልጣኞች የሚሰጥ ስልጠና ነው። ሰልጣኞች ደግም የሆርቲካልቸር ባለሞያዎች እና ልማት ሰራተኞች (የቀበሌ ግብርና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች)፣ ማለትም አውቀትና ክህሎት ለአነስተኛ ሆርቲካልቸር አምራች አርሶ አደር ቡድኖች ለማስተላለፍ ሃላፊነት ያለባቸው ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው:: ባለሙያዎቹ በተራቸው የቀሰሙትን ዕውቀትና ክህሎት ለፕሮጀክቱ ተጠቃሚ አርሶ አደሮች በሚረዱት ቋንቋ እና በቀላልአቀራረብ ማስተላለፍ ይጠበቅባቸዋል።

ኢትዮ-ሼፕ ቴክኒካዊ የአሰጣኞች ስልጠና (ቴ.አ.ስ) የወሰዱ የልማት ሰራተኞች ተጠቃሚ አርሶ አደሮችን የሆርቲካልቸር ሰብሎችን በማምረትና ግብይት ላይ ትኩረት ያደረገ ስልጠና ይሰጣሉ ።

ሼፕ ቴ.አ.ስ የአነስተኛ ማሳ ባለቤት አርሶ አደሮች ፍላጎት መሰረት ያደረገ እውቀትና ክህሎት በማሳደግ የተመረጡ ሰብሎችን ለማምረት በመስክ በተግባር የተደገፈቴክኒካዊ ስልጠናዎች ላይ ትኩረት ያደረገ አርሶ አደሮች የሚያጋጥማቸውን ተግዳሮት መፍታት ላይ ትኩረት ያደረገ ነው።

## 6.2. የሼፕ ቴክኒካዊ የአሰልጣኞች ስልጠና (ቴ.አ.ስ) ዓላማዎች

- የአሰልጣኞች ሙያዊ (ቴክኒክ) ስልጠናን ማካሄድ አላማው የተጠቃሚ አርሶ አደሮችንና ቡድኖችን የስልጠና ፍላጎት ለማርካት ይቻል ዘንድ የወረዳ ባለሙያዎች እና የልማት ሰራተኞች አስፈላጊ እውቀትና ክህሎትን ማስጨበጥ ነው።
- በተመረጡ ሰብሎች ላይ በመስክ ተግባራዊ(ቴክኒካዊ) ስልጠናዎች እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻል መረጃ ይሰጣል፣ ። የውስጥ ፍላጎት መሰረት ያደረገ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ያቀርባሉ።
- በተመረጡ ሰብሎች ላይ መሰረታዊ የአመራረት ዘዴዎችን ማስተማር።

## 6.3. የአሰልጣኞች ስልጠና አተገባበር

### 6.3.1. ተሳታፊዎች

**አዘጋጅ**: -ክልል ግብርና ቢሮ እና ዞን ግብርና መምሪያዎች

**ክትትልና ድጋፍ**: - ክልል ግብርና አማካሪ እና ሆርቲካልቸር ባለሙያ

**ተሳታፊዎች**: -

**በክልል**:- ከሆርቲካልቸር፣ አግሮኖሚ፣ ሰብል ጥበቃ፣ ድህረ-ምርት፣ኤክስቴንሽን ተወካዮች፣

**ዞን:-** ከሆርቲካልቸር፣ አግሮኖሚ፣ ሰብል ጥበቃ፣ ድህረ-ምርት፣ እና ኤክስቴንሽን ተወካዮች፣

**ወረዳ**: ከሆርቲካልቸር፣ አግሮኖሚ፣ ሰብል ጥበቃ፣ ድህረ-ምርት፣ እና ኤክስቴንሽን ባለሞያዎች፣

**ቀበሌ**: - ከሁሉም ቀበሌዎች የልማት ሰራተኞች እና የቀበሌ ግብርና ጽ/ቤት ሀላፊዎች።

**የሚወስደው ጊዜ**

ሶስት (3ቀን) በልማት ሰራተኞች የመኖሪያ አካባቢ፡-) ስልጠና መስጠት። (ስለ ፕሮግራሙ ተያያዥ ሰንጠረዥ 12 ይመልከቱ)

### 6.3.2. በታ

የአሰልጣኞች ስልጠናን ለማካሄድ በታ ሲዘጋጅ ለተሳታፊዎች ምቹ መሆኑን ማረጋገጥ። ማለትም ከርቀት፣ ከወጪ፣ የመሰብሰብያ ክፍሎች መኖር፡ የመኝታ አገልግሎት መኖር፣ እንዲሁም በተመረጡ ሰብሎች ላይ በመስክ ተግባራዊ(ቴክኒካዊ) ስልጠናዎች ለመስጠት አመቺነት አንጻር መወሰን አለበት። አጋዥ የሆኑትን እንደ ግንባር ቀደም አርሶ አደሮች፣ የችግኝ ጣቢያ እና እርሻ ምርምር ማዕከል መኖራቸውን ከግምት በማስገባት ይመቻቻል።

**ሰንጠረዥ 12**. የአሰልጣኞች ስልጠናን ለማካሄድ ናሙና የጊዜ ሰሌዳ

| ቀን | 1ኛ ቀን | 2ኛ ቀን | 3ኛ ቀን |
|---|---|---|---|
| ተግባራት | 2:30-3:00 የተሳታፊዎች ምዝገባ<br>3:00 የመክፈቻ ንግግር (በተቋም ሃላፊ )<br>-3:00-4:00 የስልጠናው አላማዎች እና መግቢያ<br><br>4:00-4:30 የሻይ ዕረፍት<br>4:30-6:30<br>**ክፍለ-ጊዜ:**<br>የሆርቲካልቸር ሰብሎች አመራረትና የድህረ ምርት አያያዝ ዘዴ ጠቅላላ ዕዉቀት (አሆሰአ እና ድምአቴ) ጂ-24<br>6:30-7:30 የምሳ ዕረፍት<br>7:30-8:00 ትምህርታዊ ገለጻ:- የተፈጥሮ ማዳበሪያ አሰራር<br>8:00-9:00<br>**ተግባራዊ ልምምድ:- የሳሙና ውህድና የቦካሺ የተፈጥሮ ማዳበሪያዎች አዘገጃጀት**<br>9:00-9:30 የሻይ እረፍት<br><br>9:30-11:00 የተቀናጀ የተባይና በሽታ ቁጥጥር ዘዴ | 2:00 የተሳታፊዎች ምዝገባ<br>2:30-3:30 **ትምህርታዊ ገለጻ**<br>የሰብል የማምረቻ የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጃትና የችግር ትንተና<br>3:30-4:00 **ተግባር: -የቡድን ስራ-** በያንዳንዱ ወረዳ ተከፍለው የምርት የጊዜ ሰሌዳ ቅጽ መሙላት።<br>4:00-4:30 የሻይ እረፍት<br>4:30-5:30 የችግር ትንተና<br>5:00-6:30: የቡድን ፕረዘንቴሽን<br>6:30-7:30 የምሳ እረፍት<br>7:30-8:30 የጀላቲን ውህድ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ማዘጋጀት<br><br>9:00-9:30 የሻይ ዕረፍት<br>9:30-11:00 ትምህርታዊ ገለጻ:- ቀይ ሽንኩርት ማምረት ተግባራዊ ቴክኒኮች | 2:00 የተሳታፊዎችን ምዝገባ<br>2:30-4:30 **ትምህርታዊ ገለጻ**<br>8:30-3:30 ነጭ ሽንኩርት<br>3:30-4:30: ድንች<br><br>4:30-5:00 የሻይ እረፍት<br>5:00-6:30 **ትምህርታዊ ገለጻ**<br>አበሻ ጎመን<br><br>6:30-7:30 የምሳ እረፍት<br>7:30-8:00 **ትምህርታዊ ገለጻ**<br>የድርጊት መርሀ-ግብር ማዘጋጀት<br>8:00-9:00 የድርጊት መርሀ-ግብር ማዘጋጀት<br>9:00-9:30 የሻይ እረፍት<br>9:30-10:00 ፕረዘንተሽን<br>10:00-10:30 የመዝጊያ ስነ-ስርአት<br>10:30 የመዝጊያ ንግግር |

## 6.4. በጀት ለማዘጋጀት የሚረዳ ናሙና ቅጽ

| የክፍያ ዓይነት | የቀን ብዛት | የሰው ብዛት |
|---|---|---|
| ውሎ አበልና እና የመጓጓዣ ወጪ (ለልማት ሰራተኞች) | 3 | 18 |
| ውሎ አበል እና የመጓጓዣ ወጪ (ለወረዳ) | 3 | 24 |
| ውሎ አበል እና የመጓጓዣ ወጪ (ለዞን) | 3 | 5 |
| ውሎ አበል (ለክልል) | 3 | 5 |
| ነዳጅ ለክልል መኪኖች | 3 | 1 |

## 6.5. የአሰልጣኞች ስልጠና እንዴት ይዘጋጃል?

የዞን ሆርቲካልቸር ባለሙያዎች የተጠቃሚ አርሶ አደሮችና ቡድኖችን የስልጠና ፍላጎት መሰረት በማድረግ ጠቃሚና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የስልጠና ርዕሶችን ይመርጣሉ። የስልጠና ርዕሶችን በመለየት ሂደት አርሶ አደሮች የስልጠና ፍላጎትና ክፍተት ከተመረጡ ሰብሎች አንጻር ማገናዘብ ይጠበቃል።

የአተገባበር ሂደቱ እንደሚከተለው ተገልጿል

ቀደም ብሎ በአርሶ አደሮች የቀረበው የገበያ ጥናት እና የሰብል መረጣ ውጤት ለማወቅ የጥናት ቅጾችን ደግሞ ማጥናት/ ማገናዘብ፡

ከተመረጡ ሰብሎች አንጻር ዋና ዋና ተግዳሮቶች መለየት፣

ከተመረጡ ሰብሎች አንጻር ለሚታዩ ችግሮች የመፍትሄ አማራጭ መለየት፣

ለሚታዩ ችግሮች ይበልጥ ተገቢ መፍትሄ በመለየት የአርሶ አደሩን ችግር በራሱ እንዲፈታና አዲስ ክህሎት ወይም ሌሎች የባህሪ ለውጦችን ማየት የሚያስችሉ የስልጠና ርዕሶችን ይመረጣሉ።

የስልጠና ርዕሶች የሚከተሉትን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል፡-

**መግቢያ**

ሆርቲካልቸር ሰብሎች አመራረት መሠረታዊ መርሆዎች፣

የሆርቲካልቸር ሰብሎች አመራረትና የድህረ ምርት አያያዝ ዘዴ ጠቅላላ እውቀት (አሆሰአ እና ድምአቴ) ጂ-24 ይመለከቱ

በተመረጡ ሰብሎች ላይ ያተኮሩ የአመራረት ቴክኒኮች ስልጠና

ስርዓተ-ምግብና ሥርዓተ-ፆታ በሆርቲካልቸር ሰብሎች ልማት ውስጥ የሚያካትት ስልጠና፣

የኢትዮ-ሸፕ ስልጠና ማንዋሎችና የገበያ መር ኤክስቴንሽን አገልግሎት መተግበሪያ መሳሪያዎች (ካሚሺባይ) አጠቃቀም፣

የስልጠና ርዕሶች ከተመረጡ በኋላ በክልል እና በዞን ሆርቲካልቸር ባለሙያዎች የሚከናወን ተግባር ይሆናል። **እንዲሁም የስልጠና አጋዥ ጽሁፎችና ቁሳቁሶች/ መሳሪያዎች ዝግጅት፡** የአሰልጣኝ ማስተማሪያ ጽሁፎች (ፕረዘንቴሽን)፣ ለሰልጣኝ የሚሰጥ ጽሁፍ (ሀንድአውት)፣ የክህሎት ልምምድ ሠንጠረዥ/ፎርማት እና የሰርቶ ማሳያ ማቴሪያሎች/ግብዓቶችን ማዘጋጀት፣ ወ.ዘ.ተ በዚህ ተግባር ይጠቃለላል።

**የስልጠና ፕሮግራም ማዘጋጀት** (ናሙና ማሳያ ቅጽ በሰንጠረዥ 12 ላይ ይመልከቱ)፣

በተመረጠው ርዕስና የስልጠና ዘዴ መሰረት አመቻች/አሰልጣኝ መምረጥ።

**የስልጠና ቦታዎች ዝግጅት፤** ከስልጠናው ቀን አስቀድሞ ከሶስት(3) ሳምንታት በፊት መጠናቀቅ አለበት። በተለይ መኝታ፣ የስልጠና ክፍሎች፣ የምግብ አቅርቦት፣ በመስክ የተግባር ሥራዎችን ማሳያ በበቂ ሁኔታ መኖራቸው ማረጋገጥ።

**ለተሳታፊዎች ጥሪ ማስተላለፍ፡** ከስልጠና ቀን ከሁለት(2) ሳምንታት ቀደም ብሎ ተሳታፊዎችን **በደብዳቤ ጥሪ ማድረግ።** በደብዳቤው መካተት ካለባቸው ነጥቦች መካከል፡- የስልጠናው ዓላማ/አስፈላጊነት፣ ቦታና ቀን፣ የተሳታፊዎችን ምዝገባ ቀን፣ የትራንስፖርትና የቆይታ ጊዜ ፣ የጊዜ ሰሌዳ ዕቅድ ጠቅሶ ለተሳታፊዎች ጥሪ ማስተላለፍ አስፈላጊ ነው፡፡

የስልጠና አጋዥ ማቴሪያሎች መዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ (ናሙና ማሳያ በዕዝል2.6 ላይ ይመልከቱ)።

ዞን ሆርቲካልቸር ባለሙያዎች የስልጠና አጋዥ ጽሁፎችና ማንዋሎች ለሰልጣኝ የሚሰጥ ጽሁፍና የመሳሰሉትን ያቀርባሉ፣

የስልጠና ጽሁፎችና ቁሳቁሶች ስልጠናውም በተያዘለት ወረዳና ቀበሌ ነባራዊ ሁኔታዎች መሰረት ክለሳ ይካሄዳል፡፡ ዝርዝር የስልጠና ጽሁፎችና ቁሳቁሶች ናሙና ከዕዝል 2.6. ላይ ይመልከቱ)።

## 6.6. የስልጠናው አተገባበር

ይህን ስልጠና ማስፈጸም የክልል እና ዞን የአመራር ቡድን ሀላፊነት ይሆናል፡፡።

*ኣስታውሱ፡-* የቀበሌ የልማት ሰራተኞች፤ አርሶ አደር ቡድኖች በመረጧቸው የሰብል አይነቶች በማቀናጀት በካሚሺባይ ስልጠና ሰዓት በቡድን ይከፋፈላሉ። የተዘጋጁትን የስልጠና አጋዥ ማቴሪያሎች ይሰራጫሉ።

> **ለትግብራ ፍንጭ:- የኢትዮ-ሼፕ የአሰልጣኞች ስልጠና ለምን አስፈለገ?**
>
> ይህን ስልጠና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ላይ ሳይንሳዊ ዕውቀትና ሙያዊ ክህሎትን በማጎልበት፣ በራስ መተማመንን ለማዳበርና የተሻለ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስጠት ለማስቻል ነው፡፡

## 6.7. ከስልጠናው በኋላ መሰራት ያለባቸው ተግባራት

የሰለጠኑ የልማት ሰራተኞች (በወረዳ እና ዞን ድጋፍ ታግዘው) የቀሰሙትን እውቀትና ክህሎት ለፕሮጀክቱ ተጠቃሚ አርሶ አደር ቡድኖች ተከታታይ የመስክ-ላይ ስልጠና መስጠት ይጠበቅባቸዋል።

ወረዳና የልማት ሰራተኞች የመስክ ስልጠና ሪፖርት በዞን እና በክልል ደረጃ ለሚመለከተው አካል ይልካሉ።

## 6.8. ፎቶግራፍ




የግብርና ባለሙያ ሰብል የማምረት ደረጃዎች በተመለከተ ትምህርታዊ ገለጻ ሲያደርግ



የተፈጥሮ ማዳበርያ አሰራር ተግባራዊ ስልጠና




ተሳታፊዎች ያዘጋጁትን የሰብል የማምረቻ የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጃት ልምምድ ውጤት ሲያቀርቡ




ተሳታፊዎችያዘጋጁትን የድርጊት-መርሃ-ግብራቸውን ሲያቀርቡ

# 7. ደረጃ 7: አሳታፊ የችግሮች ትንተና፣ የሰብል ጊዜ ሰሌዳ እና የበጀት ዝግጅት አስራር

| አራት (4) ደረጃዎች | ዋና ዋና ተግባራት (Activities) |
|---|---|
| 1. ግቡን እና ዓላማውን ለአርሶ አደርና ለአጋር አካላት ማስተዋወቅ | - የትውውቅ ፕሮግራም ማካሄድ |
| 2. የአርሶአደሮችን ግንዛቤ ማሳደግ | - አሳታፊ መሰረታዊ መረጃ የዳሰሳ ጥናት<br>- የገበያ ጥናት |
| **3. የአርሶአደሮችን ውሳኔ ሰጭነት አቅም ማሳደግ** | - የሰብል መምረጥ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የባለድርሻ አካላት መድረክ ማዘጋጀት<br>- **የሚያጋጥሙ ችግሮችን ልየታ ፣ የሰብል አመራረት የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀትና ማለማመድ** |
| 4. የአርሶአደሩን እዉቀትና ክህሎት ማሳደግ | - በገበሬ ማሳ ላይ ስልጠና መስጠት<br>- የስርዓተ ፆታ ስልጠና በመስጠት ግንዛቤ ማሳደግ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የልምድ ልውውጥ እና ጉብኝት ማካሄድ<br>- የመስክ ቀን/ የልምድ ልውውጥ ጉብኝት |
| የክትትልና ግምገማ (አሳታፊ የመጨሻ ውጤት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድን ያካትታል) | |

አዚህ ጋር ነን

## 7.1. መግቢያ

የችግር ትንተና ማካሄድ አርሶ አደሩ ከምርት እስከ ገበያ ሊያጋጥመው የሚችለው ዋና ዋና ችግሮችና መንስኤ ለመለየት ይረዳል። የአርሶ አደሮች ውይይት በማመቻቸት ባጋጠሙ ችግሮች ላይ በመመርኮዝ በህብረተሰቡ አማራጭ መፍትሄዎችን ማፍለቅ ይመለከታል። የምርት ጊዜ ሰሌዳ እና የሚያመርቱትን ሰብል የማምረቻ ወጪና ገቢ (በጀት)ስሌት ልምምድ ያደርጋሉ። አርሶ አደሮች ስለሚያመርቱት ሰብል መነሻ የማምረቻ ወጭና የትርፍ መጠን ማወቅና ከማምረታቸው አስቀድመው ለመወሰን የሚያግዝ መረጃ ይሰበስባሉ።

የግብዓት አቅርቦት ጠቅላላ ወጪ ማለትም ዘር፣ ማዳበሪያ፣ አግሮ-ኬሚካሎች፣የጉልበት ሰራተኛ፣ መጓጓዣና የግብይት ወጪዎችን ለመገመት ያስችላል። በዚህ ልምምድ የሚያመርተውን ሰብል እንዲመርጥ ማድረግ እና ምርቱን በሚፈለገው ጊዜና በመረጠው ገበያ እንዲያቀርብ እቅድ እንዲያዘጋጅ ማድረግ በአርሶ አደር ቡድን አባላቶች መካከል ትስስር እንዲፈጥሩ ማመቻቸት፣ በጋራ/በቡድን ሆኖ በመግዛትና የምርቶቻቸውን መሸጥ የመደራደር አቅማቸው ለማሳደግ ያግዛል።

## 7.2. ዓላማዎች

- አርሶ አደሮች በአመራረትና ግብይት ሂደት ምን አይነት ችግሮች እያጋጠማቸው እንደሆነ/ሊያጋጥማቸው እንደሚችል ለመረዳት፣
- መሰረታዊ የሰብል ምርት ዕቅድና ከፍተኛ ፍላጎት ያለበትን ጊዜ መለየት፣ የገበያ መስፈርቶች (ጥራት፣ ዋጋ የክፍያ ሁኔታዎች፣ ወዘተ የመሳሰሉትን) መረጃዎች ለማወቅ፣
- መነሻ የማምረቻ ወጪ እና የተጣራ ትርፍ በተመረጡ ሰብሎች ላይ እንዴት ማስላት እንዳለባቸው ለማሳወቅ፣
- የጊዜ ሰሌዳን በማስተካከል በጥሩ ዋጋና በገበያ ፍላጎት ወቅት ምርትን ለገበያ ማቅረብ የሚቻልበት አሰራር ለመማር።

## 7.3. የምርት የጊዜ ሰሌዳ አውደ ጥናት/ስልጠና አተገባበር

### 7.3.1. ተሳታፊዎች

- **አዘጋጅ አካል**:- የልማት ሰራተኞች ከወረዳ ሆርቲካልቸር ባለሙያዎች በመተባበር
- **ተሳታፊዎች**: - ተጠቃሚ አርሶ አደር ቡድን አባላት

### 7.3.2. የሚወስደው ጊዜ

ግማሽ ቀን

**ሰንጠረዥ 13.** ናሙና መርሃ-ግበት የሰብል የማምረቻ የጊዜ ሰሌዳ እና በጀት ማዘጋጃት

| ሰዓት | ተግባራት |
|---|---|
| 2:30 - 3:00 | የተሳታፊዎች ምዝገባ<br>የመክፈቻ ንግግር |
| 3:00 - 3:15 | የችግር ትንተናና የሰብል የማምረቻ የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጃት በተመለከተ ገለጻ<br>ተሳታፊ አርሶ አደሮች በፍላጎታቸው/ በመረጡት ሰብል መሰረት በቡድን መከፋፈል |
| 3:15 - 4:30 | አበይት ተግባራት:- የችግር ትንተና፣ የምርት ጊዜ ሰሌዳና በጀት ዝግጅት |
| 4:30 - 4:50 | የሻይ ዕረፍት |
| 4:50 - 5:30 | የችግር ትንተና እና የምርት ጊዜ ሰሌዳ የልምምድ ውጤቶችን በያንዳንዱ ቡድን ማቅረብ |
| 5:30 - 5:55 | የሌሎች ቡድኖች ልምደዶች በተመረጡ ሰብሎች ላይ አሳታፊ የችግሮች ትንተና በማድረግ በተለዩት ችግሮች ላይ ከሌሎች ቡድኖች ልምድ አንጻር የሚያጋጥማቸውን ችግሮች እንዴት እንደቀርፉት ማብራራት/መወያየት።<br>አርሶ አደሮች በጋራ/በቡድን ግብዓት በመግዛትና ምርቶቻቸውን በመሸጥ የመደራደር አቅማቸውን ለማሳደግ ያለው ጥቅም በባለሙያዎች ማሳወቅ |
| 5:55 - 6:05 | በቀጣይ መሰራት ያለባቸው ተግባራት ላይ መወያየት<br>የመዝግያ ንግግር |

### 7.3.3. ቦታ

በተሳታፊ አርሶ አደሮች አቅራቢያ የሚገኝ አማካይ ቦታ መሆን አለበት (ዛፍ ጥላ ስር፣ ወይም በገበሬዎች ማሰልጠኛ ማእከል (FTC) መሆን ይችላል)።

## 7.4. በጀት ለማዘጋጀት የሚረዳ ናሙና ቅጽ

| የክፍያ ዐይነት | የቀን ብዛት | የሰው ብዛት |
|---|---|---|
| አበል (ለወረዳ ባለሙያ) | 1 | 2 |
| የትራንስፓርት/ነዳጅ ወጭ (ለወረዳ ባለሙያ) | 2 | 2 |
| ውሀ | 1 | 40 |
| ቀላል ምግቦች | 1 | 5 |
| የጽህፈት መሳሪያዎች (የሰብል የጊዜ ሰሌዳ ቅጽ፣ እስክርቢቶ) | 1 | 1 |

**ከላይ የተዘረዘሩትን ቁጥሮች ግምታዊ ማሳያ ስለሆኑ አስፈጻሚ አካላት የእያንዳንዱ ወረዳ ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት በትግበራ ጊዜ ማስተካከል ይችላሉ።*

## 7.5. የምክክር ስብሰባዎችን ቅድመ ዝግጅት

- ከተጠቃሚ የአርሶ አደር ቡድን መሪዎች በመነጋገር የልማት ሰራተኞች አመቺ የሆነ ቀን ይወስናሉ።
- የምርት ጊዜ ሰሌዳ ቅጽ (ዕዝል 2.7) ማዘጋጀትና ማተም።

## 7.6. የምክክር መድረክ ማካሄድ

**የችግር/የክፍተት ትንተና ማካሄድ**

በተመረጡ ሰብሎች ላይ አሳታፊ በችግሮች ላይ ውይይት በማድረግ አርሶ አደሮች የሚያጋጥማቸውን ችግሮች በዝርዝር መለየት ያስችላል። (ለምሳሌ በሽታና ተባይ ከማለት ይልቅ ምን አይነት በሽታና ተባይ እንደሆነ በግልጽ መጠቀስ ይገባል። ችግሩ በግልጽ መለየት ካልቻሉ ይህ ግኝት በራሱ ችግር/ክፍተት ማሳያ ነው)።

ባለሙያዎች ከአርሶ አደር ቡድኖች ጋር በመተባበር የችግር/የክፍተት ትንተና ቅጽ መሙላት።

**የሰብል ጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጃት**

- የሰብል ጊዜ ሰሌዳ ከማዘጋጀት በፊት፣ አርሶ አደሮች ከፍተኛ የገበያ ፍላጎት ያለበት ወቅት መሰረት በማድረግና ከገበያ ቅኝት/ጥናት በሚያገኙት መረጃ መሰረት የሚያመርቱትን ሰብል መምረጣቸው ልብ ሊባል ይገባል።
- በማምረቻ የጊዜ ሰሌዳው በስተግራ የላይኛው ጠርዝ ላይ በተጠቀሰው መሰረታዊ የምርት መረጃ በመመስረት፣ አርሶ አደሮች

የራሳቸውን የምርት ጊዜ ሰሌዳ እቅድ ማዘጋቸት ይጀምራሉ። የሚከተሉትን ቅደም-ተከተላዊ ደረጃዎች መጀመር ይመከራል። የሚመርተው ሰብል/ዝርያ፤ የማሳ መጠን፣ የማሳ ዝግጅት፣ የዘር መጠን፣ ሰው-ሰራሽ ማዳበሪያ፣ የተፈጥሮ ማዳበሪያ (ፍግ፣ ብስባሽ/ኮምፖስት)፣ የሰብል እንክብካቤ፣ እና ምርት መሰብሰብ።

- ተፈላጊው የዩሪያ መጠን (ከተከላ በኋላ መጨመር ካስፈለገ) እና የሚያስፈልገው ዩሪያ መጠን ማስላት።
- በአማካይ ከ1ሄክታር ሊመረት የሚችል የምርት መጠን እና አርሶ አደሮች ከዚህ በፊት የሚያገኙትን ምርት በማነጻጸር፣ ምን ያህል ምርት ማግኘት እንዳቀዱ ግብ ማስቀመጥ፣ የሚሸጥበት ቦታ፣ ዋጋ መወሰን። እነዚህ መነሻ መረጃዎች ከፕሮጀክቱ በኋላ የተገኘው መሻሻል/ በምርት ዘመን መጨረሻ ላይ ምርታማነትን ለመመዘን ወሳኝ ሚና አላቸው፣
- በዚህ ሂደት ሁለተኛ ምዕራፍ፣ የማምረቻ ወጭዎች ማስላት ነው፡፡ በቅጹ በስተቀኝ በኩል የተሰጠው ቦታ መሙላት።
- በመጨረሻም፣ ቀጥሎ በተሰጠው የእኩሌታ ቀመር የአርሶ-አደሩ የተጣራ ትርፍ ማስላት።

  የተጣራ ትርፍ = (የአንዱ መለኪያ ዋጋ × ጠቅላላ ምርት ግምት) – ጠቅላላ የማምረቻ ወጪ

- በምርት ዘመን መጨረሻ ላይ የዚህ ስሌት ውጤት እና በተጨባጭ የተገኘው ትርፍ መካከል ያለው ልዩነት መገምገም ያሰፈልጋል። ይህ ተግባር ቁልፍ ሚና ያለው ልምምድ ነው። ምክንያቱም የአንድ አርሶ አደር (ሴትና ወንድ) ትርፋቸው ላይ ተጽእኖ ያሳደሩ ምክንያቶች ለመለየት ይረዳል፡፡
- በተገኘው ልምድ በመመስረት አርሶ አደሮች በሚቀጥለው የማምረት ዕቅድ ላይ ትርፋቸውን እንዴት ማሻሻል አንዳለባቸው ከግምት ውስጥ እንዲያስገቡ ያስችላቸዋል።

**የትግበራ ፍንጭ፡-አርሶ አደሮች የሰብል ጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጃት ለምን ያስፈልጋቸዋል?**

የሰብል ጊዜ ሰሌዳ አሰራር ላይ ተግባራዊ ስልጠና በመስጠት አርሶ አደሮች የምርት መጠን ክፍተት እና አማራጭ መፍትሄ ምክረ-ሀሳቦች ለመተግበር ያስችላል። አርሶ አደሮች ተፈላጊ ጥራት ያለው ምርት ከፍተኛ የገበያ ፍላጎት ባለበት ወቅት ማምረት አንዲችሉ ያግዛል።



**ነጥቦች፡- በስነ-ጾታ ስርጸት ላይ**

የባልና ሚስት ስለ የሰብል ማምረት የጊዜ ሰሌዳ ዝግጅት ግንዛቤ መያዝና እኩል መሳተፍ ግብርናቸውን በዕቅድ በመምራት ምርቱ በገበያ ተፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ እንዲደርስ ያስችላቸዋል፡፡ምርታቸውን ለመረጡት ገበያ በተፈላጊው መጠንና ጥራት እንዲያቀርቡም ያስችላቸዋል፡፡

በልምድ እንደሚታወቀው ሴቶች በሰብል ማምረት የጊዜ ሰሌዳ ዝግጅት ተሳትፎ አነስተኛ ነው፡፡ይህንን ችግር ለመቅረፍ ሴቶች በሰብል ማምረት የጊዜ ሰሌዳ ዝግጅት ላይ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማበረታታት

## ድምጽ ከኢትዮጵያ መስክ

**የማምረቻ ጊዜን ከገበያ ፍላጎት ወቅት ጋር ማጣጣም**



በገበያ ጥናት በአገኘሁት መረጃ መሰረት የድንች ማምረቻ ጊዜዬን በመቀየር በከፍተኛ ዋጋ በመሸጥ ተጠቃሚ መሆን ችያለሁ። ቀደም ሲል ድንች በመጋቢት ዘርቼ ምርት የምሰበስበዉ በዝናብ ወቅት ነበር ። በዚህ ወቅት ሌሎችም አርሶ አደሮች ምርት የሚሰበስቡበትና ለገበያ የሚያቀርቡበት ወቅት በመሆኑ በአካባቢዉ የድንች ዋጋ ዝቅተኛ ነበር ።አሁን በአገኘሁት የገበያ መረጃ መሰረት በመኸር በአጭር ጊዜ የሚደርሱ ሰብሎችን በመዝራት መሬቱን ተሎ እንዲለቁልኝ በማደረግ ድንች በመስከረም ዘርቼ በህዳርና በታህሳስ ለገበያ በማቅረብ በተሸለ ዋጋ በመሸጥ ተጠቃሚ ነኝ ።"

**አቶ ተረፈ ወርቁ** (አርሶ አደር፤ ጂጋ ቀበሌ ፤ ጃቢጠህናን ወረዳ ፤ ምዕራብ ጎጃም ዞን ፤ አማራ ክልል)

## 7.7. ናሙና ቅጾች


**ሰንጠረዥ 14.** የችግር ትንተና ናሙና ቅጽ

| ችግር | ዓላማ | ተግባራት | ደረጃ | ሃብት | ፈጻሚ አካል | ጊዜ ሰሌዳ | ክትትል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |


**ሰንጠረዥ 15.** ምሳሌ፥ የችግር ትንተና

| ዋና ዋና ችግሮች | ዓላማ | ተግባራት | ችግሩ የሚከሰትበት ደረጃ | የሚያስፈልግ ግብዓት | ፈፃሚ አካል | የመተግበሪያ ጊዜ | የሚከታተለዉ /ፈፃሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የዘር ጥራት ዝቅተኛ መሆን | ጥራቱን የጠበቀ ዘር አቅርቦት | ከአቅራቢዎች ጥራቱን የጠበቀና የተመሰከረለት ዘር እንዲቀርብ ማድረግ | ከዘር ወቅት በፊት | ከአቅራቢዎች ጋር መረጃ ለመለዋወጥ የስልክ እና ትራስፖርት ወጪ | የተጠቃሚ አርሶ አደር ተወካዮች | ነሀሴ ወር | የቀበሌ ባለሙያዎች |
| ~~አነስተኛ ምርት~~ የአፈር ለምነት መቀነስ | የአፈር ለምነትን ማሻሻል | ኮምፖስት ማዘጋጀት | ከዘር ወቅት በፊት | የእንስሳት ፍግ/ የአረንጓዴ ተክል ፤ አመድ ወዘተ | ሁሉም አርሶ አደሮች | ነሀሴ ወር | የቀበሌ ባለሙያዎች |
| ወደ አፈሩ የሚጨመሩ ኮምፖስትና ማዳበሪያ መጠን አነስተኛ መሆን | ለሰብሉ የሚያስ ፈልጉ ንጥረ ነገሮች ማሻሻል | በፓኬጁ (በካሚሽባይ) ላይ በተጠቀሰዉ መሰሠረት የሚያስፈልገዉን በቂ ንጥረ ነገር ለመጨመር ከቀበሌ ባለሙያዉ ወይም ከሞዴል አርሶ አደሮች በቂ እዉቀት መማር | ከዘር ወቅት ከመድረሱ በፊት | ስልጠና በሚሰጥበት ወቅት በስልጠና ቦታ በመገኘት | የቀበሌ ባለሙያዎ ች | መስከረም | የቀበሌ ባለሙያዎች |
| ~~የበሽታ ችግር~~ የባክቴሪያ አጠውልግ | ጠዉልግ ፤ ዓይ ትል የመሳሰሉ በሽታና ተባይ ክስተትን መቀነስ | ተመሳሳይ ቤተሰብ ያላቸዉን ሰብሎች አከታትሎ አለመዝራት(አለመትከል) የሰብል ፈረቃ መጠቀም | ከዘር ወቅት በፊት | ግብዓት አያስፈልገዉም | ሁሉም አርሶ አደሮች በየማሳቸዉ | ከመስከረ ም ጀምሮ | የቀበሌ ባለሙያዎች |
| የምርት የመሸጫ ዋጋ ዝቅተኛ መሆን | የተሻለ የመሸጫ ዋጋ እንዲኖር ማድረግ | በገበያ ጥናትና ከአጋር አካላት ምክክር መድረክ ወቅት በሚገኘዉ መረጃ መሰረት የምርት ጥራትን ማሳደግ፤ ከገዥዎች ጋር የገበያ መረጃ መሰብሰብ ። | ምርት ከመሰብሰቡ በፊት | ምርቱን ወደ ገበያ ለማጓጓዝ የትራንስፖርት ወጪ | የአርሶ አደር ተወካዮች/ ማህበራት | ከህዳር ጀምሮ | የቀበሌ ባለሙያዎች |


**ስዕል 14.** ናሙና ቅጽ፡- የምርት ጊዜ ሰሌዳ እና በጀት ፍላጎት




**ስዕል 15.** ምሳሌ የምርት ጊዜ ሰሌዳና በጀት ፍላጎት ስሌት



**ስዕል 16.** የሰብል ማምረቻ ጊዜ ሰሌዳ እና በጀት ማዘጋጃ ፎርም



## 7.8. **ፎቶግራፍ**



የቀበሌ ልማት ሰራተኞች ስለ ችግር ትንተና እና መፍትሄ መርሃ-ግብር ቅጽ ማብራርያ ሲሰጡ



አርሶ አደሮች ችግር መለየትና ችግሮቹን ለመፍታት የድርጊት መርሀ-ግብር አዘገጃጀት ሲወያዩ



ባለሙያዎች የምርት ጊዜ ሰሌዳ ቅጽ አሞላል በተመለከተ ገለጻ ሲያደርጉ



የአርሶ አደሮች የምርት የጊዜ ሰሌዳ ቅጽ ሲሞሉ



አንድ አርሶ አደር ላልተማሩ ሌሎች አርሶ አደሮች ድጋፍ እየሰጠ



የኤክስቴንሽን ባለሙያ አርሶ አደሮችን ስለ ምርት ጊዜ ሰሌዳ ቅጽ አሞላል ሲያስረዳ

## 8. ደረጃ 8: የመስክ-ላይ ስልጠና

| አራት (4) ደረጃዎች | ዋና ዋና ተግባራት (Activities) |
|---|---|
| 1. ግቡን እና ዓላማውን ለአርሶ አደርና ለአጋር አካላት ማስተዋወቅ | - የትውውቅ ፕሮግራም ማካሄድ |
| 2. የአርሶአደሮችን ግንዛቤ ማሳደግ | - አሳታፊ መሰረታዊ መረጃ የዳሰሳ ጥናት<br>- የገበያ ጥናት |
| 3. የአርሶአደሮችን ውሳኔ ሰጭነት አቅም ማሳደግ | - የሰብል መምረጥ<br>- የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለየታ ፣ የሰብል አመራረት የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀትና ማለማመድ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የባለድርሻ አካላት መድረክ ማዘጋጀት |
| 4. **የአርሶአደሩን እዉቀትና ክህሎት ማሳደግ** | - **በገበሬ ማሳ ላይ ስልጠና መስጠት**<br>- የስርዓተ ፆታ ስልጠና በመስጠት ግንዛቤ ማሳደግ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የልምድ ልውውጥ እና ጉብኝት ማካሄድ<br>- የመስክ ቀን/ የልምድ ልውውጥ ጉብኝት |
| የክትትልና ግምገማ (አሳታፊ የመጨሻ ውጤት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድን ያካትታል) | |

አዚህ ጋር ነን

### 8.1. መግቢያ

ተከታታይ የመስክ-ላይ ስልጠና መስጠት ተጠቃሚ አርሶ አደሮች በሆርቲካልቸር ሰብሎች አመራረት ላይ የተለዩ ክፍተቶችን ለመቅረፍ ነው። የስልጠና ፍላጎት ለመሙላት አመች ወቅት ለይቶ ሥልጠና ይሰጣል። ይህ ስልጠና የዘን እና የወረዳ ባለሙያዎች የኢትዮ-ሸፐ የአሰልጣኞች ስልጠና ከተሰጣቸው በኋላ ተፈጻሚ የሚሆን ነው።

የተጠቃሚዎችን መረጃ ዳሰሳ ጥናት ለመተግበር አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው።

### 8.2. ዓላማ

- ተጠቃሚ አርሶ አደሮች በተመረጡት ሰብሎች መሰረት ያላቸውን እውቀትና ክህሎት ለማሻሻል በተመረጡ አርሶ አደር ቡድኖች ማሳ ላይ ተግባራዊ ስልጠና ይሰጣል።

### 8.3. የስልጠናው ይዘትና አተገባበር

- የኢትዮ-ሸፐ ፕሮጀክት የሥልጠና ቁሳቁሶች በማዘጋጀት በንድፈ-ሀሣብና በተግባር የተደገፈ ሥልጠና መሰጠት ይኖርበታል። እንደ ስልጠናው ትምህርታዊ ይዘት፡- ገለጻ፤ የልምምድ እና ሰርቶ ማሳያ ማሳዎች ጉብኝት ዘዴዎች በማጣመር ይካሄዳል።

- በአርሶ አደሮች ስልጠናና በአሰልጣኞች ስልጠና የሚሸፈኑ አርዕስቶች ተመሳሳይ ቢሆንም የኤክስቴንሽን ሰራተኞች ግን በተመረጡት ሰብሎች ማተኮር አለባቸው። ይህም አዳዲስ አሰራሮችን በራሳቸው ማሣ ላይ እንዲሞክሩና ዕውቀትን እንዲጋሩ በማድረግ ገበያ ተኮር ምርት ማበረታታት ለማስቻል ነው።

- በኤክስቴንሽን ስልጠና ወቅት ***በካሚሺባይ/*** *Kamishibai'*/ የሥልጠና ማቴሪያሎች የተደገፈ ሥልጠና መሰጠት ይኖርበታል። 'ካሚሺባይ መነሻው በጃፓን የሆነ የታሪክ ነገራ/ገለጻ አንዱ ዘዴ እንደሆነ ይጠቀሳል። ምሳሌአዊ ካርዶች መሰረት ያደረገ የመማሪያ መሳሪያ ነው። በኢትዮ-ሸፐ ፕሮጀክት ዘዴ ካሚሺባይ የግብርና ኤክስቴንሽ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል። ባለ ሁለት(2) ገጽ ካርዶች የተዘጋጀ ከፊትለፊት ፎቶግራፍ እና በጀርባው ደግሞ የፎቶግራፉ ጽሁፋዊ መግለጫ እንዲሁም 'ለአሰልጣኝ ማስታወሻ' የያዘ ነው።

- **የካሚሺባይ ጠንካራ ጎኖች**:

  ① በኤክስቴንሽ *ን ሰራተኞች ለመጠቀም ቀላል መሆኑ*

- ለመያዝ ቀላልነት፡- በቀላሉ ለማንቀሳቀስ መቻሉ
- ረዥም ጊዜ መቆየት፡- በአየር መለዋወጥ እንዳይበላሹ ሽፋን ያላቸው በመሆኑ
- ከሌሎች የተጻፉ መሳሪያዎች ሲነጻጸር ካሚሺባይ በጠንካራ ሽፋን የተጠረዙና ረዥም ጊዜ መቆየት የሚችሉ ናቸው።

② አርሶ አደሮች በቀላሉ ይረዷቸዋል

- ምክንያቱም ከረጃጅም ጽሁፎች ይለቅ ገላጭ ፎቶዎች ገላጭ በመሆናቸው ነው።

## 8.4. የስልጠናው ፕሮግራም አተገባበር

### 8.4.1. ተሳታፊዎች

**አዘጋጅ/አመቻች፡-** የሸፐ አሰልጣኞች ስልጠና የወሰዱ የወረዳ ባለሙያዎችና የቀበሌ ልማት ወኪሎች

**ክትትልና ድጋፍ፡-** ዞን እና ወረዳ የሆርቲከልቸር ባለሙያዎች

**ተሳታፊዎች/ ሰልጣኞች ፡-** የተጠቃሚ አርሶ አደሮች ተወካይ አባላት (ከመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት የተመረጡ)

### 8.4.2. የአርሶ አደሮችን የስልጠና ቀን መወሰን

በመስክ-ላይ ስልጠና መተግበር ያለበት ከገበያ ጥናት በተገኙት መረጃዎች መሰረት የሚያመርቱትን ሰብል ዕቅድና የማምረቻ የጊዜ ሰሌዳ በማሳየት እንዲሁም ሌሎች የማህበረሰቡ የጊዜ ሰሌዳን ከግምት ውስጥ በማስገባት ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ ማቀድ ያስፈልጋል፡፡ በስልጠናው ወቅት ከሚዘሩት /ከሚተክሉት ሰብል የተከላ/የዘር ወቅት ጋር በማስተካከል የስልጠና ፕሮግራሞች ማቀናጀት ይገባል።

### 8.4.3. የስልጠና ቦታ

በተሳታፊ አርሶ አደር ቡድኖች አቅራቢያ የሚገኝ አማካይ ቦታ መሆን አለበት፡- ለተሳታፊዎች ምቹ ከሆነ በገበሬዎች ማሰልጠኛ ማዕከል (FTC) መሆን ይችላል።

**ሰንጠረዥ 16.** ናሙና የመስክ ላይ ስልጠና ፕሮግራም

| የስልጠና ጊዜ | የስልጠና ብዛት | አሆሰአ እና ድምአቴ ጂ-24 | የስነ-ጾታ ግንዛቤ እና የቤተሰብ በጀት ምጣኔ | ዶክመንቶች/ሪፖርቶች ማስረከብ |
|---|---|---|---|---|
| ነሐሴ | 1 | የችግር ትንተና፣ የሰብል የማምረቻ የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጃት | የወረዳ ስነ-ጾታ ባለሙያ የሚከተሉትን ልምምዶች ያመቻቻል፡- የአምራችነትና የማህበራዊ ሚና፣ የሃብት ተደራሽነትና መቆጣጠር | • የመስክ ሪፖርት<br>• የችግር ትንተና ውጤት፡ የሰብል የማምረቻ የጊዜ ሰሌዳ፣ በጀት ቅድ |
| መስከረም | 2 | በተመረጡ ሰብሎች ላይ መሰረታዊ በሆኑ የማምረቻ ቴክኒኮች ላይ ስልጠና | | የመስክ ሪፖርት |
| ጥቅምት | 3 | ቅድመ ምርት ዝግጅት: የአፈር ለምነት ሁኔታ፣ የችግኝ ማፍያ መደብ ዝግጅት (ኮምፖስት ዝግጅት፣ መደብ ማዘጋጀት፣ አፈርን ከተህዋስያን ማጽዳት (soil sterilization) | | በፎቶግራፍ የተደገፈ የመስክ ሪፖርት |
| ህዳር | 4 | የችግኝ መደብ መንከባከብ፡ ዘር መዝራት | | በፎቶግራፍ የተደገፈ የመስክ ሪፖርት |
| ታህሳስ | 5 | ችግኝ ማዛመት፡ ችግኝ ማዛመት/ማዛወር፣ ማዳበርያ ከላይ መጨመር፡- በብተና ማዳበርያ መጨመር (መጠን እና አጠቃቀም ዘዴ) | | በፎቶግራፍ የተደገፈ የመስክ ሪፖርት |
| ታህሳስ - ጥር | 6 | ከተከላ በኋላ ማዳበሪያ መጨመር፡- የማዳበሪያ አጠቃቀም (መጠን እና የአደራረግ ዘዴ)፣ ተባይና በሽታ መለየት | | በፎቶግራፍ የተደገፈ የመስክ ሪፖርት |
| የካቲት - መጋቢት | 7 | ምርት መሰብሰብ እና ድህረ-ምርት አያያዝ የመስኖ አስተዳደር፣ ምርት ማድረቅ ፣ ምርት በደረጃ መለየት | | በፎቶግራፍ የተደገፈ የመስክ ሪፖርት |

## 8.5. በጀት ለማዘጋጀት የሚረዳ ናሙና ቅጽ

| የክፍያ ዐይነት | የቀን ብዛት | የሰው ብዛት |
|---|---|---|
| አበል (ለወረዳ ባለሞያ) | 1 | 1 |
| ነዳጅ ለሞተር ሳይክል (ለወረዳ) | 1 | 1 |

**ከላይ የተዘረዘሩትን ቁጥሮች ግምታዊ ማሳያ ስለሆኑ አስፈጻሚ አካላት የእያንዳንዱ ወረዳ ተጨበጭ ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት በትግበራ ጊዜ ማስተካከል ይችላሉ።*

## 8.6. የስልጠና ዝግጅትና አሰራር

**የቀበሌ የልማት ሰራተኞችና የወረዳ ባለሙያዎች ማድረግ ያለባቸው:-**

- የተሳታፊ አርሶ አደር ቡድኖች የስልጠና መርሀ-ግብር በተመለከተ አስቀድሞ ማሳወቅ፣
- ለስልጠናው የሚያስፈልጉትን መሳሪያዎች/ቁሳቁሶች ማቀናጀት/ በእጅ የሚታደል ጽሁፍ (ሀንድአውት)/የተለያዩ ቅጾች ማዘጋጀት (ለዝርዝር ዕዝል 2.8 ተመልከቱ)፣
- የስልጠና ዝርዝር ጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት:- ናሙና የጊዜ ሰሌዳ (ሰንጠረዥ 16 ይመልከቱ)፣
- የስልጠናው ቀን እና ቦታ፣ እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ ሰርቶ ማሳያ ማዘጋጀት።

## 8.7. የስልጠናው አተገባበር

- ስልጠናው የሚሰጠው በቀበሌ የልማት ሰራተኞችና ወረዳ ባለሙሞያዎች ሲሆን ለዚህ የተዘጋጁትን ማጣቀሻ ሰነዶችና ናሙና የጊዜ ሰሌዳ (ሰንጠረዥ 16 ላይ ይመልከቱ)።

**የትግበራ ፍንጭ:- በመስክ ላይ ስልጠና ለምን አሰፈለገ ?**

በመስክ-ላይ የተዘጋጀ ስልጠና የአርሶ አደሮች እውቀትና ክህሎት ያጎለብታል።

## 8.8. ከስልጠናው በኋላ በቀጣይ መሰራት ያለባቸው ተግባራት

- የመስክ ላይ (በአርሶ አደሮች ማሳ ላይ) የስልጠና ክትትል የሚተገበረው በክልል እና በዞን ባለሙያዎች ሲሆን የስልጠና የትግበራ ሂደት መታዘብና እና ጥራቱን ማረጋገጥ ላይ ትኩረት ያደርጋል።
- የስልጠና ረፖርቶች በወቅቱ ለዞንና ክልል ሆርቲካልቸር ባለሞያ መላክ ይገባል።

## 8.9. ፎቶግራፍ



ባለሙያ መሰረታዊ የሰብል አመራረት **በካሚሺባይ ዘዴ** የአካባቢው አርሶ አደሮች ስልጠና እየሰጠ ነው።.



ባለሙሞያ የምርት ጊዜ ሰሌዳ ስልጠና በተመረጡ ሰብሎች ላይ መረጃ ለአርሶ አደሮች እየሰጠ ይገኛል'።



በልማት ሰራተኛ ድጋፍ አርሶ አደሮች የችግኝ መደብ ዝግጅት እና ዘር አዘራር



ባለሙሞያ ከአርሶ አደሮች ቡድን አባላት ጋር በማሳ ቅኝት ላይ

## 8.10. ናሙና የስልጠና መሳሪያዎች




የአማርኛ ቅጂ




የኦሮምኛ ቅጂ




የፊት ገጽ፡- ትልቅ ስዕል ከአጭር መግለጫ ጋር ያሳያል




የጀርባ ገጽ፡- ዝርዝር መግለጫ ያካትታል። ይህም ኤክስተንሽን ሰራተኞች መረጃውን እያዩ ስልጠና መስጠት ያስችላቸዋል



**ነጥቦች፡- በስነ-ጾታ ስርጸት ዙሪያ**

ብዙውን ጊዜ የሴቶች በመስክ የተግባር ስልጠና በዕኩልነት አይሳተፉም፡፡ ምክንያቱም በተግባር ሊያውሉት የሚችሉት ያላቸው የግብርና ቴክኒክ ክህሎት ከወንዶች ሲነጻፀር አነስተኛ ነው፡፡

ባልና ሚስት በመስክ የግብርና ስራ እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ሴቶች በተግባር የግብርና የቴክኒክ ስልጠና እንዲሳተፉ ምቹ ሁኔታ ሊፈጠርላቸው ይገባል፡፡

**ድምጽ ከኢትዮጵያ መስክ**

**ከዚህ በኋላ በክሽክሽ ምክንያት ጥቅል ጎመን የማምረት ችግር አየኖርብኝም!**



ከዚህ በፊት በክሽክሽ ምክንያት ጥቅል ጎመን ለማምረት በጣም እንቸገር ነበር ፡፡ በቀበሌ ባለሙያዎች አማካይነት የፈሳሽ ሳሙናና የበረኪና ዉህድ በማዘጋጀትና በመርጨት ክሽክሽን እንዴት መከላከል እንደሚቻል የተግባር ስልጠና ወስጃለሁ፡፡ በአገኘሁት ትምህርት መሰረት በረኪና ገዝቼ ከፈሳሽ ሳሙናና ዉሃ ጋር በማዋሃድ በጥቅል ጎመን ማሳ ላይ በመርጨት የክሽክሽ ተባይን በመከላከል ዉጤታማ መሆን ችያለሁ፡፡ ከዚህ በኋላ በክሽክሽ ምክንያት ጥቅል ጎመን የማምረት ችግር አይኖርብኝም ፤ ሌሎች አርሶ አደሮችም የኔን ማሳ በማየት ይህን አሰራር በተሞክሮነት ወስደዉ ክሽክሽን በመከላከል ተግባራዊ እያደረጉ ነዉ”

**ቄስ አለማየሁ በየነ - (አርሶ አደር** ፤በካፍታ ቀበሌ፤ አንከሻ ወረዳ ፤አዊ ዞን ፣ አማራ ክልል)

## 9. ደረጃ 9: የሥርዐተ-ፆታ ግንዛቤ ለማሳደግ የተዘጋጀ የስልጠና ማንዋል

| አራት (4) ደረጃዎች | ዋና ዋና ተግባራት (Activities) |
|---|---|
| 1. ግቡን እና ዓላማውን ለአርሶ አደርና ለአጋር አካላት ማስተዋወቅ | - የትውውቅ ፕሮግራም ማካሄድ |
| 2. የአርሶአደሮችን ግንዛቤ ማሳደግ | - አሳታፊ መሰረታዊ መረጃ የዳሰሳ ጥናት<br>- የገበያ ጥናት |
| 3. የአርሶአደሮችን ውሳኔ ሰጪነት አቅም ማሳደግ | - የሰብል መምረጥ<br>- የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለየታ ፣ የሰብል አመራረት የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀትና ማለማመድ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የባለድርሻ አካላት መድረክ ማዘጋጀት |
| 4. **የአርሶአደሩን እዉቀትና ክህሎት ማሳደግ** | - በገበሬ ማሳ ላይ ስልጠና መስጠት<br>**- የስርዓተ ፆታ ስልጠና በመስጠት ግንዛቤ ማሳደግ** ⬅ አዚህ ጋር ነን<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የልምድ ልውውጥ እና ጉብኝት ማካሄድ<br>- የመስክ ቀን/ የልምድ ልውውጥ ጉብኝት |
| የክትትልና ግምገማ (አሳታፊ የመጨሻ ውጤት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድን ያካትታል) | |

### 9.1. መግቢያ

የ ሼፕ ኤክስቴንሽን ትግበራ ዘዴ በሆርቲካልቸር ልማት ተሳታፊ አርሶ አደሮችን የሥርዓተ ጾታ ስልጠና መስጠት ግብርናን በዋናነት የገቢ ማስገኛ ተግባር/ አግሪ ቢስነስ / ለመምራት የሚያስችል ተግባር መሆኑን አዉቀዉ እንዲመሩት አቅማቸዉን ያሳድጋል ብሎ ያምናል። የስርዓተ ጾታ ስልጠና አርሶ አደሮች በቤተሰብ ደረጃ የጋራ ራዕይ እንዲኖራቸዉ ያደርጋል። ማለትም የቤተሰብ የኑሮ ሁኔታ የማሻሻል፤ ለግባቸዉ መሳካት ያነሳሳል። በትግበራ ወቅት የስርዓተ ጾታ እኩልነት ከግምት ዉስጥ ካልገባ በባልና ሚስት መካከል የዉሳኔ አሰጣጥ ላይ ልዩነት ወይም አለመግባባት ይፈጠራል ።በቤት ዉስጥ በአንደኛዉ አካል (በሚስት ወይም በባል ) ላይ ወደ አንደኛው ያደላ የስራ ጫና ይፈጠራል ። በቤተሰብ ዉስጥ የስርዓተ ጾታ ምንነትና ግንዛቤ እያደገ በሄደ ቁጥር በባልና ሚስት መካከል መግባባቱ አብሮ ያድጋል፤ የስራ መደጋገፉና መተሳሰቡ ይጎለብታል፡ በግብርና ስራቸዉና በግብይት ዉሳኔ አሰጣጥ፤ በገቢ አጠቃቀምና አሰተዳደር ወቅት የጋራ ተሳትፎ ስለሚኖራቸዉ የተሻለ ሃብት ይፈጥራሉ፣ ኑሮአቸዉ ይሻሻላል ።

### 9.2. የስልጠናው ዓላማዎች

- በሥርዐተ-ፆታ እና በጾታ መካከል ያለው ልዩነት ለመረዳት፤
- በቤተሰብ ደረጃ በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለዉን ሃላፊነትና ሚና መረዳዳት እንዶኖር፤
- በቤተሰብ ደረጃ በወንዶችና በሴቶች መካከል ቤተሰቡን በመምራትና በማስተዳደር በሚከናወኑ ተግባራት ማን የበለጠ ጫና እንዳለበት ለማስረዳት፤
- በቤተሰቡ ዉስጥ በሃብት አጠቃቀምና ዉሳኔ በመስጠት ላይ የበለጠ ሚና እንዳለዉ ለማወቅና በቀጣይ ምን መስተካከል እንዳለበት ግንዛቤ ለመያዝ፤
- በቤተሰብ ደረጃ በሴቶች ላይ ያለዉን የስራ ጫና ለመቀነስ የሚያስችል የድርጊት መርሃ-ግብር ለማዘጋጀት።

### 9.3. የስልጠናው ትግበራ ሂደት

#### 9.3.1. የስርዓተ ጾታ ስልጠና ተሳታፊዎች

- **የስልጠናዉ አዘጋጅ:-** የቀበሌ ባለሙያዎች፣ የወረዳ ሆርቲካልቸር ባለሙያዎች፣ ከወረዳና ዞን ስርዓተ ጾታ ኤክስፐርቶች ጋር በመሆን ፤
- **የስልጠናዉ ተሳታፊዎች:** የሸፕ ቡድን አባላት ከቤተሰብ አባላት ውሰጥ ባልና ሚስት ጋር በመሆን።

### 9.3.2. ለስልጠናዉ የሚያስፈልገዉ ጊዜ

ግማሽ ቀን

| ሰዓት | ተግባራት |
|---|---|
| 3:00 - 3:30 | መግቢያ፡- ሥርዐተ-ፆታ እና ጾታ ልዩነትን መረዳት |
| 3:30 - 4:15 | ሰነድ/ ቅጽ 1፣ በወንዶችና ሴቶች መካከል የስራ ድርሻና ሀላፊነት |
| 4:15 - 5:00 | ሰነድ/ ቅጽ 2፣ ዕለታዊ ስራ ክንውን ጊዜ ሰሌዳ |
| 5:00 - 5:45 | ሰነድ 3: ሀብትን የመገልገልና ቁጥጥር ሓላፊነት |
| 11:45 - 12:30 | ሰነድ 4: ሰነድ 4: ሥርዐተ-ፆታ ድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት |
| 12:30 - 12:40 | ውይይት/ማጠቃለያ |

### 9.3.3. የስልጠናዉ ቦታ

የስልጠናዉ የሚሰጥበት ቦታ በተቻለ መጠን ሰልጣኞች በሚኖሩበት አቅራቢያ ቢሆን ይመረጣል። ስልጠናዉን እንዳመችነቱ በዛፍ ስር፣ በአቅራቢያ ት/ቤቶች ባሉ መሰብሰቢያዎች ወይም በአርሶ አደር የስልጠና ማዕከል መስጠት ይቻላል።

## 9.4. ለስልጠናዉ የሚያስፈልግ በጀት ታሳቢ

| የበጀት ወጪ ርዕስ | ቀን ብዛት | ተሳታፊ ብዛት |
|---|---|---|
| የዉሎ አበል (ለዞንና ወረዳ ኤክስፐርቶች) | 1 | TBD** |
| የትራንስፖርት/ነዳጅ | 1 | TBD** |
| የሻይ ቡና | 1 | 45 |
| የቁሳቁስ (የስርዓተ ጾታ ትንተና መረጃ መሳሪያዎች, ፍሊፕ ቻርት, ማርከር) | - | - |
| ማሰታወሻ ደብተርና እስክርቢቶ | 1 | 45 |

*ከላይ የተቀመጡት ዝርዝሮች ለመነሻ ታሳቢ የተጠቀሱ ሲሆን እንደወረዳዉና አካባቢዉ ሁኔታ ሊለያዩ እንደሚችል ታሳቢ ይደረግ።*
***TBD በቀጣይ እንደሁኔታዉ የሚወሰን*

## 9.5. የስልጠናዉ ቅድመ ዝግጅትና አካሄድ

- ከአርሶ አደር ቡድን መሪዎች ጋር በመወያየት ለሰልጠኖች አመቺ በታና ጊዜ በመወሰን የስልጠናዉን አካሄድ መርሃ-ግብር /ቸክ ሊሰት/ ማዘጋጀት ፤
- **ሥልጠናው ከመዘጋጀቱ በፊት ባልና ሚስት በጋራ የስልጠናው ተሳታፊ እንዲሆኑ ማነሳሳትና ማረጋገጥ፣**
- በጥሪዉ መሰረት በስልጠናዉ ላይ ባልና ሚስት የሚገኙ መሆኑን ማረጋገጥ፤
- ለስርዓተ ፆታ ስልጠና አጋዥ ማንዋል ፤ ፍሊፕቻርት፤ ማስመሪያና ማርከር ማዘጋጀት፤

## 9.6. ስልጠናዉ እንዴት ይካሄዳል;

- የስርዓተ ጾታ ስልጠና መካሄድ ያለበት ለዚህ ስልጠና የተዘጋጀዉን ማንዋል መሰረት አድርጎ መሆን አለበት (ማጠቀሻ:- የስርዓተ ጾታ ስልጠና ማነዋል).

**<u>ደረጃ 1</u>**: የስልጠናዉ ተሳታፊዎችን ተሳትፎ ለማበረታታትና ለማነቃቃት በፆታና በስርዓተ ፆታ መካከል ያለዉን ልዩነት እንዲያስረዱ ጥየቄ በመጠየቅ ሃሳብ እንዲሰጡ ማድረግ፤

- <u>የስርዓተ ፆታ ኤክስፐርቱ በአካባቢያቸዉ ምን ዓይነት የስርዓተ ፆታ ጉዳዮች እንዳሉ በመጠየቅና በማወያየት ተሳትፎአቸዉን ማበረታታት፤ (ስልጠናዉን የሚመራዉ ሰዉ በሚሰጡ ሃሳቦች ላይ ሴቶች አስተያየታቸዉን እንዲሰጡ መጋበዝና የማበረታታት ስራ መዘንጋት የለበትም ።</u>
- በፆታና በስርዓተ ፆታ መካከል ያለዉን ልዩነት በቂ ዉይይት ከተካሄደና መግባባት ከተደረሰ ወደ ሚቀጥለዉ የስልጠና ርዕስ መሄድ ፤

**<u>ደረጃ 2</u>**: በወንዶችና በሴቶች መካከል የስራ ድርሻና ሀላፊነት ትንተና **መስራት (ቅፅ 1**)


__ደረጃ 3__: የስርዓተ ጾታ ትንተና (ቅፅ **2) መሰረት በሴቶችና ወንዶች መካከል ያለዉን ዕለታዊ የስራ ክንውን ትንተና ማካሄድ ፤**

__ደረጃ 4__: የስርዓተ ጾታ ትንተና ቅፅ **3 መሰረት በሀብትና የመገልገያ አጠቃቀምና ቁጥጥር ኃላፊነት የወንዶችና የሴቶችን ድርሻ ትንተና ማካሄድ ፤**


የስርዓተ ፆታ ስልጠና በወንድና በሴት መካከል ያለዉን የሥራ ጫናና ሃላፊነት እኩልነት በማስረዳት የሚኖረዉን ጥቅም ግንዛቤያቸዉን በማስፋት፤ የሴቶችን የሥራ ጫና በመቀነስ ዙሪያ ተሳታፊዎች እንዴት እንደተረዱት ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ከስልጠናዉ መጨረሻ ሁሉም የስልጠናዉ ተሳታፊዎች በቤተብ ደረጃ ሊተገበሩ የሚችሉ፤ በሴቶች ላይ ያለዉን ጫና ለመቀነስ የሥርዐተ-ፆታ ድርጊት መርሃ ግብር እቅድ እንዲያዘጋጁ ማድረግ ያስፈልጋል።.

**ከግንዛቤ ማስጨበጫ ቅስቀሳ በኋላ፣- አንዳንድ አርሶ አደሮች ስለ ስርዓተ ጾታ በቂ ግንዛቤ ላይኖራቸዉ ይችላል፤**
አንዳንዱ አርሶ አደሮች ስለ ስርዓተ ጾታ ሲጠየቁ በእኛ አካባቢ የስርዓተ ጾታ ችግር የለም የሚል መልስ ይሰጣሉ። የዚህ ስልጠና ዋና ዓላማ አርሶ አደሮችን በአካባቢያቸዉ ምን ዓይነት የስርዓተ ጾታ ችግሮች እንዳሉ ለይተዉ እንዲያዉቁ፤ እነዚህን ችግሮች በቤተሰብና በማህበረሰቡ ዘንድ እንዴት ሊፈቱአቸዉ እንደሚችሉ ማስረዳትና ግንዛቤ መፍጠር መሆኑን ማሳወቅ ነው ።


## 9.7. የስርዓተ ፆታ ስልጠና ማንዋል ናሙና




የስልጠና ማንዋሉ አማርኛዉ ክፍል




የስልጠና ማኑዋል በአፋን ኦሮሞ



4. የሥርዓተ-ፆታ ትንታኔ ሰነድ 3

ሥልጠና ዝግጅት | 1ኛ ቀን | 2ኛ ቀን

ዕለታዊ የስራ ክንውን የጊዜ ሰሌዳ

4.1. ደረጃ 3. ዋና ዓላማው በገጠሩ አርሶ አደሮች ወንዶችን፣ ሴቶችን ወንዶች ልጆችንና ልጃገረዶችን ጨምሮ አለት ተእለት የሥራ ጫና ለማወቅና እያንዳንዱ ሥራ ለመከወን የሚፈጀው ጊዜ ለመገመት ይረዳል።

የስልጠናው አላማ:-

ተሳታፊዎች በቤተሰብ ደረጃ የወንዱና የሴቱ የሥራ ድርሻና ኃላፊነቶች መረዳት

ለስልጠናው የሚያስፈልግ ግዜ:-

30 ደቂቃ

አስፈላጊ ቁሳቁሶች

ተገላጭ ቻርት፥ ማስመሪያ ፥ መፃፊያ ማርከር

4.2. ደረጃ በደረጃ የሚሰሩ ተግባራት

| ቅደም ተከተል | ዝርዝር ተግባራት |
|---|---|
| ደረጃ 1 | ወንድና ሴቶች ተሳታፊዎች ለሁለት(2) በመክፈል ቡድኖችን እንዲመሰርቱ ማድረግ። "ዕለታዊ የስራ ክንውን መቈጠሪያ" በንጠረዥ በመጠቀም የሥራ ድርሻቸውን በሰንጠረዥ ላይ እንዲጽፉ ይደረጋል። አስተባባሪው/ዋ ከተሳታፊዎች ከእያንዳንዱ ቡድን አንድ ሰው መርጦ/ጣ የቡድን ሥራው እንዲረዱ ያደርጋል/ታደርጋለች:: |
| ደረጃ 2 | በመስኖ ወቅት የስራ ቀን እንዲመርጡ በማድረግ በመውሰድ ለያንዳንዱ ቡድን የወንዶችና የሴቶች የሥራ ድርሻዎችና ሃላፊነቶች በተመለከተ ጥያቄ በመጠየቅ ማብራሪያና ይሰጣሉ። መብት አላቸው፤ |

የሴቶች አለታዊ ስራ በገጠር ሁብረተሰብ


| ሰአት | ተግባሮች |
|---|---|
| ከነጋቱ 11 ሰዓት | ከእንቅልፍ መንቃት / ውተት ማለብ |
| ከጠዋቱ 1 ሰዓት | ቁርስ ማዘጋጀት |
| ከጠዋቱ2 ሰዓት | በአማድ አፈር ማከም |
| ከጠዋቱ 3ሰዓት | በማሳ መስራት |
| ከቀኑ 6 ሰዓት | ምሳ ማዘጋጀት |
| ከቀኑ 7ሰዓት | የምግብ እቃ ማጠብ/ ከብቶች መመገብ/ ውሃ መቅዳት/ እንጨት መልቀም/ ውተት ማለብ |
| ከቀኑ 11 ሰዓት | እራት ማዘጋጀት |
| ከቀኑ 12 ሰዓት | ከብት ማሰማራት / ልጆች ማጠብ |

የወንዶች አለታዊ ስራ በገጠር ሁብረተሰብ

| ሰዐት | ተግባሮች |
|---|---|
| ከነጋቱ 11 ሰዓት | የቤትና የቤተሰብ አባላት ደህንነት ፍተሻ |
| ከጠዋቱ12 ሰዓት | ከእንቅልፍ መንቃት / ደህንነት ፍተሻ |
| ከጠዋቱ1:30 ሰዓት | ቁርስ መመገብ |
| ከጠዋቱ 2 ሰዓት | የስራ ስምሪት መስጠት |
| ከጠዋቱ 3 ሰዓት | በማሳ መስራት |
| ከቀኑ 7 ሰዓት | ምሳ መመገብ አረፍት |
| ከቀኑ 10 ሰዓት | ጓደኞች ማግኘት |
| ከምሽቱ 1 ሰዓት | ለእራት አረፍት |
| ከሌሊቱ 4 ሰዓት | ወደ መኝታ |

8

የስርዓተ ጾታ ትንተና ቅፅ 3 (በአማርኛ)



1 Qophii

Qophii | Guyyaa 1 | Guyyaa 2

Qabxiilee armaan gadii mirkaneeffachuu:

- Osoo leenjii kooriniyaa hin jalqabbiin dura, qonnaan bultootni xiyyeeffannaa hunduu akka leenjii koorniyaa irratti hirmaatan beeksisuu
- Dhiiraa fi dubaartiin leenjii irratti hirmaachuu isaani mirkaneeffachuu.
- Yommuu mariin garee gaggeessan dhiirrii fi dubaartiin iddoo tokko taa'uu isaanii mirkaneeffachuu. Yoo iddo tokko taa'aan yaadaa isaanii karaa bilisisa ta'een waljijjiiruu ni danda'uu.

Haala mijeessitoonni (ogeessi koorniyaa fi Hojjatan Misoomaa) qonnaan bulaan akka hirmaanna ho'aa taasisu kakaasuu.

- Qonnan bulaan waan hirmaatoonni hojjachaa jiranii fi kaayyoon isaa maal akka ta'e akka hubatan hordofaa jirachuu isaanii mirkaneeffachuu.
- Dhiirrii fi dubartii barbaachiisummaa fi itti gaafatamummaa bay'ina hojii jiru addan qoddachuun qabsiisuu.
- Erga huba nnoon dabale
  - Dhiirrii hojii ulfaataa dubarti irraa jiru ni hubatu,hojii qonnaatiif qofaa osoo hin taanee maatii isaanillee ni gargaaru.Erga hubannoon dabalee warrii dhiiraa hadha warraa isaanii ni deeggaruu. kanaafuu dubaartoonni hojii alatiinis irra caalaa isaanii bu'a qabeessaa ta'u danda'u.
  - Dubartiin yeroo gahaa hojii qonnaatiif waan kennaniif galii mana isaanii ni dabalu.

Qonnan bulaan tokko tokko marii irratti karaa ho'a ta 'en hirmaachuu dhabuun waan baratama ta'edha.
Dhimma kanaaf haala mijeessiotoonni filannoo isaanii ni gaafatu.

የስነ-ጾታ ስልጠና መግቢያ በአፋን ኦሮሞ

## 9.8. ፎቶግራፍ




የአሰልጣኞች ስልጠና በወረዳ የስርዓተ ጾታ ኤክስፐርት



ለአርሶ አደሮች የስርዓተ ፆታ ስልጠና በወረዳ ኤክስፐርት ኦሮሚያ ክልል



ለአርሶ አደሮች የስርዓተ ፆታ ስልጠና በወረዳ ኤክስፐርት ሲሰጥ (ጃቢጣህናን ወረዳ አማራ ክልል)



ለአርሶ አደሮች የስርዓተ ፆታ ስልጠና በወረዳ ኤክስፐርት ሲሰጥ (ደቡብ አቸፈር ወረዳ አማራ ክልል)

### ሳጥን 1 /Column1: ስለ አንድ በግብርና የሚተዳደር ቤተሰብ አባወራ ታሪክ

ከእለታት አንድ ቀን ለመሰብሰብ የደረሰ ቲማቲሜን ለመሸጥ በማሰብ በጠዋቱ ከቤት ወጥቼ ገበያ ፍለጋ ተጓዝኩኝ ። እኔ ሩቅ ገበያ ፍለጋ ላይ ስደከም አንድ ገዥ ወደ ቤቴ መጣና ሚስቴን አገኛት። ሰውየው ሚስቴን ቲማቲሙን ትሸጥለት ዘንድ ከቻለች ጠየቃት። ነገር



ግን ለመሸጥ ምንም ስልጣን ስላልነበራትና የኔም እቅድም ባለማወቋ እንደማትችል ነገረችው። የኔው ገበያ ፍለጋ ውጤት ኣልባ በመሆኑ ወደ ቤቴ አመራሁኝ ። ቤት በደረስኩ ጊዜ ባለቤቴ የእለቱ ኹነቶች አወራችኝ። ባመለጠኝ እድል በጣም መጥፎ ስሜት ተሰማኝ። የደረሰ ቲማቲሜን የምሸጥበት ቦታ ባለማግኘቴ ተበላሽቶ ቀረ።

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለስልጠናው ተሳታፊ አርሶ አደሮች ጠይቁ፦

- ✓ በታሪኩ የሰማችሁት ሁኔታ በእናንተ አጋጥሞ ያውቃልን?
- ✓ ችግሩ የተከሰተው ለምን ይመስላችኋል?
- ✓ ይህ አይነት ችግር እንዴት ሊቀረፍ ይችላል?

### Column2:- ስለ አንዲት በግብርና የምትተዳደር ቤተሰብ የአባወራ ሚስት ታሪክ

ባለቤቴ “ቀይ ሽንኩርት ትርፋማ መሆኑ ሰምቻሉሁኝ። ጠቅላላ ማሳችን ቀይ ሽንኩርት እንትከለው” ብሎ ነገረኝ። እኔ ግን እንዲህ በማለት ሀሳቡን ተቃወምኩት “አዎን እስማማለሁ ነገር ግን በግማሽ ማሳ ይሁን ፣ መላው ማሳችን ኣይሆንም አልኩት ምክንያቱም በርካታ ሌሎች አርሶ አደሮች ቀይ ሽንኩርት እንደተከሉ ኣይቻለሁ። በተጨማሪም ገና ብዙ ሰዎች ቀይ ሽንኩርት እንተክላለን ሲሉ ሰምቻለሁ። ምርታችን ለገበያ በምናደርሰበት ወቅት ዋጋው እንደሚቀንስ አውቃለሁ ። ባለቤቴ ግን ያልኩትን አልሰማኝም፣ ያሰበውን ብቻ አደረገ። በመጨረሻም እንደገመትኩት ከፍተኛ ኪሳራ ደረሰብን ። ከዚህ መራራ ልምድ በኋላ ግን ባለቤቴ “በዚህ ወቅት ምን ሰብል ብናመርት ጥሩ ይመስልሻል” በማለት ይጠይቀኝ ያማክረኝ ጀምሯዋል።



ለስልጠናው ተሳታፊ አርሶ አደሮች ጠይቁ፡-

✓ ተመሳሳይ ሁኔታ በእናንት አጋጥሞ ያውቃልን?

✓ ችግሩ የተከሰተው ለምን ይመስላችኋል?

✓ ይህ አይነት ችግር እንዴት ሊቀረፍ ይችላል ትላላችሁ?



**ነጥቦች፡-በስነ-ጾታ ስርጸት ላይ**

ብዙ ጊዜ ሴቶች በስነ-ፆታ (ጄንደር) ስልጠና በንቃት ስለማይሳተፉ ሀሳባቸውንና ልምዳቸውን አይገልጹም፡፡ በስነ-ጾታ (ጄንደር) ስልጠናዎችና አውደጥናቶች ሴቶች ከስነ-ጾታ ጋር የተያያዙና ሌሎች ሀሳቦቻቸውንና ልምዳቸውን እንዲገልፁ ሊበረታቱ ይገባል፡፡ባልና ሚስት በ(ስነ-ጾታ-Gneder) እና (ጾታ-Sex) መካከል ያለውን ልዩነት ላይ ተከታታይ ግንዛቤ መፍጠር በቤተሰብና በማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ችግሮች እየቀነሱ ሊሄዱ ይችላሉ፡፡

## ድምጽ ከኢትዮጵያ መስክ ላይ

**ባልና ሚስት ፡ የግብርና ስራን በጋራ የመምረጥ ሚና**



“ሁለታችን ባልና ሚሰት የስርዓተ ፆታ ስልጠና በወሰድነዉ መሰረት በጋራ ተወያይተን የማምረትና የመወሰን መብት እንዳለን ተረድተናል፡፡.

ከስልጠናዉ በፊት የእርሻ ስራዉን የምመራዉና የምወስነዉ፡ ገንዘብ የማስቀምጠዉ እኔ በራሴ ብቻ ነበር ፤ ባለቤቴ በገንዘብ ላይ ምንም ድርሻ አለነበራትም፤ ሞባይል ስልክ አልነበራትም፡ለሰራተኞች ክፍያ የምፈፅመዉ እኔዉ እራሴ ብቻ ነበርሁ፤ በአጋጣሚ ዘግይቼ ከመጣሁ እኔን እንዲጠብቁ ታደርግ ነበር ፡፡

አሁን ባለቤቴ በራሷ ክፍያ ትፈፅማለች ፤ የራሷ ሞባይል ስልክ አላት ፤ እኔ በሌለሁበት ወቅት ገዥዎች ሲመጡ በስልክ ከኔ ጋር ደዉላ ተወያይትን በጋራ ወስነን ሽያጭ ትፈፅማለች፤ የራሷ የቁጠባ ባንክ አካዉንት ከፍታ ትቆጥባለች፤ በአሁኑ ወቅት በእርሷና በኔ መካከል ጥሩ ግንኙነት አለ፡፡”

**አቶ አቢቲ ሀጂ ወሰና.** (አርሶ አደር ፤ ሻያ ቀበሌ ፤ ሎዴ ሀጦሳ ወረዳ ፤ አርሲ ዞን ፤ኦሮሚያ ክልል)

## 10. ደረጃ 10: የልምድ ልውውጥ ጉብኝት በማዘጋጀት የአርሶ አደሮችን የመማር ፍላጎት ማነሳሳት

| አራት (4) ደረጃዎች | ዋና ዋና ተግባራት (Activities) |
|---|---|
| 1. ግቡን እና ዓላማውን ለአርሶ አደርና ለአጋር አካላት ማስተዋወቅ | - የትውውቅ ፕሮግራም ማካሄድ |
| 2. የአርሶአደሮችን ግንዛቤ ማሳደግ | - አሳታፊ መሰረታዊ መረጃ የዳሰሳ ጥናት<br>- የገበያ ጥናት |
| 3. የአርሶአደሮችን ውሳኔ ሰጭነት አቅም ማሳደግ | - የሰብል መምረጥ<br>- የሚያጋጥሙ ችግሮችን ልየታ ፣ የሰብል አመራረት የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀትና ማለማመድ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የባለድርሻ አካላት መድረክ ማዘጋጀት |
| **4. የአርሶአደሩን እዉቀትና ክህሎት ማሳደግ** | - በገበሬ ማሳ ላይ ስልጠና መስጠት<br>- የስርዓተ ፆታ ስልጠና በመስጠት ግንዛቤ ማሳደግ<br>- **(እንደ አስፈላጊነቱ) የልምድ ልውውጥ እና ጉብኝት ማካሄድ** ⬅ አዚህ ጋር ነን<br>- የመስክ ቀን/ የልምድ ልውውጥ ጉብኝት |
| የክትትልና ግምገማ (አሳታፊ የመጨሻ ውጤት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድን ያካትታል) | |

### 10.1. መግቢያ

በተመረጡ ሰብሎች የልምድ ልውውጥ ቁልፍ ተግባር በመሆኑ ልምድ ለማካፈል፣ የአመራረት ዘዴ፣ እውቀትና መልካም ልምዶች ለመማር፣ እንዲሁም አነስተኛ ማሳ ባለቤት የሆኑትን አርሶአደሮች በሆርቲካልቸር ሰብል ያላቸውን አስተሳሰብና አመለካከት መቀየር ትኩረት ያደረገ ነው ። በመሆኑም ተሳታፊዎች የቀሰሙትን እውቀትና ቴክኒካዊ ልምዶች በቀላሉ በራሳቸው ማሳ ላይ ለመተግበር ያስችላቸዋል።

### 10.2. ዓላማዎች

- ጥሩ ልምዶችና አዳዲስ የአመራረት ስልቶች ከሞዴል አርሶአደሮች ለመቅሰም፣
- አዲስ የተመረጡ አርሶ አደሮች አሁን የሚያጋጥማቸው ተግዳሮት ልምድ ካላቸው አርሶ አደሮች ልምድ በመቅሰም እንዴት እንደሚፈቱት ይማራሉ፣
- የአርሶአደሮችን አስተሳሰብ፣ ግንዛቤ ለመለወጥ እና ለማሻሻል።

### 10.3. የልምድ ልውውጥ ጉብኝት አተገባበር

#### 10.3.1. ተሳታፊዎች

**አዘጋጅ /አመቻች**:- ፈጻሚ ክልል፣የዞንና ወረዳ ባለሞያዎች፤ ፐሮገራሙ የሚካሄድበት ክልል፣ ዘንና ወረዳ ባለሙያ ከሰብል ልማት፣ የሆርቲካልቸርና ኤክስቴንሽን ቡድን።

ክትትልና ድጋፍ :- የክልል ከፍተኛ ባለሙያ

**ከክልል:-** ሁለት(2) ባለሙያዎች

**ከዞን:-** አንድ(1) ባለሙያ

**ከወረዳ**:- አንድ(1) ባለሙያ

**ከቀበሌ:** የልማት ሰራተኞች እንደአሰፈላጊነቱ ከታቀፉ ቀበሌዎች ከእያንዳንዳቸው 3 የልማት ሰራተኛ)

**የአርሶ አደር ተወካዮች፡-ከታቀፉ ቀበሌዎች** ከአንድ ቡድን ስድስት (6) አርሶ አደር (የጾታ ምጣኔው እኩል ቢሆን ይመረጣል) ማስታወሻ:- ከፍተኛው ጠቅላላ የተሳታፊዎች ቁጥር 50 ሰው ይደርሳል። ነገር ግን ባለው በጀት መጠን፣ በተሸከርካሪ አቅምና መኝታ መኖር ይወሰናል።

### 10.3.2. የልምድ ልውውጥ የሚወስደው ጊዜ

ከ3 እስከ 5 ቀን

### 10.3.3. የልምድ ልውውጥ ቦታ

ለጉብኝት የሚመረጠው ቦታ የሚመረጠው በአቅራቢያው ካሉት ቦታዎች በተነጻጸሪ ዘመናዊ የሆርቲካልቸር ሰብል አመራረት ልምድ ያለው መሆን አለበት።

**ሰንጠረዥ 17.** በአርሲ ዞን የተዘጋጀ የልምድ ልውውጥ ጉብኝት ናሙና የድርጊት መርሃ ግብር

| ቀን | ሰዓት | የሚከናወኑ ተግባራት | አዳር |
|---|---|---|---|
| **ታህሳስ 16** | 2:00 ከጠዋቱ | የተመረጡ አርሶ አደሮች መቂ ይደርሳሉ | መቂ |
| **ታህሳስ 17** | 3:00 - 5:30 | አርሶአደሮች ወደ ዱግዳ ወረዳ ቴፖ-ጮሮኬ ቀበሌ ጉዞ ይጀምራሉ።<br>አርሶአደሮች የቲማቲም እርሻ ይጎበኛሉ። | መቂ |
| | 5:30 - 6:30 | ጉዞ ወደ አዳሚ ቱሉ ወረዳ፣ ኢዶጎጆላ ቀበሌ፡ ጥቅል ጎመን ማሳ ጉብኝት | |
| | 6:30 - 7:00 | ጉዞ መልስ ወደ መቂ | |
| | 7:00 - 8:30 | የምሳ ዕረፍት | |
| | 8:30 - 10:30 | ጉዞ ወደ ቦራ ወረዳ ኢላን ቀበሌ።<br>አበሻ ጎመን እና ቀይ ሽንኩርት ማሳዎች ጉብኝት | |
| | 10:30 - 11:30 | አርሶአደሮች ጋር ውይይት እና ማጠቃለያ ፕሮግራም | |
| **ታህሳስ 18** | 2:30 - 4:30 | ጉዞ ወደ አዳማ እና አዳማ ገበያ ጉብኝት ለገበያ ጥናት | ወደ ቤት መልስ |
| | 4:30 - 6:00 | መልስ ወደ አሰላ | |

## 10.4. የልምድ ልውውጥ ጉብኝት፣ የተሳታፊዎች ብዛትና በጀት ለማዘጋጀት የሚረዳ ናሙና ቅጽ

| የክፍያ ዓይነት | የቀን ብዛት | የሰው ብዛት |
|---|---|---|
| ሻይና ቡና አገልግሎት (በቀን 2 ጊዜ) | 3 | 51 |
| አበል (ለአርሶ አደሮች) | 4 | 28 |
| አበል (ለቀበሌ የልማት ሰራተኞች) | 2 | 16 |
| አበል (ለወረዳ) | 2 | 6 |
| አበል (ለዞን) | 2 | 2 |
| አበል (ለክልል) | 2 | 2 |
| ለአውቶቢስ ኪራይ | 3 | 1 |
| ነዳጅ (ለክልል) | 3 | 1 |

**ከላይ የተዘረዘሩትን ቁጥሮች ግምታዊ ማሳያ ስለሆኑ አስፈጻሚ አካላት የእያንዳንዱ ወረዳ ተጨባጩ ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት በትግበራ ጊዜ ማስተካከል ይችቻላሉ።*

## 10.5. የልምድ ልውውጥ ጉብኝት ዕቅድ ዝግጅት

### 10.5.1. ከጉብኝት በፊት የሚሰሩ ተግባራት

ውጤታማ የልምድ ልውውጥ ለማካሄድ ቢያንስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት መከናወን ይኖርባቸዋል፡፣


- **መጀመሪያ፡**- የልምድ ልውውጥ ዓላማ መለየትና ማስቀመጥ (የልምድ ልውውጥ ማካሄድ ምን አይነት (የዕውቀት፣ የክህሎት እና የአመለካከት ክፍተቶችን) መሙላት የሚያስችል እንደሆነ በግልጽ መለየት ያስፈለጋል። **ለምሳሌ**፡-አርሶ አደሮች በህብረት ግብዓት መግዛትና ምርት መሸጥ እንዲችሉ ማበረታታት። የሰብል ቅኝት በማካሄድ ተባይ እና በሽታ መቆጣጠር፣ ወይም በገበያ ፍላጎት መሰረት የተመዘገበ ምርጥ ዘር መጠቀም፣ ወ.ዘ.ተ)
- ጉብኝት በሚደረግበት ቦታ የተሻሉ አርሶ አደሮች (ግንባር ቀደም ገበሬዎች) ፈልጎ ወይም መርጦ በማዘጋጀት የጉብኝቱ

ፕሮግራሙ የተሳካ እንዲሆን ጥረት ማድረግ።

- ጉብኝት የሚደረግበት ቀን ለፕሮግራሙ ዓላማ ይበልጥ የተሻለ ወቅት መምረጥ።
- ከመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት ጋር በመመካከር ተወካይ እንዲሰይሙ ማመቻቸት። በተቻለ መጠን ወንድና ሴት እኩል ውክልና እንዲኖራቸው ማበረታታትና መተግበር።
- ስለ ተወካይ አርሶ አደሮች ሚናና ሀላፊነት በግልጽ ማሳወቅ፣ እነዚህም:
  - ✓ ከጉብኝት መልስ ለተቀሩት አርሶ አደሮች ወይም ቡድኖች የተገኘውን ልምድ ማካፈል ፣
  - ✓ ከልምድ ልውውጥ በተገኘ ተሞክሮ ቢያንስ ሶስት (3) ለህብረተሰቡ ጠቃሚ የሆኑ ቁልፍ አሰራሮች ወይም ዕውቀቶች/ክህሎቶች (ሰብል ማፈራረቅ፤ ተጓዳኝ ሰብል አተካከል/ companion planting፣ የተቀናጀ የተባይና በሽታ ቁጥጥር ዘዴ፣ ወ.ዘ.ተ) ሰርተው ማሳየት እንደሚጠበቅባቸው ማሳወቅ። ይህም ለሰርቶ ማሳያ የሚሆን መደብ (ማሳ) መመደብ ያካትታል (ዕዝል 2.10.1)
- ዋናው የጉብኝት ቀን ከመድረሱ አስቀድሞ የቀበሌ ልማት ሰራተኞች፣ የወረዳና የዞን ባለሙያዎች ቅድመ-መስክ ጉብኝት ማድረግ አለባቸው። ለዚህ ልምምድ አጋዥ ናሙና ቅጽ (ዕዝል 2.10.2) ተያይዟል። በዚህ ልምምድ አርሶ አደሮች ትክክለኛ የሰብል የአመራረት ዘዴ ካለ በመሳሪያ መለካትን ይማራሉ።

**ስዕል 17.** ልኬትን በተግባር መለማመጃ ፎርምእ

**የሰውነት ክፍሎቻቹ በመጠቀም መለካት**

| የሰውነት ክፍሎች | ርዝመት (ሴ.ሜ) |
|---|---|
|  | |

## 10.6. የልምድ ልውውጥ ጉብኝት አተገባበር

- እያንዳንዱ ተሳታፊ አርሶ አደር ከዞን እስከ ወረዳ ድረስ በርካታ ቦታዎችን ይጎበኛሉ። በዚህ ሂደት የልማት ሰራተኞች ለአርሶ አደሮች ከመስክ ጉብኝቱ የታዘቡትን ቁምነገሮች በማስታወሻና በፎቶግራፍ እንዲመዘግቡ ያበረቷቷቸዋል። በዚህ መረጃ መሰረት ተሳታፊ አርሶ አደሮች ስለ መስክ ቀኑ ግብረ መልስ እንዲሰጡ ማድረግ። ከጉብኝት ጉዞ በኋላ ወደ አካባቢያቸው ሲመለሱ በማስረጃ የተደገፈ አጠቃላይ ግብረ መልስ እንዲሰጡ ያግዛቸዋል።
- በመስክ ጉብኝት ማጠናቀቂያ ዕለት የማጠቃለያ ግምገማ ማድረግ አስፈላጊ ነው። በስብሰባው ወቅት፣ ተሳታፊዎች የሚከተሉትን ነጥቦች ጨምሮ ሃሳብ መለዋወጥ ይኖርባቸዋል ከነዚህም ውስጥ:-
  - ✓ ከመስክ ጉብኝቱ ምን እንደታዘቡና እንደተማሩ፣
  - ✓ በመስክ ጉብኝቱ ከሁሉም በላይ መሳጭ ሁኖ ያገኙት ምን እንደነበር፣
  - ✓ አርሶ አደሮች የትኛው ዕውቀትና ክህሎት በራሳቸው ማሳ መተግበር እንደሚችሉ ፣
  - ✓ በተቀባይና አስተናጋጅ አርሶ አደሮችና በጎብኚ አርሶ አደሮች መካከል ያለው ልዩነት ምንድ ነው?

**ከመስክ ጉብኝት በኋላ የግብረ መልስ ክፍለ ጊዜ አተገባበር**

- ተሳታፊ ተወካይ አርሶ አደሮች ግብረ-መልስ የሚሰጡበት አመቺ ቀንና ሰዓት መወስን አለባቸው፣
- ተሳታፊዎች/ በተወካዮቻቸው በመስክ ጉብኝት ስላዩት ነገር እለታዊ ማጠቃለያ ግብረ መልስ ውጤቶች በረፖርት መልክ

በማደራጀት መቅረብ አለበት፣

- የሪፖርቱ አቀራረብ ግልጽና ተሳታፊዎች በቀላሉ ሊረዱት በሚችሉት መልክ መቅረብ አለበት። ተወካይ አርሶ አደሮችና የልማት ሰራተኞች በመስክ ጉብኝት ያነሱት ፎቶዎችና ቪዲዮዎች ከሪፖርታቸው ጋር በማቀናጀት ማቅረብ ይችላሉ።
- ከመስክ ጉብኝቱ የታዘቡትንና የተማሩትን አዲስ ዕውቀት እንዴት በተግባር በመተርጎም ችግራቸውን መቅረፍ እንደሚችሉ መወያየት።

**የማስፈፀሚያ ፍንጭ:- የልምድ ልውውጥ ማካሄድ ለምን አስፈለገ?**

የልምድ ልውውጥ ጉብኝት ማካሄድ የአርሶ አደሮችን አስተሳሰብ በመቀየር፣ የተመረጡ የግብርና አሰራሮችን ተግባራዊ እንዲያደርጉና ቢዝነስ-ተኮር እንዲሆኑ ያስችላቸዋል።

## 10.7. ቀጥሎ መሰራት ያለባቸው ተግባራት

- ለህብረተሰቡ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ግብረ መልስ እንዲሰጡ ማድረግ፤
- የዞን፣ የወረዳ ባለሙያዎች፣ የቀበሌ ልማት ሰራተኞችና በአርሶ አደሮች የትግበራ መርሃ-ግብር መሰረት ቀጣይነት ያለው ክትትላዊ ድጋፍ መስጠት ይጠበቅባቸዋል።

## 10.8. ገላጭ ፎቶግራፎች



ስለ ጉብኝቱ ዓላማዎች እና መርሀ-ግብር ለተሳታፊ አርሶአደሮች በልማት ሰራተኞች በአውቶብስ ውስጥ ማብራሪያ ሲሰጥ



አርሶአደሮች የቲማቲም አመራረት፣ ምርት እና ትርፍ በተመለከተ ነጥቦች ላይ ልምድ እየቀሰሙ



ጎብኚ አርሶ አደሮች ከመስክ መልስ በኋላ በልማት ሰራተኞች ድጋፍ በመስክ ጉብኝት የተማሩትን በግብረ-መልስ መመዝገቢያ ወረቀት ላይ ሲሞሉ



ጎብኚ አርሶ አደሮች ከተቀባይ አርሶ አደር ጋር በመስኖ አጠቃቀም ዙርያ የልምድ ልውውጥ ሲያደርጉ



የልማት ሰራተኞች በዛፍ ጥላ ስር የማጠቃለያ መርሃ-ግብር ሲያካሂዱ



ተሳታፊዎች የገበያ ቅኝት እያደረጉ (አዳማ)



**ነጥቦች፡- በስነ-ጾታ ስርጸት ላይ**

አብዛኛው ጊዜ ሴቶች በሚካሄዱ የልምድ ልውውጥ ጉብኝቶች ስለማይሳተፉ በራሳቸው ማሳ ላይ በተግባር ሊያውሉት የሚችሉት የግብርና የቴክኒክ ዕውቀታቸውንና ክህሎታቸውን ማዳበር አይችሉም።

ስለዚህ ሴቶች በማሳቸው በተግባር የሚያውሉት የግብርና የቴክኒክ ዕውቀትና ክህሎት እንዲኖራቸው በተቻለ መጠን ባልና ሚስት በልምድ ልውውጥ ጉብኝት እንዲሳተፉ ቢደረግ የተሻለ ይሆናል።
በሌላ በኩል ባልና ሚስት በልምድ ልውውጥ ያገኙትን ዕውቀት፤ክህሎት፤ ልምድና ሀሳብ

## ልምድ ልውውጥ ከቀሰሙ አርሶ አደሮ

**የልምድ ለዉዉጥ ጉብኝት ለእኔ የበለጠ እንድነሳሳ አድርጎኛል**



“በልምድ ልዉዉጥ ጉብኝት መሳተፌ በጣም አነሳስቶኛል፤ሌሎች አርሶ አደሮች ከእኛ በበለጠ በጥንካሬና በጥሩ ሁኔታ መስራታቸዉን ተረድቻለሁ ። የሚያመርቱት በኪራይ መሬት ነዉ፤ የመስኖ ዉሃ የሚያገኙት የዉሃ መሳቢያ ሞተርና ነዳጅ ገዝተዉ ነዉ ። እኛ ግን የምናመርተዉ በራሳችን መሬት የዉሃ መሳቢያ ሞተርና የነዳጅ ወጪ ሳናወጣ በመሆኑ እድለኞች ነን፤ ይህን ወጪ አዉጥተዉም የእርሻ ማሳቸዉ አያያዝና እንክብካቤ ከኛ በተሻለ ደረጃ በመስራታቸዉ ትምህርት ወሰጃለሁ። የሰብል ፈረቃና እርቀት አጠቃቀምንም ከነሱ ተምሬ በራሴ ማሳ ላይ ተግበራዊ አድርጌአለሁ ።”

**አቶ. ሹራማ አባ ጋሮ** (አርሶአደር ፤ ዋሮ ኮሎቦ ቀበሌ፤ ዲዶ ወረዳ፤, ጅማ ዞን፤ ኦሮሚያ ክልል)

**እኔ የበለጠ በጀት በመመደብ ለማምረት በራስ የመተማመን አቅም እንዲኖረኝ ረድቶኛል**



“ቀደም ሲል የአትክልት ዘር የምንገዛዉ በዝቅተኛ ዋጋ በአገኘነዉ ከየትም ቦታ ነበር ፡፡ የዘሩን ጥራትና ደረጃ ፤ የምርታማነት ሁኔታ ከግምት ዉስጥ አናስገባም ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ትክክለኛ ጥራትና ምርታማ የሆኑ ዝርያዎችን ስለማንጠቀም ዉጤታማ ባለመሆናችን ወጪ አዉጥተን በስፋት ለማምረት እንጠራጠር ነበር፡፡ አሁን ግን በዚህ በበካፍታ ቀበሌ ተገኝተን በአገኘነዉ የልምድ ልዉዉጥ (ተሞክሮ) ከፍተኛ ጥራት ያላቸዉ ዘሮች ዋጋቸዉ ከፍተኛ ቢሆንም የሚያስገኙት ምርትና ትርፋማነት ከፍተኛ መሆኑን ለመረዳት ችያለሁ፡፡ ከዚህ በኋላ ለተሻለ ዘር የተሻለ ዋጋ የሚያስፈልገዉ መሆኑንና ሁሉም ዝርያዎች እኩል ዋጋ የማይኖራቸዉ መሆኑን ስለተረዳሁ ለተሻለ ዘር የተሻለ ወጪ አዉጥቼ በብዛትና በጥራት ለማምረት ተነሳስቻለሁ፡፡”

**አቶ. ኢልካን ቦጋለ** (አርሶ አደር.፤ቱልታ ቀበሌ፤ አንከሻ ወረዳ ፤አዊ ዞን፤አማራ ክልል

## 11. ደረጃ 11: የመስክ ጉብኝት ቀን/ የገበሬ በዓል ማዘጋጀት

| አራት (4) ደረጃዎች | ዋና ዋና ተግባራት (Activities) |
|---|---|
| 1. ግቡን እና ዓላማውን ለአርሶ አደርና ለአጋር አካላት ማስተዋወቅ | - የትውውቅ ፕሮግራም ማካሄድ |
| 2. የአርሶአደሮችን ግንዛቤ ማሳደግ | - አሳታፊ መሰረታዊ መረጃ የዳሰሳ ጥናት<br>- የገበያ ጥናት |
| 3. የአርሶአደሮችን ውሳኔ ሰጭነት አቅም ማሳደግ | - የሰብል መምረጥ<br>- የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለየታ ፣ የሰብል አመራረት የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀትና ማለማመድ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የባለድርሻ አካላት መድረክ ማዘጋጀት |
| **4. የአርሶአደሩን እዉቀትና ክህሎት ማሳደግ** | - በገበሬ ማሳ ላይ ስልጠና መስጠት<br>- የስርዓተ ፆታ ስልጠና በመስጠት ግንዛቤ ማሳደግ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የልምድ ልውውጥ እና ጉብኝት ማካሄ[ድ]<br>- **የመስክ ቀን/ የልምድ ልውውጥ ጉብኝት** |
| የክትትልና ግምገማ (አሳታፊ የመጨሻ ውጤት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድን ያካትታል) | |

አዚህ ጋር ነን

### 11.1. መግቢያ

የመስክ ጉብኝት ቀን የፕሮጀክቱ ነባር አርሶ አደሮች ከፕሮጀክቱ ስለ ተማሩት ነገር ለአዲስ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት አባላትና ሌሎች ተሳታፊዎች (በፕሮጀክቱ ያልታቀፉ የአርሶ አደር አባላት) እንዲያጋሩ ዕድል ይፈጥራል።

### 11.2. ዓላማዎች

- የአርሶ አደር ተወካዮች ከጉብኝቱ የተማሩትን ተግባር ልምዳቸውን በአካባቢያቸው ላሉ አርሶ አደሮች ያስተላልፋሉ።
- ተሳታፊዎች (በፕሮጀክቱ ያልታቀፉ አርሶ አደሮችና **የ**ልማት ሰራተኞች) ገበያ-ተኮር ስልት ላይ ያተኮረ ትምህርት እንዲቀስሙ ያስችላል ።
- የስኬታማ አርሶ አደሮች ልምድ በማጋራት የአርሶ አደር አባላት ተነሻሽነት መጨመር።

### 11.3. የመስክ ጉብኝት ቀንን አጠቃላይ ሂደት ማቀድ

#### 11.3.1. ተሳታፊዎች

**አስተባባሪ/አመቻች**:- የወረዳ ባለሙያዎች፤ የቀበሌ ልማት ሰራተኞች እና አርሶአደሮች ተወካዮች (ቡድን)

**ክትትልና ድጋፍ**:- በክልል የፕሮጀክቱ የቴክኒክ አማካሪ እና በዞን ባለሙያዎች

**ተሳታፊዎች**: የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበር አባላት፣ ተጠቃሚ አርሶ አደሮች እና የቀበሌ ልማት ሰራተኞች

#### 11.3.2. የሚወስደው ጊዜ

የአርሶ አደር የመስክ በዓል የሚወስደው ግማሽ ቀን ሲሆን በተመረጠ ማሳ ላይ እንደሰብሉ የዕድገት ደረጃ 3 ዙር የመስክ ቀን ማድረግ ይቻላል። የጊዜው መርዘም ወይም ማጠር ትኩረት የተደረገበት ምክንያት ና እንደየ የሰብል እድገት ደረጃ ሊለያይ ይችላል።

#### 11.3.3. የመስክ ጉብኝት የሚደረግበት ቦታ

የመስክ ጉብኝት ቦታ ሲመረጥ ከተቀባይ አርሶ አደር ተወካዮች ጋር በመመካከር ሊመረጥ ይገባል። በጉብኝቱ መርሃ-ግብር በርካታ ሠርቶ ማሳያዎች/ማሳዎች ሊካተቱ ይችላሉ። ነገር ግን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላኛው ቦታ ያለው ርቀት በጥንቃቄ ሊገመገም ይገባል።

**ሰንጠረዥ 18.** የመስክ ጉብኝት ዕቅድ ምሳሌ

| ሰዓት | ተግባሮች |
|---|---|
| 2:00 - 2:30 | የተሳታፊዎች ምዝገባ |
| 2:30 - 2:45 | የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር በተቀባይ ህብረተሰብ ተወካይ |
| 2:45 - 3:00 | መግብያ እና የቀኑ ድርጊት ጊዜ ሰሌዳ ማስተዋወቅ |
| 3:00 - 3:50 | የመጀመርያ መስክ መጎብኘት:- ቁልፍ የመማር ነጥቦችን አጠር ያለ መረጃ ለአርሶ ኣደሮች እና ልማት ወኪሎች ገለጻ ይደረጋል። ስኬቶችና በመስክ ከመተግበር ትምህርት ማስተዋውቅ |
| 4:00 - 4:50 | 2ኛ መስክ (ማሳ) ጉብኝት ማደረግ |
| 4:50 - 5:30 | የማጠቃለያ ውይይት፡- ከተሳታፊዎች ጋር ውይይት ማደረግ፡ ምን እንደተማሩና እና እንዴት በራሳቸው ማሳ /ኑሮ እንዴት ሊጠቀሙበቸው እንደሚችሉ መወያየት። |
| 5:30 - 6:30 | የምሳ እረፍት/ቀላል ምግብ (አንደ ኣስፈላጊነቱ) |

## 11.4. በጀት ለማዘጋጀት የሚረዳ ናሙና ቅጽ

| የክፍያ ዓይነት | የቀን ብዛት | የሰው ብዛት |
|---|---|---|
| ሻይ/ቡና (በቀን 1 ጊዜ) | 1 | 40 |
| አበል (ለቀበሌ የልማት ሰራተኞች) | 1 | 8 |
| አበል (ለወረዳ) | 1 | 5 |
| አበል (ለዞን) | 1 | 2 |
| አበል (ለክልል) | 1 | 1 |
| የመጓጓዣ ወጪ (ለቀበሌ ልማት ሰራተኞች) የመጓጓዣ ወጪ | 1 | 8 |
| ነዳጅ ለሞተር ሳይክል (ለወረዳ) | 1 | 5 |
| ነዳጅ ለሞተር ሳይክል (ለዞን) | 1 | 1 |
| ነዳጅ ለመኪና (ለክልል) | 1 | 1 |

**ከላይ የተዘረዘሩትን ቁጥሮች ግምታዊ ማሳያ ስለሆኑ አስፈጻሚ አካላት ነባራዊ ሁኔታን ከግምት ውስጥ በማስገባት በትግበራ ጊዜ ማስተካከል ይቻላል።*

## 11.5. የመስክ ጉብኘት ቀን

- የወረዳ ባለሙያዎችና የቀበሌ የልማት ሰራተኞች የመስክ ጉብኝት በትክክል ስለመታቀዱ ማጣራት እና በታው ድረስ በመሄድ የአስተናጋጅ አርሶ አደሮችን /ማሳ መምረጥ።
- የመስክ ጉብኝት ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት፣ የወረዳ ባለሙያዎችና የልማት ስራተኞች አርሶ አደሮችን ለማስተማር የለዩአቸውን ነጥቦች ክለሳ ማድረግና በተጠቃሚ አርሶ አደሮች ላይ ምን አይነት በጎ ለውጥ/ ተጽዕኖ ማምጣት እንደተፈለገ ግልጽ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።
- ለአርሶ አደር አባላትና የመስኖ ውሀ ተጠቃሚ ማህበራት ጉብኝት የሚካሄድበትን ቀን፤ ጊዜና ቦታ ቢያንስ ከሁለት(2) ሳምንታት አስቀድሞ በግልጽ ማሳወቅ፣
- አስፈላጊ ቁሳቁሶችን ለጉብኝት ማዘጋጀት፣ ተንቀሳቃሽ ድምፅ ማጉያ (በመስሪያታችሁ ካለ)፣ ባትሪ ድንጋይ የሚሰራ መሆኑን ማረጋገጥ።
- በሚጎበኘው ቦታ ፕሮጀክቱን ለማስተዋወቅ የሚያስችሉ ፅሁፎችን ወይም ምልክቶችን ተሳታፊዎች በቀላሉ ሊረዱት በሚችል ሁኔታ የሚታይ ስዕላዊ መግለጫዎችን፤ በራሪ ወረቀቶችን፣ ፕሮጀክቱን የሚገልጹ ፅሁፎችን፣ ባነሮችን፣ የሠርቶ ማሳያው ገላጭ ምልክቶችን በተቀባይ ዞን፣ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች ከቀበሌ ልማት ወኪሎች ጋር በመሆን ማዘጋጀት።

## 11.6. የመስክ ጉብኘት ቀን ዝግጅት ሂደት

- የተመረጠውን ቀንና ቦታ ለጉብኝቱ ተሳታፊዎች ማሳወቅ/ ይፋ ማድረግ። በ በገበያ ቦታ እና የቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት ማስታወቂያ መለጠፍ ውጤታማ ዘዴ ሊሆን ይችላል።

- ከተቻለ ነጋዴዎች፣ ደላሎች፣ ጅምላ ሻጮች በመስክ በዓል ቀን እንዲሳተፉ መጋበዝ፤ የምርት ፍላጎታቸውን በተለይ በጥራት እና በመጠን በጅምላ ከሚወስዱ አካላት ጋር የውይይት መድረክ ይፈጥራል።
- የወረዳ ባለሙያዎችና የልማት ሰራተኞች ትኩረታቸው የአርሶ አደሮች ውይይት ማመቻቸት ላይ መሆን አለበት። የዚህ ጉብኝት ዋና ተዋናዮች አርሶ አደሮች መሆናቸው ማስታወስ ይገባል።

**የትግበራ ፍንጭ:- የመስክ ቀን ማካሄድ ለምን አስፈለገ ?**
የመስክ ቀን ተግባራዊ እንዲደረግ የሚታቀድበት ምክንያት በግብርና ስራዎች መልካም ልምዶችን ለማስፋትና፣ የሽፐ-ዘዴ አሰራሮችን ለማስተዋወቅ እንዲሁም በሽፐ-ዘዴ በተሻሻሉ አሰራሮች፣ አዳዲስ አሰራሮች ለማስፋፋት (scale up) ለማድረግ ያስችላል።

## 11.7. በቀጣይ መሰራት ያለባቸው ተግባራት

- በአርሶአደሮች ማሳ ላይ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣
- አርሶ አደሮች በሠርቶ ማሳያው አተገባበርና ስለ አገኙት አዲስ ትምህርት ገለጻ እንዲያደርጉ፣ በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ እና ስለ መስክ ጉብኝቱ ግብረ መልስ እንዲሰጡ ውይይት ማድረግ።

## 11.8. ገላጭ የሆኑ ፎቶ ግራፎች



የመስክ ጉብኝት ቀን መርሃ-ግብርና ዓላማዎችበተመለከተ በባለሙያዎች ገለጻ ሲደረግ



በመስክ ጉብኝት ቀን አርሶ አደሮች የአትክልት ማሳዎችን ሲጎበኙ






ተቀባይ/አስጎብኚ አርሶ አደሮች በሠርቶ ማሳያው ስለ ሰብሉ አመራረትና ግብይት ልምዳቸውን ሲያካፍሉ

## የገበሬ በዓል ከቀሰሙ አርሶ አደሮች የቀረበ ተሞክሮ

**ማየት ማመን ነዉ፡**



“በዚህ የአርሶ አደሮች የመስከ ቀን ተገኝቼ በአየሁት የጥቅል ጎመን ማሳ ስፋትና አሰራር በጣም ተገርሜአለሁ ። እነዚህ አርሶ አደሮች ለመሸጥ ማምረት የሚለዉን መርህ ተከትለዉ ለገበያ ብለዉ ማምረታቸዉን እንድረዳ አድረጎኛል ። እኔና የኔ ቡድን አባላት የጥቅል ጎምን ለማምረት የክሽክሽ ተባይ ስጋቱ ስለአለብን በገበያ ተፈላጊ እንደሆነ ብናዉቅም አናመርትም ነበር። አሁን ግን በዚህ የመስክ ቀን ክሽክሽን በቀላሉ መከላከል እንደሚቻል ጥሩ ትምህርተ አግኝተናል ። ይህ የተማርነዉ ትምህርት ማየት ማመን ነዉና በቀጣይ በስፋት እንድናመርት የሚያበረታታንና የበለጠ እንድንሰራ አቅም የሚሆነን በመሆኑ ወደ ተግባር ለመቀየር ቃል እንገባለን”

**ከአዊ ዞን በመስክ ቀን ጉብኝት ተገኝተዉ ሃሳባቸዉን ካካፈሉ አርሶ አደሮች የተወሰደ**

# ምዕራፍ 3: ድጋፋዊ ክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ

# ክትትልና ግምገማ



## 1. መደበኛ ክትትል

| አራት (4) ደረጃዎች | ዋና ዋና ተግባራት (Activities) |
|---|---|
| 1. ግቡን እና ዓላማውን ለአርሶ አደርና ለአጋር አካላት ማስተዋወቅ | - የትውውቅ ፕሮግራም ማካሄድ |
| 2. የአርሶአደሮችን ግንዛቤ ማሳደግ | - አሳታፊ መሰረታዊ መረጃ የዳሰሳ ጥናት<br>- የገበያ ጥናት |
| 3. የአርሶአደሮችን ውሳኔ ሰጪነት አቅም ማሳደግ | - የሰብል መምረጥ<br>- የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለየታ ፣ የሰብል አመራረት የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀትና ማለማመድ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የባለድርሻ አካላት መድረክ ማዘጋጀት |
| 4. የአርሶአደሩን እዉቀትና ክህሎት ማሳደግ | - በገበሬ ማሳ ላይ ስልጠና መስጠት<br>- የስርዓተ ፆታ ስልጠና በመስጠት ግንዛቤ ማሳደግ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የልምድ ልውውጥ እና ጉብኝት ማካሄድ<br>- የመስክ ቀን/ የልምድ ልውውጥ ጉብኝት |
| **የክትትልና ግምገማ (አሳታፊ የመጨሻ ውጤት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድን ያካትታል)** | |

እዚህ ጋር ነን

### 1.1. መግቢያ

የክትትልና ድጋፍ መርሃግብር የታቀዱ የቴክኒካዊ ስራዎችን አተገባበር ለመከታተልና ለመደገፍ የሚያስችል የክትትልና ድጋፍ መረሃግብር በወረዳና በልማት ሰራተኞች ይዘጋጃል፡፡ ተጠቃሚ አርሶ አደሮች በልማት ሰራተኞች የሚደገፉትን የምክርና የስልጠና ተግባራት ምን ያህል እንደተረዱትና ተግባራዊ እንዳደረጉት ለመገንዘብ ይረዳል። የድኅረ-ትግበራ ግምገማ ደግሞ በፕሮጀክቱ የተካተቱት አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች መሳካታቸውን ለማረጋገጥ/ የተዘጋጁ ዝርዝር ዕቅዶች መፈጸማቸውን በመመዘን መረጃ መስጠት ይጠበቅበታል።

### 1.2. ዓላማው

የክትትልና ድጋፍ ተግባር ዓላማ የታቀዱ ስራዎች (በጊዜ፣ በዉጤት፣ በሃብት አጠቃቀም) የአፈጻጸም ደረጃ ለማወቅ እንዲሁም ተጠቃሚ አርሶ አደሮች ያጋጠማቸውን ችግሮች በመለየትና በመደገፍ ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡

### 1.3. መደበኛና ወቅታዊ የክትትል ተግባር አሰራር

#### 1.3.1. ተሳታፊዎች

- **አዘጋጅ/ፈጻሚ አካል፡-** የወረዳ ሃላፊዎችና ባለሙያ ፣የልማት ሰራተኞች፡፡
- **ተቆጣጣሪና ድጋፍ ሰጭ አካል፡-** የፌዴራል፣ የክልልና የዞን ሃላፊዎችና ኤክስፐርቶች
- **ተሳታፊዎች**:- የተጠቃሚ አርሶ አደሮች አባላት።

#### 1.3.2. የሚወስደው ጊዜ፡-

አንድ (1.0) ቀን ለአንድ ቡድን፣

የክትትልና ድጋፍ ድግግሞሽ፡- የክትትልና ድጋፍ ስራ በተከታታይ ሳይተጓጎል መካሄድ ያለበት ተግባር ነዉ ፡፡ ይህም በፌደራል ደራጃ በየ3 ወሩ፣ በክልል ደረጃ በየ2 ወሩ ፣ በዞን ደረጃ በወር አንድ ጊዜ ፣ የወረዳ ባለሞያ በሳምንት አንድ ጊዜ፣ በቀበሌ ደራጃ ተከታታይ የሆነ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋሉ።

#### 1.3.3. የሚከናወንበት ቦታ

➢ ስራዎች በተከናወኑባቸዉ/ በተጠቃሚ አርሶ አደሮች ማሳ፤

### 1.4. የክትትልና ግምገማ በጀት ለማዘጋጀት የሚረዳ ናሙና ቅጽ

የክትትልና ግምገማ የበጀት ፍላጎት ዕቅድ ምሳሌ

| የክፍያ ዓይነት |
| --- |
| የዉሎ አበል (ለወረዳ/ለዞን/ለክልል/ ለፌደራል ባለሙያና ሹፌሮች) |
| **ለቀበሌ ባለሙዎች ለ ሞባይል ስልክ ወጪ** |
| ለትራንስፖርት/ለነዳጅ ወጪ) |

**የሚስፈልገዉ ቀን ብዛት፣ ሰዉ ሃይል መጠን ፣ የክትትል ድግግሞሽ በዛት ከላይ በቁጥር 1.3.2 መሰረት ይሆናል።.*

## 1.5. ለክትትል ድጋፍ ትግበራ ቅድመ ዝግጅት ማካሄድ

- የፌደራለ፡ ክልል፣ ዞን ኤክሰተርቶች የክትትልና ድጋፍ እቅድ ያዘጋጃሉ፣ በእቅዱ መሰረት የራሳቸው ቼክሊስት በማዘጋጀት ለወረዳዎች ያሳዉቃሉ።
- የወረዳ ሃላፊዎች ፣ ኤክስተርቶችና የቀበሌ ባለሙያዎች ከአርሶአደሮች ጋር በመወያት ከትትልና ድጋፍ የሚካሄዱበት ቦታና ቀን ያካተተ ቸክሊት በማዘጋጀት ያመቻቻሉ ።
- የወረዳ ግብና ፅ/ቤት የመስከ ጎብኝት ለማካሄድ ሚወስደዉን ጊዜና የሚስፍልገዉን ወጪ ከግምት በማስገባት የጉብት አካሄዱን ከዞንና ከክልል ጋር በማዉያት ያመቻቻል ።
- የቀበሌ ባለሙያዎች በአርሶ አደሮች ማሳ የሚካሄደዉን የመስክ ክትትልና ድጋፍ ለመምራት የራሱን ቅድመ ዝግጅት ያደርጋል ።

## 1.6. የክትትል ድጋፍ ትግበራ እንዴት ይካሄዳል?

- የወረዳ ኤክስተርቶችና ሃላፊዎችና የቀበሌ ባለሙያዎች በእቅዳቸዉ መሰረት የአርሶ ደሮችን ማሳ በመጎብኘት የጋጠሙ ችግሮችና ክፍተቶችን በመለየት የሙያ ድጋፍ የደርጋሉ፣
- የፌደራለ፡ ክልል፣ ዞን ኤክሰተርቶች በወረዳ ኤክተርቶችና የቀበሌ ባለሙያዎች አመቻችነት የአርሶ አደር ቡድኖችን ማሳ በመጎብኘት የተከናወኑ ተግባራትን ግምገማ ያካሂዳሉ ፣ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በማሳት ሙያዊ ደጋፍ ይሰጣሉ ፣
- በክትትልና ድጋፍ ቅኝት ወቅት በሚያገኙት የስራ ዉጤት መሰረት የአርሶ አደሮችንና ቀበሌ ባለሙያዎች ብቃትና ክፍተት በመለየት ሙዊ ድጋፍ ያደርጋሉ፣
- የክትትልና ደጋፍ ወቅት የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችነ በመለየት የግብረመለስ ሪፖረቶችን በማዘጋጀት በየደረጃዉ ለሚመለካተቸዉ አካላት ያቀርባሉ ።

**የትግበራ ፍንጭ:- መደበኛ ክትትል መተግበር ለምን?**
የተገኙትን ለውጦች ለማወቅና የተግባራት አፈጻጸም ደረጃ በመመዘን ሞያዊ ድጋፍ (ምክረ-ሀሳብ) ለልማት ሰራተኞችና አርሶ አደሮች ለመስጠት ነው።

## 1.7. በቀጣይ የሚከናወኑ ተግባራት

- የወረዳ ኤክስተርቶች በክትትልና ድጋፍ ወቅት የተከናወኑ ስራዎችን ከአመታዊ እቅዶችና መረሃግብር ጋር በማገናዘብ በመገምግምና ዉጤታቸዉን በመለየት አፈጻጸማቸዉን ለዞንና ወረዳ በሪፖርት መልክ ያሳዉቃሉ። ለቀበሌና ለአርሶ አደር ቡድን አባላት በግብረመልስ ይልክሉ ።
- በክትትልና ግምገማ ወቀት ተገኙ መላካም ተሞክሮዎችና አሰራሮች በመቀመር በቀጣ ለሚከናወኑ ተግባራት አተገባበር በግብዓትነት /በማሰተማሪነት እዲዉሉ ይደረጋል።

## 1.8. ገላጭ ፎቶ ግራፍ



### የአርሶ አደሩ - ድምጽ ከኢትዮጵያ መስክ



**የባለሙዎች ክትትልና ደጋፍ መተኪያ የሌለዉ ተግባር ነዉ፡**

“ኤክሰፐርቶቸና የቀበሌ ባለሙዎች የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ያደርጉልናል ። በየጊዜዉ ማሳችንን ዉስጥ በመዝለቅ ስለ ማዳበሪያ አጨማመር ተባይና በሽታን እንዴት እንደምንለይና እንደምንከላከል በተግባር ያሳዩናል፡ያሰተምሩናል ። እኛም በተግባር ስለምናየዉና በማሳ ላይ ስለምንማር ወደ ተግባር ለመቀየር አንቸገርም” ።

**ቄስ ብርሃኔ ዉበት** (አርሶ አደር፤ የጨረቃ ቀበሌ ፤ደንበጫ ወረዳ፤ምዕራብ ጎጃም ፤ ዞን አማራ ክልል)

# ክትትልና ግምገማ



## 2. የመጨረሻ ዳሰሳ ጥናት

| አራት (4) ደረጃዎች | ዋና ዋና ተግባራት (Activities) |
|---|---|
| 1. ግቡን እና ዓላማውን ለአርሶ አደርና ለአጋር አካላት ማስተዋወቅ | - የትውውቅ ፕሮግራም ማካሄድ |
| 2. የአርሶአደሮችን ግንዛቤ ማሳደግ | - አሳታፊ መሰረታዊ መረጃ የዳሰሳ ጥናት<br>- የገበያ ጥናት |
| 3. የአርሶአደሮችን ውሳኔ ሰጭነት አቅም ማሳደግ | - የሰብል መምረጥ<br>- የሚያጋጥሙ ችግሮችን ልየታ ፣ የሰብል አመራረት የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀትና ማለማመድ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የባለድርሻ አካላት መድረክ ማዘጋጀት |
| 4. የአርሶአደሩን እዉቀትና ክህሎት ማሳደግ | - በገበሬ ማሳ ላይ ስልጠና መስጠት<br>- የስርዓተ ፆታ ስልጠና በመስጠት ግንዛቤ ማሳደግ<br>- (እንደ አስፈላጊነቱ) የልምድ ልውውጥ እና ጉብኝት ማካሄድ<br>- የመስክ ቀን/ የልምድ ልውውጥ ጉብኝት |
| **የክትትልና ግምገማ (አሳታፊ የመጨሻ ውጤት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድን ያካትታል)** | |

እዚህ ጋር ነን

### 2.1. መግቢያ

የመጨረሻ ዳሰሳ ጥናት ውጤት ፈጻሚ አካላትን በምክር አግልግሎት (ኤክስቴንሽን) ተግባራት የአፈጻጸም ደረጃ መረጃ ማለትም በሰብል ምርት፤ የተሻሻሉ የሰብል አመራረትና የግብይት አሰራር ተግባራዊ ማድረግና በገቢ አመላካቾች የመጣው ለውጥ በተመለከተ ጠቋሚ መረጃዎች ለመሰብሰብ ይረዳል። በዚህ የክትትል ተግባር፣ አርሶ አደሮችና የኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ያላቸውን ዕውቀት ይለካሉ። እንዲሁም ሙያዊ/ ቴክኒካዊ ክፍተት በመለየት ምን አይነት ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ለማወቅ ወሳኝ ሚና አለው።

### 2.2. ዓላማዎች

- አርሶ አደሮች በሆርቲካለቸር ሰብሎች ልማት የመተግበር አቅም፡ የግብይት ሂደታቸዉን ፣ የወጪና ገቢያቸዉን አፈፃጸም ላይ ያለዉን ልዩነት በማወዳደር የተገኘዉን የተጣራ ገቢያቸዉ ላይ የመጣዉን ለዉጥ ለማወቅ ያስችላል፡፡
- ይህ ጥናት የሚከናወነው መሰረታዊ መረጃ (መነሻ ጥናት) በተካሄደበት መጠይቅ/ ፎርም መሰረት ሆኖ በሁለቱም ጥናቶች የተገኙ ውጤቶችን በማነጻጸር በአርሶ አደር ቡድኖች ዘንድ የመጣውን ለውጥ ለማወቅ ይቻላል።

### 2.3. የክትትልና የመጨረሻ ዳሰሳዊ ጥናት አተገባበር

#### 2.3.1. ተሳታፊዎች

- **አዘጋጅ/ፈጻሚ አካል ፡-** የወረዳ ባለሙያና የልማት ሰራተኞች
- **ክትትልና ድጋፍ ፡-ፌደራል፣ ክልል፣** የዞን ኤክስፐርቶች
- **ተሳታፊዎች**:- የተጠቃሚ አርሶ አደሮች አባላት

#### 2.3.2. የሚወስደው ጊዜ

አንድ(1) ቀን ለአንድ ቡድን

#### 2.3.3. ቦታ

በተሳታፊ አርሶ አደሮች አቅራቢያ የሚገኝ አማካይ ቦታ መሆን አለበት። ዛፍ ጥላ ስር ወይም በገበሬዎች ማሰልጠኛ ማዕከል (FTC) መሆን ይችላል።

### 2.4. ወቅታዊ ክትትል/ የመጨረሻ ዳሰሳ ለማከናውን የሚያስፈልግ በጀት ለማዘጋጀት የሚረዳ ናሙና ቅጽ

| የክፍያ ዓይነት | የቀን ብዛት | የሰው ብዛት |
|---|---|---|
| የዉሎ አበል (ለወረዳ ኤክስፐርቶች) | 1 | 2 |
| የዉሎ አበል (ለፌደራል፣ ለክልል፣ ለዞን ኤክስፐርቶችና ሹፌሮች) | 1 | TBD** |
| ለትራንስፖርት/ ነዳጅ ወጪ | 1 | TBD** |
| ለቁሳቁስ (ፍሊፐ ቻርት፣ ማርከር፣ ክሊፐቦርድ) | 1 | 1 |
| ለቁሳቁስ (ለቅጸ ቅጽ ማባዛትና እስክርቢቶ) | 1 | 45 |

*ከላይ የተዘረዘሩትን ቁጥሮች ግምታዊ ማሳያ ስለሆኑ አስፈጻሚ አካላት የእያንዳንዱ ወረዳ ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት በትግበራ ጊዜ ማስተካከል ይችላሉ።

**TBD፦ እንደሁኔታው የሚወሰን

## 2.5. የመጨረሻ ግምገማ ጥናት እንዴት እንደሚዘጋጅ

- የወረዳ ባለሙያዎች የጥናት ቀንና በታ ከልማት ሰራተኞችና ከተጠቃሚ አርሶ አደሮች ጋር በመመካከር ያመቻቻሉ፣
- የቀበሌና ወረዳ ባለሙዎች በተሳታፊ አርሶ አደሮች ዘንድ የሚካሄደዉን ቅኝት/ጉብኝት ያስተባብራሉ፣
- የወረዳ ባለሙያዎች በመጠይቁ ላይ የራሳቸውን አስተያየት አክለውና በበቂ ቁጥር ኮፒዎች በማባዛት ዝግጁ ያደርጋሉ።

## 2.6. የመጨረሻ ዳሰሳ ጥናት እንዴት እንደሚተገበር

- የወረዳ ኤክስፐርቶችና የቀበሌ ባለሙያዎች መረጃ መሰብቢያ ቅፆችን ለአርሶ አደሮች በማንበብ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸዉ የማደረግ ስራ ይሰራሉ
- ለዳሰሳ ጥናቱ ትግበራ አመቺ የሆነ ቀን መወሰን (ዝርዝር አሰራሩን በተመለከተ ገጽ33. ደረጃ2. አሳታፊ መነሻ ጥናት ይመልከቱ) ፡ ፡

**የትግበራ ፍንጭ: የመጨረሻ ዳሰሳ ጥናት ለምን አሰፈለገ?**

ይህን ጥናት ማካሄድ የወረዳ ባለምያዎችና የቀበሌ ልማት ሰራተኞች በተጠቃሚ አርሶ አደሮች ዘንድ የዕውቀት፣ ክህሎትና ገቢ አመላካቾችን፣ የተገኘው መሻሻል ደረጃ ለማወቅ ያስችላል። ተጠቃሚ አርሶ አደሮች ደግሞ የአሁኑ ሁኔታ ከበፊቱ ሁኔታቸው ጋር በማነጻጸር ያገኙት መሻሻል ለማወቅ ያስችላቸዋል ፡፡

## 2.7. በቀጣይ መሰራት ያለባቸው ተግባራት

የዞንና ወረዳ ባለሙያዎች በኤክስቴሽን ምክር አገልግሎቱ በዓመቱ መጨረሻ ዳሰሳ ጥናት የተሰበሰበውን መረጃ /የጥናቱ ውጤት ትንተና በመስራት ለዞን አመራር ቡድን ያጋራሉ። በተመሳሳይ መልኩ ከልማት ሰራተኞች ጋር በመመካከር ለተጠቃሚ አርሶ አደሮች ግብረ-መልስ ይሰጣሉ።

## 2.8. ፎቶግራፍ



የሸፐ ፐሮጀችት የመሰረታዊ መረጃ/ መነሻ ዳሰሳ ጥናት ሲካሄድ

# ተያያዥ ሰነዶችና ቅጾች ዝርዝር

ሁሉም ቁሳቁሶች ከሚከተለው URL (ጃይካ ድህረ ገጽ) ሊወርዱ ይችላሉ።
https://www.jica.go.jp/project/english/ethiopia/010/materials/index.html

## ምዕራፍ 2: የ"ኢትዮ-ሼፕ" ፕሮጀክት የትግበራ ሂደት መመሪያ

**2-1: የዝግጅት ሂደት**

| ሰነድ ቁጥር | የሰነዱ ርዕስ | የሰነዱ ዓይነት |
|---|---|---|
| **ቅድመ ዝግጅት 1፡ የማስተዋወቅ የምክክር መድረክና የፕሮጀክቱ የአሰራር ዘይቤ ማስረዳት** | | |
| 1.1.1 | የኢትዮ-ሼፕ ዓላማ ለአርሶ አደር የማስተዋወቅ መድረክ _ | ፕረዘንቴሽን |
| 1.1.2 | የፕሮጀክቱና አጋር አካላት ተግባርና ኃላፊነት | ፕረዘንቴሽን |
| 1.1.3 | የኢትዮ-ሼፕ ፕሮጀክት ተግባራት የአፈጻጸም ሪፖርት | ፕረዘንቴሽን |
| 1.1.3.1 | የፕሮፖዛል አሰራር ዝርዝር መግለጫ | ፕረዘንቴሽን |
| 1.1.3.2 | የፕሮፖዛል/ የመነሻ ዕቅድ _ቅጽ | ፕረዘንቴሽን |
| 1.1.3.3 | ሀንድአውት_የመነሻ ዕቅድ/ፕሮፖዛል _ሰነድ | ሀንድአውት |
| 1.1.4 | የአርሶ አደሮች መምረጫ መስፈርት | ፕረዘንቴሽን |
| 1.1.5. | መረጣ በተመለከተ የተወሰነ የአእምሮ ዳሰሳ (brainstorming) | ፕረዘንቴሽን |
| **ቅድመ ዝግጅት 2. የፕሮጀክት ወረዳዎች መረጣ** | | |
| 1.2.1. | የመስክ ግምገማ ሰነድ | ሀንድ አውት |
| **ቅድመ ዝግጅት 3: የሼፕ የአሰልጣኞች ስልጠና የምክክር መድረክ/ዎርክ-ሼፕ ሂደት (SHEP ToT)** | | |
| 1.3.1 | ስለ ኢትዮ-ሼፕ ፕሮጀክት መግቢያ | ፕረዘንቴሽን |
| 1.3.2 | ሥርዓተ-ፆታ፡ ሥርዐተ-ፆታ ለምን? | ፕረዘንቴሽን |
| 1.3.3 | የሥርዐተ-ፆታ ትንተና | ፕረዘንቴሽን |
| 1.3.4 | የማስተዋወቅ የምክክር መድረክ | ፕረዘንቴሽን |
| 1.3.5 | መነሻ ጥናት (Baseline_Survey) | ፕረዘንቴሽን |
| 1.3.6 | የገበያጥናት፤ሰብል መረጣና የሰብል አመራረት መርሃ ግብር ዝግጅት | ፕረዘንቴሽን |
| 1.3.7 | የገበያ ትስስር ፎረም | ፕረዘንቴሽን |
| 1.3.8 | የስራ ድርሻና ሀላፊነት | ፕረዘንቴሽን |
| 1.3.9 | የተሳታፊዎች የመምረጫ መስፈርት | ፕረዘንቴሽን |
| 1.3.10.1 | በፕሮጀክቱ መነሻና መዳረሻ ጥናት_ለ24 ጥያቄዎች (ጥ_24) | ቅጽ |
| 1.3.10.2 | የሰብል መረጣ ቅጽ | ቅጽ |
| 1.3.11.1 | ምሳሌ፡-የሰብል መረጣ ቅጽ | ቅጽ |
| 1.3.12.1 | የገበያ ጥናት ቅፅ | ቅጽ |
| 1.3.12.2 | ምሳሌ፤-የገበያ ጥናት | ቅጽ |
| **ቅድመ-ደረጃ 4: ተጠቃሚ አርሶ አደሮች ማህበራት/ቡድን መምረጥ** | | |
| 1.4.1. | የቡድን መምረጫ መስፈርት | ቅጽ |

**2-2: የአርሶ አደሮች ስልጠና**

| ሰነድ ቁጥር | የሰነዱ ርዕስ | የሰነዱ ዓይነት |
|---|---|---|
| **ደረጃ 1: የአርሶ አደር ተወካዮች የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም ማዘጋጀት ከመስኖ ማህበራት ለተመረጡ ተወካይ አርሶ አደሮች** | | |
| **ደረጃ 2. አሳታፊ መነሻ የዳሰሳ ጥናት** | | |
| 2.2.1 | በፕሮጀክቱ መነሻ_እና-መጨረሻ/መዳረሻ ጥናት-ጂ 24 | ቅጽ |
| 2.2.2 | በፕሮጀክቱ መሰረታዊ/ መነሻ_እና_መጨረሻ_ ጥናት_ጥ_CP እና IA | ቅጽ |
| **ደረጃ 3: የገበያ ጥናት** | | |
| 2.3.1 | ቅጽ፡-_የገበያ ጥናት | ቅጽ |
| 2.3.2 | ምሳሌ፡-_የገበያ ጥናት | ቅጽ |
| 2.3.3 | የገበያ ጥናት _ቅጽ_ኤክሰል | ቅጽ |
| **ደረጃ 4: የሚመረተው ሰብል መረጣ** | | |
| 2.4.1 | ቅጽ፡-_የሰብል መረጣ ቅጽ | ቅጽ |
| 2.4.2 | ምሳሌ፡-_የሰብል መረጣ ቅጽ | ቅጽ |

| | | |
|---|---|---|
| 2.4.3 | ቅጽ፡-_የሰብል መረጣ ቅጽ_ኤክሰል | ቅጽ |
| **ደረጃ 5: የገበያ ትስስር መድረክ** | | |
| 2.5.1 | ለገበያ ትስስር ፎረም የሚቀርብ ስለ ኢትዮ-ሼፕ ምልከታ | ፕረዘንቴሽን |
| **ደረጃ 6: ኢትዮ-ሸፕ ቴክኒካዊ የአሰልጣኞች ስልጠና (ቴ.አ.ስ)** | | |
| 2.6.1 | የስልጠናው ዓላማዎች | ፕረዘንቴሽን |
| 2.6.2 | መግቢያ | ፕረዘንቴሽን |
| 2.6.3 | አሆሰአ እና ድምአቴ (ጂ- 24) | ፕረዘንቴሽን |
| 2.6.4 | የቦካሺ ዝግጅት | ፕረዘንቴሽን |
| 2.6.5 | ተባይና-በሽታ መቆጣጠር | ፕረዘንቴሽን |
| 2.6.6 | የሰብል_ማምረቻ-የጊዜ-ሰሌዳ | ፕረዘንቴሽን |
| 2.6.7 | የድርጊት_መርሃ-ግብር አዘገጃጀት | ፕረዘንቴሽን |
| **ደረጃ 7: አሳታፊ የችግሮች ትንተና፣ የሰብል ጊዜ ሰሌዳ እና የበጀት ዝግጅት አሰራር** | | |
| 2.7.1 | የሰብል_ማምረቻ-የጊዜ-ሰሌዳ - በእንግሊዝኛ | ቅጽ |
| 2.7.2 | የሰብል_ማምረቻ-የጊዜ-ሰሌዳ - በአማርኛ | ቅጽ |
| 2.7.3 | የሰብል_ማምረቻ-የጊዜ-ሰሌዳ - በኦሮምኛ | ቅጽ |
| **ደረጃ 8: በገበሬ ማሳ ላይ ስልጠና** | | |
| 2.8.1 | ካሚሺባይ የስልጠና ሰነድ፡- በእንግሊዝኛ | ፒ.ዲ.ኤፍ |
| 2.8.2 | ካሚሺባይ የስልጠና ሰነድ፡- በአማርኛ | ፒ.ዲ.ኤፍ |
| 2.8.3 | ካሚሺባይ የስልጠና ሰነድ፡- በኦሮምኛ | ፒ.ዲ.ኤፍ |
| 2.8.4 | ፅሑፍ-በእንግሊዝኛ | ፒ.ዲ.ኤፍ |
| 2.8.5 | ፅሑፍ-በአማርኛ | ፒ.ዲ.ኤፍ |
| 2.8.6 | ፅሑፍ-በኦሮምኛ | ፒ.ዲ.ኤፍ |
| **ደረጃ 9: የሥርዐተ-ፆታ ግንዛቤ ለማሳደግ የተዘጋጀ የስልጠና ማንዋል** | | |
| 2.9.1 | የስልጠና ማንዋል: የሥዓተ-ፆታ ግንዛቤ ለማሳደግ የተዘጋጀ - በእንግሊዝኛ | ፒ.ዲ.ኤፍ |
| 2.9.2 | የስልጠና ማንዋል: የሥዓተ-ፆታ ግንዛቤ ለማሳደግ የተዘጋጀ - በአማርኛ | ፒ.ዲ.ኤፍ |
| 2.9.3 | የስልጠና ማንዋል: የሥዓተ-ፆታ ግንዛቤ ለማሳደግ የተዘጋጀ - በኦሮምኛ | ፒ.ዲ.ኤፍ |
| **ደረጃ 10: የልምድ ልውውጥ ጉብኝት በማዘጋጀት የአርሶ አደሮችን የመማር ፍላጎት ማነሳሳት** | | |
| 2.10.1 | ቅድመ ድህረ የመስክ_ዝግጅት | ቅጽ |
| 2.10.2 | የማጣሪ ሺትና አካላዊ ልኬት | ቅጽ |
| 2.10.3 | ናሙና_ፕሮግራም_እና_በጀት | ቅጽ |

**ምዕራፍ 3: ክትትልና ግምገማ**

### 1. መደበኛ ክትትል

| ሰነድ ቁጥር | የሰነዱ ርዕስ | ዓይነት |
|---|---|---|
| 3.1.1 | የሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ | ቅጽ |
| 3.1.2 | ምሳሌ፡-_የሪፖርት ማቅረቢያ_ቅጽ | ቅጽ |
| 3.1.3 | የተዘጋጀ ናሙና ሪፖርት | ቅጽ |

### 2. የፕሮጀክት የመጨረሻ ግምገማ ጥናት/ Endline survey

| ሰነድ ቁጥር | የሰነዱ ርዕስ | ዓይነት |
|---|---|---|
| 3.2 | የፕሮጀክት መጨረሻ ጥናት_ቅጽ | ቅጽ |

### 3. የኢትዮ-ሼፕ (SHEP) የተግባር እውቀት መመዘኛ መጠይቅ/ ቴስት

| ሰነድ ቁጥር | የሰነዱ ርዕስ | ዓይነት |
|---|---|---|
| 3.3 | የኢትዮ-ሼፕ (SHEP) የተግባር እውቀት መመዘኛ መጠይቅ | ቅጽ |

Japan International
Cooperation Agency